አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ ፣ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃግብር

# ራስን ፍለጋ፣ በአለማየሁ ገላጋይ ሶስት የተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ፣ ስነልቦናዊ ንባብ

ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ

በ

ገ/ጻዲቅ ቢያዝን

2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ ፣ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃግብር

# ራስን ፍለጋ፣ በአለማየሁ ገላጋይ ሶስት የተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ፣ ስነልቦናዊ ንባብ

ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ

በ

ገ/ጻዲቅ ቢያዝን

አማካሪ

አየለ ፍቅሬ ( ዶ/ር)

2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ ፣ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃግብር

# ራስን ፍለጋ፣ በአለማየሁ ገላጋይ ሶስት የተመረጡ ልቦለዶች ውስጥ፣ ስነልቦናዊ ንባብ

ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ

በ

ገ/ጻዲቅ ቢያዝን

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ______________________________ | __________________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | |
| ______________________________ | __________________ |
| የውጪ ፈታኝ ስም | |
| ______________________________ | __________________ |

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ ይህን ጥናት ጀምሬ እንዳጠናቅቅ ለረዳኸኝ ለልዑል እግዚአብሔር ከእናትህ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር የተመሰገንክ ሁን፡፡ በመቀጠል ከጥናቱ ከዚህ እንዲደርስ በዚህ ደረጃ የማይመጥን ስህተት ስሳሳት እንኳን አንድም ቀን ሳይሰለቹ ሙያዊ አስተያየትና ድጋፍ ላደረጉልኝ  ለአማካሪዬ ዶ/ር አየለ ፍቅሬ ከልብ አመሰግንዎታለሁ፡፡ በመጨረሻ ስማርም ሆነ ይህን ጥናት ሳደርግ አንድም ቀን ከጎኔ ላልተለያችሁኝ እና ውድ ጊዜያችሁን ለሰጣችሁኝ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ መባፅዮን አባተ እና ለልጆቼ እጅግ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ሥነፅሁፍ እና እንደ ስነልቦና አይነት ሌሎች የትምህርት መስኮችን ወስዶ የሥነፅሁፍ ንባብ ማድረግና ጹሁፋዊ ትንተና መከወን በሀገራችን ኢትዮጵያ እየተለመደ የመጣ የሥነፅሁፍ የጥናት መስክ ሁኗል። ነገር ግን አብዛኞቹ ጥናቶች በብሉይ ሚቶሎጅና በፍሩዲያን ንድፈሀሳብላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። ስለዚህ ራስን ፍለጋ የሚለውን ጽንሰሀሳብ ከዩንጊያን ንድፈሀሳብ አንጻር መመልከት ለመስኩ ተጨማሪ እይታ ይዞ ይመጣል። በመሆኑም ይህ ጥናትም ዋና አላማው በአለማየሁ ገላጋይ **በፍቅር ሥም፣ታለ በዕውነት ሥም እና ሐሰተኛው በእምነት ሥም** ልቦለዶች ውስጥ የራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤን በይነ-ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ መተርጎም፣ማሳየትና መፈከር ነው።

ይህ ጥናት ጽሑፍ ትንተና(Text analysis) ከሚባለው የጥናት አይነት ውስጥ ይመደባል። ለጥናቱ የተመረጡ ሶስት ልቦለዶች በታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ሲሆን ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ የሹሜትን የዩንጊያን የራስን ፍለጋ እሳቤ ዋና መገለጫዎች እና ሥረመሰረታዊያን በማቀናጀት የጽሑፍ ትንተና ተደርጓል።

የሶስቱም ታላሚ ልቦለዶች ዋና ገፀባህርይ ታለ በራስን ፍለጋ  በሁለት ዋና የህይወት አጋማሽ ሂደት ውስጥ የነበረ ሲሆን በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት የራሱን ግላዊ ክብር መገንባት ላይ አተኩሯል። ይኸውም  በማህበረሰቡ ወንድ የሚያስብለውን ጉዳዮች መፈጸም እና ራሱን በሌሎች ዘንድ የአዋቂነትን ክብር( በፍልስፍና ተከራክሮ የሚያሸንፍ) ሁኖ መገኘት ነበር። ከዚህ በመቀጠል ወደ ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት በስኬት የተሸጋገረ ሲሆን ይህ ደግሞ በዚህ ምድር የመጣበትን ዓላማ መጠየቅ፣ ፈጣሪን መርምሮ ለመረዳት እና የፈጣሪና የተፈጥሮን ግንኙነት የፈለገበት ነበር።  በታለ የራስን ፍለጋ ህይወት ያጋጠሙ ፀረራስን ፍለጋዎች መኖራቸውን ጥናቱ አረግጧል። ይህም በመጀመሪያ አጋማሽ ህይወት ያደጉ ኢጎዎችን በሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ካለማስገዛት የመነጨ ሲሆን ራስን ፍለጋው በቶሎ መልስ ካላገኘሁ የሚል በህይወት ተስፋ መቁረጥና ፍርሃት ናቸው፤ ራስን እስከማጥፋት ማሰብና መፀፀት የፀረራስን ፍለጋው ውጤቶች ናቸው። የዩንግ ሥረመሰረታዊያን ማለትም ፐርሶና፣ ሻዶው፣ አኒማ እና ሰልፍ በታለ የራስን ፍለጋ ህይወት ወስጥ  በጉልህ እንደተስተዋሉ ጥናቱ አረጋግጧል።

የዩንጊያን የራስን ፍለጋ መገለጫ እሳቤዎች እና ሥረመሰረታዊያን ለልቦለዶቹ ጭብጥ መዳበር ከፍተኛ አስተዋፆ ነበራቸው። ይህን በእያንዳንዱ እሳቤዎች ስር የተጠየቁ የራስን ፍለጋ ጥያቄዎችና የተገኙ መልሶች፣ እንዲሁም ሂደቶች ልቦለዱ እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋጽዎ አድርገዋል።

## ሙዳየ ቃላት

1. Anti-Individuation - ፀረ ራስን ፍለጋ
2. collective- ቡድን
3. conscious -ንቁ
4. Data- ውሂብ
5. Ego-ኢጎ
6. Interdisciplinary-በይነ-ዲሲፕሊናዊ-
7. Inter-textul -በይነ-ቴክስታዊ
8. Persona - ግለሰብ
9. Process -ሂደት
10. psychoanalysis- ፍካሬ ልቡና
11. psycho-social -ማህበረ ልቡና
12. Prevalence of Individuation- የራስን ፍለጋ መገኛ
13. Relationship- ግንኙነት
14. Self - ራስ
15. State -ሁነት
16. Sub conscious- ከፊል ንቁ
17. Text analysis-የጽሑፍ ትንተና
18. Two halves of life- ሁለት አጋማሽ ህይወት
19. Uncnscious -ኢ-ንቁ

# የቃላት መፍቻ

ማህበረ ልቡና- የማህበራዊ ተፅዕኖ በግለሰቦች ባህርይ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ እና በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኑነት የሚያመላክት ነው፡፡

ራስ- self የሚለውን የእግሊዝኛ ቃል የሚወክል ሲሆን እኔነታችን ወይም ከየት መጥነታችን የመፈለግመ፣ የመጠየቅና የመመርመር ሂደት እና መሆን

በይነ-ዲሲፕሊናዊ- ከአንድ በላይ የሆኑ የትምህርት መስኮችን የመመርመር ልማድ

በይነ-ቴክስታዊ- ከአንድ በላይ የሆኑ ቴክስቶችን (መጻሕፍትን) ዝምድና የሚተነተንትና የሚፈከርበት ሥነዘዴ ነው፡፡

ቡድን- በራስን ፈላጊው ግለሰብ ዙሪያ ያሉ ሁለትና ከዚያ በላይ ሰዎች ወይም የዚህ ቡድን አባላት፣ ቤተሰብ፣ የቅርብ ጓደኛ ወዘተ.

ንቁ-ይሁን ብለን  የምንተገብረው ተግባር ፣ ንቃተ ህሊና ወይም ንቁ የአዕምሮ ክፍል ሀሳብ፣ ስሜት፣ እውቀት፣ ትውስታ፣ ግንዛቤ ወዘተ.

ከፊል ንቁ፡- በትክክል የማንገነዘበው ነገር ግን በተግባራችን እና በስሜታችን ተፅዕኖ የሚያሳድር የአዕምሮ ክፍል

ኢ-ንቁ - በንቁ አዕምሯችን እየተጠቀምነበት ያልሆነ፣ የተቆጠበው ሀሳብና ስሜት ፣ የተኛውና ሰፊው የአምሯችን ክፍል ነው

የጽሑፍ ትንተና፡- ከአንድ ቴክስት ውስጥ የተለያዩ ውሂቦችን በማውጣት መተንተንና የመፈከር ስልት

ግንኙነት- ራስን ፈላጊው በተለይም በቀዳሚው የልጅነት ህይወቱ የነበረው የጠበቀ ቁርኝት ያመላክታል፡፡ በተለይም ከእናቱ፣ ከቤተሰቦቹ

ፍካሬ ልቡና- ልብን ወይም ህሊናን መፈከር፣ መተንተን ወይም መተርጎም

ማውጫ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
ሙዳየ ቃላት ........ iii
የቃላት መፍቻ ........ iv
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.3.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ ........ 3
1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር አላማ ........ 3
1.4.ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........ 3
1.5. የጥናቱ ፋይዳ ........ 4
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7 የጥናቱ ዘዴ ........ 4
1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 5
ምዕራፍ ሁለት ........ 6
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 6
2.1 ጽንሰሀሳባዊ ዳሰሳ ........ 6
2.1.1 ሥነፅሁፍና ስነልቦና ........ 6
2.2. ንድፈሀሳባዊ ማዕቀፍ ........ 8
2.1.2.. ራስን ፍለጋ ........ 9
2.1.2.1. የራስን ፍለጋ ምንነት ........ 9
2.1.2.2 የራስን ፍለጋ ጽንሰሀሳብ የእሳቤው መገለጫ ባህሪያት ........ 12
2.1.2.3 የራስን ፍለጋ ደረጃዎች (stages of individuations) ........ 18
2.1.2.4 የራስን ፍለጋ ሥረመሰረታዊያን ........ 19
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 23
ምዕራፍ ሶስት ........ 27

3.ትንታኔ ........ 27
3.1 ቡድን እና ግለሰብ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 28
3.2 . ሁለት አጋማሽ ህይወት በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 34
3.3 ግንኙነት በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 37
3.4. ሁነት ወይስ ሂደት በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 41
3.5. የራስን ፍለጋ መገኛ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 44
3.6. ፀረ ራስን ፍለጋ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 45
3.7.ራስ እና ኢጎ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 47
3.8. ራስ እና ፈጣሪ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ ........ 49
ምዕራፍ አራት ........ 53
4. ማጠቃለያና መደምደሚያ ........ 53
4.1. ማጠቃለያ ........ 53
4.2 መደምደሚያ ........ 55
ዋቢ ጽሑፎች ........ 56
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ........ 58

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ሥነፅሁፍ ደራሲዎች ስለ ሰው ልጆች እና ስላላቸው ማህበራዊ ግንኙነት ስለነበረው፣ ስላለውና ስለሚመጣው ዓለም በጥልቅና በሰላ ምናባቸው የረቀቀውን አግዝፈው፣ የተደበቀውን ገልጠው፣ የራቀውን አቅርበው ዙሪያ ገባውን ለአንባቢያን የሚያደርሱበት በቋንቋ የሚቀርብ የጥበብ ስራ ነው። በዚህም ሥነፅሁፍ የሰዎችን ግላዊና ማህበራዊ ግንኙነት፣ ግጭት፣ ፍቅር፣ ምኞት፣ ፍላጎት፣እርቅ፣ ፍርሃት ወዘተ. በዳበረ ጥበብ ይቀርብበታል። ከሥነፅሁፍ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ልቦለድ ሲሆን፣ በዚህ ዘመን ልቦለዶችን ከአላባዊያንና መዋቅራዊ ጉዳዮችን ከማጥናት አልፎ በሌሎች ተያያዥ የጥናት መስኮች ውስጥ ዘልቆ በመግባት አዲስ አይታ እና አመለካከት ለማምጣት ጥናቶች እየተሰሩ ይገኛሉ። ለዚህም እንደ ስነልቦና፣ ፍልስፍና፣ታሪክ፣ሶሾሎጅ የመሳሉት ጥናት መስኮች ውስጥ ያሉ አዳዲስ ፍልስፍናዎችንና ፊለጎችን በመውሰድ ሥነፅሁፍ ውስጥ እንዴት እንደለመዱ የመመርመርና የመፈተትና  ጥናት ማደረግ በሀገራችን በተወሰኑ የሥነፅሁፍ ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ የታየ፣ ነገር ግን ብዙ ስራ የሚጠብቀው ሆኖ ይታያል።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የጥናቱ ቀዳማይ ምንጭ የሆኑት ደራሲ አለማየሁ ገላጋይ ስራዎች **በፍቅር ሥም**(2009 ዓ. ም) ፣**ታለ በዕውነት ሥም** (2011 ዓ.ም) እና **ሀሰተኛው በእምነትሥም**(2012 ዓ.ም) ለአንባቢያን የበቁ ስራዎች ናቸው። ደራሲ አለማየሁ ገላጋይ እነዚህ ሶስት ስራዎች በፊት 8 ያክል ስራዎችን ለአንባቢያን ያበቃ ሲሆን በስራዎቹ የድህረ ዘመናዊነት ልቦለድ ማሳያ የሆኑ ልቦለዶችን አበርክቷል።

አንደ ስነልቦና፣አንትሮፖሎጅ፣ሶሾሎጂ፣ታሪክ ወዘተ. አይነት ተያያዥ የጥናት መስኮች ለመከሰቻነት ቋንቋን ከመጠቀማቸው ባሻገር የሰውን ልጆችንና እና ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ማጥናታቸው፣ በዙሪያቸው ለሚፈጠሩ ፍላጎቶችን ለማርካትና ለችግሮች መፍትሄ ለማፈላለግ የሚጥሩ በመሆናቸው ከሥነጽሑፍ ጋር በእጅጉ የተሻረቡ/የተገመዱ አድርጓቸዋል። ከዚህ ባሻገር የጥናት መስኮቹ ሊህቃን ሙያቸውን ለመግለጽ፣ ለማስተዋወቅ እና ሀሳባቸውን ለሌሎች

ለማስተላለፍ በሚያርጉት ሂደት ሥነፅሁፍ(ይበልጡን ልቦለድ) የጥናት መስኮቹ ማደሪያ ሆኗል፡ ፡በሀገራችን በሥነፅሁፍ ስራዎች ላይ ስነልቦናዊ እና መሰል ንባብ ማድረግ እየተለመደ መጥቷል፡፡ የሚደረጉ ጥናቶች በጥናት መስኮቹ መካከል ያለውን ዝምድናና መሸረብ ለማስረፅ አይን ከፋች መሆናቸውና ለሌሎች መሰል ጥናቶች መነሻ መሆናቸው የሚደነቅ ነው፡፡ ነገር ግን ክፍተቶችም ይታይባቸዋል፡፡ ከሚታዩ ክፍተቶች መካከል በሥነፅሁፍ ውስጥ የሚታዩ የሌሎች መስኮች ፈለጎችና እይታዎች በአግባቡ በሥነፅሁፍ ውስጥ መፈከርና የመተንተን እጥረት እና የሚደረጉ ሥነፅሁፋዊ ንባቦች በተወሰኑ የትምህርት መስክ ንድፈሀሳቦች ላይ ያተኩሩ መሆናቸው ነው፡፡

የእነዚህ ጥናቶች ትኩረት በብሉይሚቲዮሎጅና በፍሮይድ ሳይኮ አናላይቲካል ንድፈሀሳቦች (unconscious) ላይ ያተኩራሉ፡፡ ነገር ግን ከፍሮይድ ሳይኮ አናላይቲካል ንድፈሀሳብ በተጨማሪ የዩንጊያን አናላይቲካል ሳይኮሎጅን (collective unconscious) እንደ አንድ የስነልቦና ንድፈሀሳብ አድርጎ ስነልቦናዊ ንባብ ላይ መጠቀም የተለመደ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የዩንጊያን ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም ጥናት ባደርግ በመስኩ ላይ ሚታየውን ክፍተት በመጠኑ ይሞላል፡፡

ከዚህ መነሻ በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ በዋንኛነት በታላሚ ልቦለዶቹ ውስጥ የሚገኙ ስነልቦናዊ ይዘቶች በመፈለግ ከዩንጊያን ስነልቦናዊ ንድፈሀሳብ አንፃር በይነ-ቴክስታዊ ትንተና ማድረግ አንድ የሥነፅሁፋዊ ንባብ ጥናት አካል ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በጥናቱ ዳራ እንዳስተዋወቅኩት በመስኩ ያለው የእውቀት ክፍተት ነው፡፡ ይህም በመስኩ በእርግጥ ስነልቦናዊ ንባብ ጥናት በአንድም በሌላም መልኩ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ ጥናቶች በብሉይ ሚቶሎጅና በፍሩዲያን ትወራ(unconscious) ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ ራስን ፍለጋ የሚለውን ጽንሰሀሳብ ከዩንጊያን ትወራ(collective unconscious) አንጻር ብመለከተው ለመስኩ አዲስ እይታ ይዞ በመምጣት ያለውን ክፍተት ለመሙላት ከማሰብ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህን ጥናት እንዳደርግ ያደረጉኝ ግለሰባዊ መነሳሳቶች አሉ፡፡ እነዚህም " ሥነፅሁፋዊ ሂስ" የተሰኘውን ኮርስ ስማር ስለ በየነ-ዲስፐሊናዊ ጥናት እና ሥነፅሁፍ ሂስ አዲስ

እይታ እንዲኖረኝ በማድረጉ እና እውን ይህን የተለያዩ የትምህርት መስኮች መቀላቀል ሳይንሳዊ የአጠናን ሂደትን ተከትየ ማረጋገጥ እችላለሁ ወይ? ከሚል መነሳሳት በተጨማሪ የአለማየሁ ገላጋይ ስራዎችን ሳነብ ብዙውን ጊዜ ከልቦለድነታቸው ባሻገር ብዙ የፍልስፍ፣ የስነልቦና፣ ስነመለኮታዊ ቃላት፣ጥቅሶች፣ ሀሳቦች አገኛለሁ። በመሆኑም እነዚህን መፅሐፍት ስነልቦናዊ ንባብ ማድረግ እችልባቸው ይሆን ብዬ በማሰቤ ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ የሚከተሉት አብይና ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል።

### 1.3.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዐቢይ አላማ በአለማየሁ ገላጋይ **በፍቅር *ሥም*፣*ታለ* በዕውነት *ሥም* እና ሐሰተኛው በእምነት *ሥም*** ልቦለዶች ውስጥ የራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤን በይነ-ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ መተርጎም፣ማሳየትና መፈከር ነው።

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር አላማ

1. በልቦለድ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ የራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤዎች በምን አይነት ሁኔታ እንደተገኙ ይመረመራሉ።

2. የራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤዎቹ እንዴት ቀረቡ የሚለውን መተንተን።

3. በልቦለዶቹ ወስጥ የትኞቹ የዩንግ ሥረመሰረታዊ እንደተንፀባረቁ ማሳየት።

## 1.4.ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

1. ራስን ፍለጋ በአለማየሁ ገላጋይ **በፍቅር *ሥም*፣*ታለ* በዕውነት *ሥም* እና ሐሰተኛው በእምነት *ሥም*** ልቦለዶች ውስጥ በምን አይነት ስነልቦናዊ ሁኔታ ቀርቧል?

2. የታለን የራስን ፍለጋ ሂደት ከዩንግ የራስን ፍለጋ ንድፈሀሳብ አንፃር ምን ይመስላል።

3. በራስን ፍለጋው የትኞቹ የዩንግ ሥረመሰረታዊያን በጉልህ ተንፀባረቁ?

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት በዋንኛት በመስኩ ሰፋ ብለው የተሰሩ የምርምር ስራዎች ባለመኖራቸው በመስኩ እየታየ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት አካዳሚያዊ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ይኸውም በሙያ መስኩ ውስጥ ያሉ አንባቢያን በጥናቱ ውስጥ የቀረቡትን ትንተናዎች ተመልክተው ልቦለዳዊ ስራዎች ውስጥ እንዴት ስነልቦናዊ እሳቤዎች እንደለመዱባቸው ሀሳቦችን ያገኛሉ፤ መሰል የሥነፅሁፍ ጥናት መስክ ላይ ተጨማሪ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ የመስኩ ተመራማሪዎች ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ እንዲመረምሩ፣ የአማርኛ ሥነፅሁፍን ንባብ የሚያሳድግና በዚሁ መንገድ ሌሎች ልቦለዳዊ መጽሐፍትን መተንተንም ሆነ ሌሎች ተገቢ ንድፈሀሳቦች በመጠቀም እንዲገመግሙ ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ በመጨረሻም በተመሳሳይ ጥናት ለሚሰሩ የጥናት ርዕስ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በአለማየሁ ገላጋይ ሶስት ስራዎች ማለትም **በፍቅር ሥም፣ታለ በዕውነት ሥም እና ሐሰተኛው በእምነት ሥም** ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡ ጥናቱ ልቦለዶችን ከዩንጊያን እራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤዎች አንጻር ስነልቦናዊ ንባብ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ የሹሜትን የዩንጊያን የራስን ፍለጋ እሳቤው ዋና መገለጫዎችእና ሥረመሰረታዊያን በማቀናጀት የጽሑፍ ትንተና(Text analysis) ማድረግ ነው፡፡

ትንተናውንና ፍከራውን ሲቀርብ በአንድ ዋና ገፀባህሪ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ ገፀባህርይው እንደየ መጻሕፍቱ ወይም መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉ ገፀባህሪያት ሆን ብለውም ይሁን በዘፈቀደ እንደሚጠቀሙበት የሚለያይ ሆኖ መጠሪያው ግን የአንድ ገፀባህርይ መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡ እሱም፡- ታለ ፣ ታለሰው ወይም አላዛር ቢዝን ነው፡፡ ይህም በሶስቱም መጻሕፍት ላይ ዘላቂ ገፀባህርይ መሆኑና ራስን ፍለጋ እሳቤ ለመተንተን ታላሚ ገፀባህርይ በመሆኑ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

የጥናቱ ዘዴ በዋንኛነት የጥናቱ አይነት፣ የጥናቱ አቀራረብ፣የጥናቱ መተንተኛ ስልት፣ጥናቱ የሚከተለውንድፈ ሀሳብ፣ ታላሚ ቴክስቶች አመራረጥና የመረጃ ምንጮችን ያሳያል፡፡

ይህ ጥናት ጽሑፍ ትንተና(Text analysis) ከሚባለው የጥናት አይነት ውስጥ ይመደባል፡፡ የጽሑፍ ትንተና የሚባለው የምርምር ዘዴ በጥቅሉ ሲታይ ፣ አንድን ጽሑፍ ወስዶ ከይዘትም

ይሁን ከቅርጽ አኳያ የሚመለከት ፣ በጽሑፉ ውስጥ የሚያገኛቸውን የተለያዩ ጉዳዮች እያነሳ የሚተነትን ነው። ከሚተያኩርባው በርካታ ነጥቦች መካከል የደራሲውን አብይ ሀሳብ መፈለግ ፣ ጭብጡ የቀረበበትን ቴክኒክና ቋንቋ መመርመር፣የስራውን ዘውግ መለየት ወዘተ. (Hoover 2013: 2-3) የሚሉት ይገኙበታል።

ይህ ጥናት የሚከተለው የጥናት አቀራረብ በይነ-ቴክስታዊ ነው። በይነ-ቴክስታዊ ማለት ከአንድ በላይ በሆኑ ቴክስቶች መካከል ያለውን የፅንሰሀሳብ መዛነቅ፣ የይዘት መዋሃድ እና መሸረብ የሚፈክርበት ስልት ነው።

ለጥናቱ የተመረጡ ሶስት ልቦለዶች በታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ሲሆን ይህም አጥኝው ራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤዎችን በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ይበልጥ ይገኛሉ ብሎ በማሰቡ ነው ። ከዚህም በተጨማሪ በአንዱ ልቦለድ ውስጥ ማሳየት አይቻልም ወይ ለሚለው ሶስቱን መጻሕፍት የተመረጡበት ምክኒያት ይበልጥ ጥናቱን ተጨባጭ ለማድረግ እና እሳቤዎቹን ለማጎልበት በማሰብ ነው።

ጥናቱ ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮችን ተገልግሏል። እነሱም ቀዳማይና ካልዐይ ናቸው። ቀዳማይ የመረጃ መንጮቹ ታላሚ ልቦለዶቹ ሲሆኑ ካልዐይ የመረጃ ምንጮች ያልኳቸው ደግሞ የጥናቱ ቀጥተኛ ተተኳሪ ያልሆኑ ፣ ነገር ግን የጥናቱ ዳር ይወጣ ዘንድ የመረጃ ድጋፍ የሰጡኝን ነው። ሥነጽሑፋዊ ንድፈሀሳቦች በተለይ ከስነልቦና የለመዱ እንደ ማህበረ ልቦናና ፣ ፋካሬ ለቡና፣ሂሶች ፣ ጥናቶች ና መጻሕፍት በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአራት ምዕራፎች ተዋቅሮ ቀርቧል። በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክኒያት፣ ጥናቱ አላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ፋይዳና፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ዘዴናቸው። በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት፣ በምዕራፍ ሶስት ትንተና በመጨረሻም በምዕራፍ አራት የጥናቱ ማጠቃለያ ቀርበዋል።

# *ምዕራፍ ሁለት*

# 2. ክለሳ ደርሳናት

## 2.1 ጽንሰሀሳባዊ ዳሰሳ

በዚህ ጽንሰሀሳባዊ ዳሰሳ ስር *ሥነፅሁፍና* ስነልቦና ምንና ምን ናቸው? ያላቸው ግንኙነት እስከምን ድረስ ነው የሚለው የሚቀርብበት ክፍል ነው፡፡

### 2.1.1 *ሥነፅሁፍና* ስነልቦና

አንድ *ሥነፅሁፋዊ* ስራ በስነልቦናዊ ንድፈሀሳብ ከመተንተናችን በፊት በሁለቱ መካከል ያለውን ዝምድና ወይም የሚያመሳስል ፀባይ በትክክል መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ከላይ ከፍ ብለን እንዳነሳነው የሌሎች የትምህርት መስክ መከሰቻቸው ቋንቋ መሆኑ እና በሌሎች የትምህርት መስክ ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች ስራቸውን ለማስተዋወቅ *ሥነፅሁፍን* መጠቀማቸው እየተለመደ መምጣቱን ተረድተናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በሚገባ የምሁራንን ሀሳብ እያጣቀስን አፍታትተን ለማየት እንሞክር፡፡ የ*ሥነፅሁፍና* የስነልቦና ግንኙነት በተመለከተ ኢምሬ የሚከተለውን ሃሳብ ሰጥቷል፡፡

> *የሰው ልጅ አካልና ነፍስ መካከል ያለው ግንኙነት ከነተቃርኖውና አሻሚነቱ በማጥናት እንደ ሥነፅሁፍ እና ስነልቦና የተሳሰረ ሌላ የሳይንስ ዘርፍ የለም፡፡ በተወሰኑ ህጎች በመጠቀም የሰውን ልጅ ነፍስ እና ከፊል ኢ-ንቁ አካል በረጅምና የዳበረ ጉዞ ምስጢራዊ ጎኑን ለማወቅና ያላቸውን ግንኙነት ለመበየን ጥረት አድርገዋል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ሁለቱም ዘርፎች ለአንድ ክ/ዘመን ያክል እራሳቸውን በአርትና ሳይንስ ህልውናቸውን ለማቆየት ትግል ማድረጋቸው ያመሳስላቸዋል*(ኢምሬ 2006፣III)[1]፡፡

ከላይ ከቀረበው የኢምሬ ሀሳብ እንደምንረዳው *ሥነፅሁፍ* እና ስነልቦና በሰው ልጅ አካል እና ነፍስ ያለውን ግንኙነት ማዕከል አድርገው የሚሰሩ በመሆናቸው ከሌሎች የሳይንስ ዘርፎች በተለየ መቀራብ እድል አግኝተዋል፡፡ ይኸውም ረጅም በሆነ *ሥነፅሁፋዊ* ትረካ የሰዎችን የተዛነቀ ነፍስ ወይም ከፊል ንቁ አዕምሮ ለማወቅ የሁለቱም ግንኙን ከፍተኛ አስተዎፆ ያለው መሆኑ ነው፡፡ በእርግጥም *ሥነፅሁፍ* ይሁን ስነልቦና የሰው ልጅ አካል፣ አዕምሮ እንዲሁም

ከባቢያዊ ግንኙነታቸው የስራዎቻቸው ወይም የጥናታቸው ማዕከል ነው። የኢምሬን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ ካን ሥነፅሁፍን ስነልቦና ያላቸውን ግንኙነት እንደሚከተለው አስረድቷል።

> *ሥነፅሁፍ እና ስነልቦና የሰውን ነፍስ የሚያጠኑ ሁለት የሳይንስ ዘርፎች ናቸው፡፡ ስነልቦና የሰውን ልጅ ባህርይና ምክኒያቶቹን የሚያጠና ሲሆን ሥነፅሁፍ የሰውን ልጅ ባህርይ በልቦለድ አማካኝነት ይገልፃል። እነዚህ ሁለት የማህበራዊ ሳንስ ዘርፎች የሰው ልጅ ባህርይ የሚመጋገቡና የጋራ ጥቅም አላቸው ብለው ያምናሉ*(ኢምሬ 2016፣49)[2]።

ካን ስነልቦና ሰዎችን ባህሪ እና መነሻዎቹን ሚያጠና ሲሆን ሥነፅሁፍ ደግሞ ሰውን ልጅ ባህሪ በልቦለድ የሚገልፅ በመሆኑ እርስ በርሳቸው የሚገናኙ መሆኑን ይገልፃል። ይህ የጥናት መስኮቹ መቀራረብ በቀላሉ አንዱ አንዱን እንዲደግፍ፣ አንዱ በአንዱ ውስጥ እንዲገኝ እንዲጋመድ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ይኖረዋል። ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ከሁለቱም የጥናት መስክ ባህርይ አንፃር የቀረበ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ በስራዎቻቸው ከሚያነሱት ጭብጥ አንፃር ደግሞ ግንኙነታቸው እንደሚከተለው ተገልጧል።*"የሰው ልጆች የጽሁፍ ጭብጥ እስከሆኑ ድረስ የስነልቦና መሰረታዊ ጉዳዮች በሥነፅሁፋዊ ስራዎች ውስጥ ይገኛሉ። የስነልቦና ጽሁፎች ስለ ሥነፅሁፍ ማወቅ ያለብን አብዛኛውን ጉዳዮች ይሸፍናሉ። ምክኒያቱም ሥነፅሁፍ የአዕምሮ ውጤት ስለሆነ ነው"(2016፣50)[3]።*

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ሥነፅሁፋዊ ስራዎች ጭብጥ የሰው ልጅ እንደመሆኑ መጠን ስነልቦናዊ ጉዳዮችን በውስጡ ይኖሩታል። በሌላ በኩል ደግሞ ስነልቦናዊ የፈጠራ ስራዎች ደግሞ ሥነፅሁፍ መያዝ ያለበትን ሁሉ ይይዛል። ለዚህ ምክኒያቱ ደግሞ ስነልቦናዊ ጉዳዮችን ለማስረዳት ፈጠራ የታከለበት የሰውን ገፀባርይ መጠቀምና ከደረቅ ሳይንስነት አውጥቶ እያዋዙ የበለጠ ማስረዳት ተመራጭ በመሆኑ ነው። ይህን ደግሞ በሚከተለው በኢምሬ ሀሳብ ማስረጃነት ማረጋገጥ እንችላለን።

> *በዚህ ወቅት ደስተቭስኪ ለስነልቦና ፍፁም አስፈላጊና አንዱ ጠቃሚ ሰው እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። መጽሐፉ በስነልቦና ት/ክፍል ውስጥ እንደ መማሪያና ማጣቀሻ መጽሐፍ ያገለግላል። ነገር ግን በሥነፅሁፍና በሥነፅሁፍ ጥናትም በተመሳሳይ ያገለግላል። ስነልቦናዊ ውሂብ ለደራሲያን እና ለሥነፅሁፋዊ*

*አጥኚዎች ለሁለቱም ያገለግላል። ለደራሲያን የምናባዊ አለም ገፀባህርይ ሂደት ሲሆን ለሥነፅሁፍ አጥኚዎች ደግሞ ውስጣዊውን አለም ሀልው በሆኑ ሥነፅሁፋዊ ስራዎች ለመመልከት በምናደርገው ጥረት ይጠቅማሉ* (ኢምሬ 2009፣ 325)[4]።

ኢምሬ እንደገለፀው የዶስቶቭስኪ ስራዎች ብቻ ሳይሆን በሃገራችን ኢትዮጵያም ደራሲያን ስነልቦናዊ ጉዳዮችን እና እሳቤዎችን ገፀባህሪያትን በመጠቀም በልቦለድ አማካኝነት ቀለል ባለ አገላለፅ ማስረዳትና አንባቢያን ጋር መገናኘት እየተለመደ መጥቷል። ከእነዚህ መካከል ምህረት ደበበ፣ አለማየሁ ገላጋይ፣አዳም ረታ ወዘተ. ይጠቀሳሉ። ይህ ደግሞ ስነልቦናዊ መልዕክቶችን ከማስተላለፍ ባሻገር ለሥነፅሁፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፆ አብርክቷል። እያበረከተ ይገኛል። ሌላው ሥነፅሁፍ ጥናቶችንና የስነልቡናን ግንኙነት በተመለከተ ሶላክ እንዲህ ብሏል። *"ከሥነፅሁፍ መነሻነት፣ ስነልቦናን ከፀሀፊው፣ ከግጥሙና ከሥነፅሁፋዊ ሥራው መሰረት አድርገን ስንተነትን ተግባራዊ ውሂብ በመስጠት አዲስ እይታ እንዲኖረን ያደርጋል"*(2004,104)[5]።

ሶላክ እንዳለው ከዚህ ጥናት ጋርም የሚቀራኘው እና ተተኳሪው ነጥብ ስነልቡናዊ እሳቤዎችን በተለያዩ ጥንታዊ በሆኑ ሥነፅሁፋዊ ስራዎች፣ ሚቶች ውስጥ ማሳየት፣ መተንተን እና መፈከር በውጭው ዓለም ቆየት ያለና በሀገራችን ኢትዮጵያም እየተለመደ የመጣ የሥነፅሁፍ ጥናት መስክ ሁኗል። የፍሩድና ዩንግ ስነልቦናዊ ንድፈሀሳቦቻቸው ሥነፅሁፍና ሰዋዊ ሀብቶች የበለጠ ቦታ እንዲያገኙና ስነልቦናና ሥነፅሁፍ የበለጠ እንዲዛመዱ ምክንያት ሆኗል።

## 2.2. ንድፈሀሳባዊ ማዕቀፍ

በንድፈሀሳባዊ ማዕቀፍ ስር የጥናታዊ ጽሑፌ ማጠንጠኛ የሆኑ ራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤ ምንነት፣ የራስን ፍለጋ ጽንሰ ሀሳብ እሳቤዎች፣ የራስን ፍለጋ ደረጃዎችና የራስን ፍለጋ ሥረመሰረታዊያን ተዳሰውበታል።

## 2.1.2.. ራስን ፍለጋ

### 2.1.2.1. የራስን ፍለጋ ምንነት

ራስን ፍለጋ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በእንግሊዝኛ "Self search" ወይም "Individuation" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይወስዳል፡፡ ከዚህ አንጻር ራስ የሚለውን መነሻ ቃል ባግባቡ ማየት ግድ ይላል፡፡

በፍሩዲያን /ከሊኒያን/ ፍካሬ ልቡናዊ ባህል አስተሳሰብ ራስ ወይም self የሚገልጸው የኢጎ እድገት ውጤት እደሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዩንግ ራስ ከኢጎ በፊት የሚገኝ ነው ይላል፡፡ ራስ የሚጀመሪያው ሆኖ ኢጎ ከእሱ የሚያድግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ራስ የሚለውን ቃል ብያኔ በአግባቡ ለመረዳት የኢጎን ምንነት በመጠኑ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ስለ ኢጎ ምንነት ከተጻፉ ጽሑፎች መካከል የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> *ኢጎ ምክኒያታዊ የስነ-ልቦና አስተዳደር ውክል ነው፡፡ ነገር ግን ኢጎ የኢድ ህያው ጥንካሬ ይጎለዋል፡፡ ኢጎ የኢድ ተፈጥሮአዊ ግፊት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በምንም አይነት አጥፊ ስርዐት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛው የኢጎ ክፍል ኢ-ንቁ የአዕምሮ ክፍል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኢጎ በተለምዶ በንቁ አዕምሮ የምናስባቸውን ይይዛል*(ኢታል ፤ 157)[6]፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው በፍሩዲያን የፍካሬ ልቡና መሰረት ኢድ(ኢ-ንቁ) የተደበቀውና አደገኛው ወይም ሳይጣናዊው ሀሳባዊው የአምሮ ክፍል ሲሆን "ሱፐር ኢጎ" (ንቁ) ደግሞ መላዕካዊው ሀሳባዊ የአዕምሮ ክፍል ነው፡፡ የኢድ እና የሱፐር ኢጎ ድምር ደግሞ ኢጎን ይሰጣል፡፡ በፍሩዲያን ኢድ የሚባለው ኢ-ንቁ የአምሮ ሀሳባዊ ክፍል በዩንጊያን "ሻዶው" በሚል ፅንሰሃሳብ ተተክቷል፡፡

በራስን ፍለጋ ላይ ምርምር ያደረጉና የጻፉ አብዛኞች ምሁራን ጽንሰ ሀሳቡ ውስብስብ ሂደት እንደሆነ እና ለመግለጽ ከባድ እንደሆነ ይመሰክራሉ፡፡ ከነዚህ መካከል አን እንዲህ በማለት ገልፀዋል፡፡

> *ራስን ፍለጋ የሚለውን ሀሳብ መበየን ቀላል ያልሆነና ውስብስብ ሂደት ነው፡፡ የኔ ግንዛቤ ኒሊ ከተናገረው ጋር ይመሳሰላል፡፡ ኒሊ እንዳለው ባጭሩ ራስን ፍለጋ ማለት ንቁ ለመሆንና አንዳች ነገር ለማወቅ መምረጥ፣ ይህ ማለት ደግሞ*

*በተለይም ሰው ስለመሆን መንቃት ማለት ነው። እኛ በሙሉነት፣ በጥንካሬና በውስንነት የመገኘት ችሎታ አለን* (አን 2014፣13)[7]።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው የራስን ፍለጋ ሂደት ቀላል ያልሆነና ውስብስብ መሆኑን እንደ ሌሎቹ የዩንግ ንድፈ ሀሳባዊያን ታስረዳለች። ነገር ግን በቀላሉ ንቁ (conscious)፣አገናዛቢ መሆንን መምረጥ ጥንካሬያችንና ውስንነታችን በማወቅ ራሳችን መሙላት መቻል ራስን መፈለግ መሆኑን ታስረዳለች።

በሌላ በኩል ፎድሃም ራስን ፍለጋ በተመለከተ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል። *"ግለተፈጥሮ የመፍጠርና በዛ ላይ የመሰልጠን ሂደት… እና… ከአጠቃላይ ቡድናዊ ስነልቦና ለመለየት ግላዊ ስነልቦና የማዳበር ሂደት ነው"(*1969፣1)[8]።

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንረዳው ራስን መፈለግ ከማህበረሰቡ ስነልቦና በመለየት የራስን ስነልቦና መገንባት ግለሰባዊ ተፈጥሮ የመቅረጽና እና በዛ ላይ የመሰልጠን ሂደት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ሌላው ስለ ራስን ፍለጋ/ ኢንዲቪዲዮሽን/ ጠንከር ያለ ብያኔ የሰጠው ሹሜት ሲሆን ከዩንግ እና ዩንጊያን አስተምሮ አንጻር ስለ ራስን ፍለጋ የሚከተለውን ሃስብ ጽፏል።

> *ዩንግ እንደተመለከተው ራስን ፍለጋ ራስን የማብቃት ሂደት ሲሆን የህይወት ጥቅምና ትርጉም መለማመድና ማሰስ፣ ይህም ማለት አንድ ሰው ራሱን ሲፈልግ እና ራሱን መሆን ሲችል ማለት ነው። ይህም በተቃርኖ ውህደት የተመሰረተ ይናል። ምሳሌ ንቁ እና ኢ-ንቁ ፣ ግለሰብ እና ቡድን፣ ልቡና እና ሶማ ፣ ፈጣሪና ሰው፣ ህይወት እና ሞት ይሆናል*(ሹሜት 2005፣597)[9]።

ከቀረበው ብያኔ እንደምንረዳው ራስን ፍለጋ የራስን የማብቃት ሂደት እንደሆነ፣ በህይወት የመኖርን ፍችና ጥቅም መለማመድ ና መፈለግ እንደሆነ ይገልጻል። አንድ ሰው ራሱን የሚፈልግበትና በትክክል ማን እንደሆነ የሚያረጋግጥበት መንገድ እንደሆነ አትቷል። ይህም ተቃርኖዎች በመመጋገብ የሚገነቡት እንጂ ንቁ የሆነውና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ቀኝ ተብሎ የሚታሰበው ብቻ ሳይሆን ኢ-ንቁ የአዕምሯችን ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሁሉ ራስን ፍለጋ ለማከናወን አስፈላጊ እንደሆኑ አስረድቷል።

ሌላው ስቲን ስለ ራስን ፍለጋ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው ገልፆታል።

*ራስን ፍለጋ በሁለት ትልቅ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያልፋል። የመጀመሪያው የግለሰቡ አሁን በፊት ከነበሩ ኢ-ንቁ መገለጫዎች መለየት(መተንተን እና ንቁ መሆን ) በአዲስ የተለየ ምስልና የልቡና ይዘት መለወጥን ይጠይቃል። ይህ እንቅስቃሴ የንቁነት ምስል የመፍጠር ተፅዕኖ አለው። ሁለተኛው ግለሰቡ በትንተና መሸጋሪያ ከፈጠረ በኋላ ራስን ፍለጋ ለአስቸኳይ ጊዜ ህይወት ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ እና ዘላቂ የሆነ ክትትል ማድረግ አለበት*(ስቲን 2005፣2)[10]።

ከላይ ከስቲን ሀሳብ እንደምንረዳው ራስን ፍለጋ በሁለት ዋና እንቅስቃሴዎች የሚያልፍ ሲሆን መጀመሪያው ራሱን በመመርመር ከኢ-ንቁ ወደ ንቁ ሁነት የሚመጣበትና ተጨማሪ አዲስ ምስልና የስነልቦና ይዘት የሚያገኝበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥንቃቄ ቀጣይነት ያለው ትኩረት በመስጠት ራስ እንደሚገኝ ያትታል። ሁለተኛው ደረጃ ግን በጥንቃቄ እና ቀጣይነት ባለው መንገድ ካልተተገበረ ላይሳካ የሚችል ከተተገበረ ግን ደግሞ ራስን ፍለጋ የሚፈጥር መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህ የስቲን ሀሳብ ከዩንግ ሁለት አጋማሽ ህይወት ጋር የተቀራረበ ብያኔ መሆኑ ልብ ይለዋል። ከዚህ በተጨማሪ የራስን ፍለጋ አስፈላጊነት ስቲን እንደሚከተለው ገልጾታል፡-

*የራስን ፍለጋ መርህ ሰው የመሆን መሰረት እንደሆነ ይተረጎማል። ሰዎች እራሳቸውን ከአካባያቸው እንዲለዩ እጅግ መሰረታዊ ነገር ነው። ይህ ለግለሰቦች መንቃት አስፈላጊው ተፈጥሮ ነው። ራስን ለመሆን መዳረሻ የመፍጠርና መለየት ያስፈልጋል። ስለዚህ ራስን መፈለግ ከሰው ተፈጥሮ ጋር መስማማት ማለት ነው*(ስቲን 2005፣3)[11]።

በአጠቃላይ ራስን ፍለጋ ደረጃዎች ታልፈው ከተሳካ ለሰው ልጆች ጠቃሚ እንደሆነ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም። ይህም ሰዎች የሰው ልጆች መነሻና መዳረሻቸውን እንዲያውቁ፣ ከየት መጥነታቸውን እንዲመረምሩ፣ ከተፈጥሮ ጋር እንዲስማሙ፣ ከፍ ወዳለ ስብዕና እንዲሸጋሩ እድል ይፈጥራል።

## 2.1.2.2 የራስን ፍለጋ ጽንሰሀሳብ የእሳቤው መገለጫ ባህርያት

በዚህ ክፍል የሚቀርቡ ራስን ፍለጋ ንድፈ ሀሳብ መገለጫ ባህርያት ሲሆኑ የዩንጊያን የራስን ፍለጋ ንድፈሀሳብ ከሌሎች ፍካሬልቡና ንድፈሀሳቦች በትክክል የሚለዩትና ዋና ማጠንጠኛ ናቸው።

እንደ ሹሜት የራስን ፍለጋ እሳቤዋና መገለጫ ባህርያት 8 ናቸው። እነሱም Collective and persona፣Two halves of life፣Relationship፣**State or process**፣The prevalence of individuation፣Anti- Individuation፣Self and ego፣Self and God ናቸው። እነዚህን ከዚህ እንደሚከተለው ሹሜትን መነሻ በማድረግ ለማብራራት እሞክራለሁ።

**ሀ.ቡድን እና ግለሰብ(Collective and persona)**

ራስን ፍለጋ በግለሰባዊና በቡድን ውስጥ ያሉ ቅንጣቶች ጥምረት ያስፈልጉታል። ዩንግ ራስን ፍለጋ የቡድን እና የግለሰባዊያን ጥምረትን እንደሚከተለው በአጽንኦት አስረድቷል። *"የራስን ፍለጋ ዓላማ በአንድ በኩል በግለሰቦች ለራስ የተሰጠን ሀሰተኛ ሽፋን በሌላ በኩል ደግሞ ጥንት የነበረውን ምስል በሌሎች በቀረበ ሀሳባዊ እቅድ ሃሳቡና ባህሪውን መለወጥ ከማሰባጠር የተለየ አይደለም"(ዩንግ* ,269)[12]።

ከዩንግ ሀሳብ እንደምንረዳው አንድ ሰው ራሴን ፍለጋ ሂደት ውስጥ ነኝ በሚል ግላዊ ተግባር፣ ጉዳይ እና ክብር አብዝቶ የሚጨነቅ ከሆነ ያለበትን ቡድን መገለጫዎች፣ እሳቤዎች፣ ባህል፣ አይነኬ ጉዳዮች ወዘተ. የመጣስና የመጋጨት እድል ያጋጥመዋል። ይህ ደግሞ ከመነሻው እራስን ፍለጋው እንዳይሳካ እና እንዲጨነግፍ ሊያደርገው ይችላል። በመሆኑም በግለሰብና በቡድን ውስጥ ያሉ ባህሪያትአንዱ አንዱን ሳይጫኑ እንዲመጋገቡ አድርገ ማስኬድ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል። ሹሜት ቡድን እና ግለሰብን በተመለከተ ይህን ሀሳብ ሰጥቷል።

> *አንድ ግለሰብ ለግላዊ ጉዳይ እና ክብር አብዝቶ የሚጨነቅ ከሆነ ካለው ግላዊ ሽፋን ለመውጣት አደጋ ውስጥ ይወድቃል። ለምሳሌ የት/ቤት መምህር ቤት እንደሚተጋ ወይም ተንታኝ በፍፁም መተንተን እንደማያቆመው ማለት ነው። በዚህ አይነት እንደ ጋሪ ፈረስ በተከለለ ህይወት ወይም አጭር እና ለራስ ብቻ የማሰብ ህይወት የቡድን እሴቶችን የሚጋፋ ይሆናል። ይህ ደግሞ ጥልቅ በሆነ*

*ራስን የማምለክ ባይተዋርነት መግባትና በማህበረሰቡ ዘንድ መገለል ያመጣል*(ሹሜት 2005፣595)[13]።

እንደ ሹሜት ገለጻ በግለሰባዊ ጉዳዮች ላይ ካተኮርን ያልተረጋጋ ህይወት መምራት፣ በአጭር እይታና ለራስ ብቻ በሆኑ ግቦች ላይ ማተኮር ፣ የብዙሃኑን እሴቶች መግፋት ይገጥማል። ይህ ደግሞ ራስን ወደ ማምለክ መቃወስ እና መገለል፣ በጥልቅ ራስን ማሰብና በማህበረሰቡ እንድ ቦታ ስም መሰጠት እንደሚገጥም ያስረዳል።

በውስጣዊ አለም መመሰጥ በሂደት በውጫዊ ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነትና በስራ ቦታ ፍላጎት ማጣት ያስከትላል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከማህረሰቡ ጋር ያለን ግንኙነት እየተራራቀ መምጣት በመጨረሻ መለየትና ስም መሰጠትን ያመጣል። በዚህም "የአምሮ በሽተኛ፣ እብድ" ወዘተ. የሚል ስም ተሰጥተውት ራስን እስከ ማጥፋት የሚደርስ ቀውስ ሊገጥም ይችላል። በአጠቃላይ በራስን ፍለጋ ሂደት በማህበረሰቡና ራሱን የሚፈልገው (በምትፈልገው) ግለሰብ መካከል ድንበር የሚቀመጥ ሳይሆን፣ አንዱ ለአንዱ አስተዋጽዎ የሚያደርጉና ለራስን ፍለጋው መሳካት አስተዋጽዎ የሚያደርጉ ናቸው። ይህ ካልሆነ ራስን ፍለጋው ዳር ሳይደርስ ሊጨነግፍ የሚችልበት አጋጣሚ ይፈጠራል።

### ለ.ሁለት አጋማሽ ህይወት(Two halves of life)

ራስን ፍለጋ ሂደት ሁለት ዋና አጋመሽ ህይወት እንዳሉት የዩንግ ንደፈሀሳብ አራማጆች ያምናሉ። ከላይ የራስን ፍለጋ ብያኔ እንደተመለከትነው ስቲን ሁለት አጋማሽ ህይወት በሚያንፀባርቅ መልኩ እንደሚከተለው መግለፁ ይታወሳል። ይኸውም፦

> *ራስን ፍለጋ በሁለት ትልቅ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያልፋል። የመጀመሪያው የግለሰቡ አሁን በፊት ከነበሩ አ-ንቁ መገለጫዎች መለየት (መተንተን እና ንቁ መሆን) በአዲስ የተለየ ምስልና የልቡና ይዘት መለወጥን ይጠይቃል። ይህ እንቅስቃሴ የንቁነት ምስል የመፍጠር ተፅዕኖ አለው። ሁለተኛው ግለሰቡ በትንተና መሸጋሪያ ከፈጠረ በኋላ ራስን ፍለጋ ለአስቸኳይ ጊዜ ህይወት ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ እና ዘላቂ የሆነ ክትትል ማድረግ አለበት*(ስቲን 2005፣2)[14]።

ዩንግ ሆነ ስቲን እንደሚገልፁት ራስን ፍለጋ የሰው ልጆች ካሉት ሁለት አጋማሽ ህይወት ውስጥ ከመጀመሪያ የሚነሳ የሁለተኛው አጋማሽ ህይወታችን እድገት ነው። በመጀመሪያው

አጋማሽ ራስን ከፍ ማድረግ ወይም ኢጎ በመፍጠር ላይ መጨነቅ እና የቡድን ልማዶችን ማልመድ፣ ለምሳሌ ግላዊ ማህበራዊ ክብር መገንባት ላይ የሚያተኩር ነው።

ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ግን ከሞት ጋር ለሚያያዙ ቃላት መጨነቅ ይመጣል። የመኖራችን ትርጉም መፈለግ ፤ በአለም ስንኖር እያንዳንዳችን በተለየ አስተዋጾ ማድረግ እና የመገንባት ጉዳይ ላይ መጨነቅ ሲሆን ይህ ደግሞ ለስርዐተ ነርቭ መቃወስ ዋንኛው ምክንያት ነው።

**ሐ.ግንኙነት**(Relationship)

ዩንግ በራስን ፍለጋ ሂደት ግንኙነት ምን ማለት እንደሆነ የሚከተለውን ሀሳብ ገልጧል። "*ራስን መሆን መዛመድ ነው። ራስን መሆን የሚኖረው አንተ እስካለህ ብቻ ነው። ራስ መሆንን አንተ ትሰረዋለህ እንጂ ሆነህ የምትገኘው አይደለም። ራስ የሚኖረው በምትሰራው ነው፣ ስራ ማለት ደግሞ ግንኙነት ማለት ነው*"(ዩንግ 1935,73)[15]።

ከዩንግ ሀሳብ እንደምንረዳው ራስን መሆን ምክኒያታዊ ነው።ራስን ፍለጋ ከሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ይወሰናል። ግንኙነት በተለይም ደግሞ ራስን ፈላጊው በልጅነት ጊዜው የሚኖረው መስተጋብር በጥሩም ይሁን በመጥፎ ራሱን በሚፈልግበት ወቅት ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በተለይም ደግሞ በመጀመሪያ ከእናቱ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከዛም ከቤተሰቦቹ ጋር ሚኖረው ግንኙነት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ይህ ፅንሰ ሀሳብ ደግሞ በዩንጊያንም ሆነ በፍሩዲያን ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው።

**መ.ሁነት ወይስ ሂደት**(State or process)

ራስን ፍለጋ ሁነት ነው? ወይስ ደግሞ ሂደት ነው? የሚለውን በተመለከተ ሹሜት የሚከተለውን አስፍሯል።

> የሌላው አከራካሪ ነገር ዩንግም ግንዛቤ ውስጥ ያስገባው ራስን ፍለጋ የሚሆን ነው፣ መድረስ የሚቻል ነው ወይስ ሁሌም በሂደት ውስጥ ያለ ነው? ራስን ፈለጋ በጭራሽ የማያልቅ ሂደት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰው ልምዶችን ሊያመነጭ ይችላል፤ የሚሰማውን ፣ በአጭር ጊዜ በዚህ ሁኔታ የሚደረስ ይመስላል*(ሹሜት 2005፣598)*[16]።

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ራስን ፍለጋ መደረስ የሚቻል/ መሆን የሚቻል ነው ወይስ ደግሞ ሁሌም ሂደት ላይ ያለ የማይደረስ ነው ሚለው ፅንሰ ሀሳብ ገና ያለየለት አከራካሪ ጉዳይ መሆኑ ነው። በእርግጥ የሰው ልጆች እልቆ መሳፍርት የሆኑ ከየት መጥነት ጥያቄዎች ያሉት በመሆኑ ራስን ፍለጋ ሂደት መሆኑን አመላካች ይሆናል። ነገር ግን ደግሞ አንድ ሰው በራሱ ሚያስቀምጣቸው የህይወት ጥያቄዎች ቢኖሩትና እነዛን ጥያቄዎች በራስን ፍለጋ ሂደት ውስጥ ገብቶ መልስ ቢያገኝላቸው መደረስ የሚቻል ነው ሚለውን ሊያመላክት ይችላል።

**ሠ.የራስን ፍለጋ መገኛ (The prevalence of individuation)**

ራስን ፍለጋ መገኛ በዋንኛነት ራስን ፍለጋ በሁሉም ዘንድ የሚተገበር ነው ወይስ ደግሞ ለምሁሩ ወይም ለነቃው አካል የተሰጠ ነው የሚለውን ሀሳብ የሚያንፀባርቅ ነው። የራስን ፍለጋ መገኛ በተመለከተ ዩንግ እንደሚከተለው ሀሳብ ሰጥቷል።*"ይህን የሚለምዱት አስልች በሆነው መንገድ የሚያልፉ ብቻ ናቸው። ነገር ግን... ግለሰባዊ አ-ንቁ ክፍለአካላቸውን በተመለከተ ለሚመጡ ሁሉ አስፈላጊ ጉዳያቸው ነው"*(ዩንግ 1954,430)[17]። ዩንግ ራስን ፍለጋ ስለ ኢ-ንቁ አዕምሮው ምንነት ለመመርመር፣ ለማወቅ ለሚጨነቅ ማንኛም ሰው የሚያልፍበት ሲሆን ይህ ሂደት ግን አሰልቺና አስቸጋሪ በመሆኑ ይህ ሂደት ለመጋፈጥ በቆረጡ ግለሰቦች የሚከናወን እንደሆነ ያስረግጣል። ሹሜት የዩንግን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ እንደሚከተለው ያስረዳል፡-

> *ራስን ፍለጋ በጣም የተሰራጨ ነው? ሁሉም ቦታ የሚገኝ አለማቀፋዊ ነው ወይስ ለምሁር የተሰጠ ነው። ዩንግ ራስን ፍለጋ ኢ-ንቁ ተፈጥሮአዊ ቀጣይነት ያለው ሂደት ይላል፣ ነገር ግን ጥቂት የሆነ ነገር ነው ይላል። ራስን ፍለጋ የኢጎ እድገትን ይፈልጋል። ነገር ግን ተመሳሳይ አይደሉም። ራስን ፍለጋ ለራስ ያለን ከፍ ያለ አመለካት ተፅዕኖን መግደል ይጠይቃል(ሹሜት 2005፣599)[18]።*

ከዩንግም ሆነ ከሹሜት ሀሳብ የምንረዳው ራስን መፈለግ ስለ ኢ-ንቁ አዕምሮው ለሚያስብ ሁሉ ክፍት የሆነ ነገር ግን ደግሞ ይህን አሰልቺ እና አስቸጋሪ የሆነ ጉዞ ለሚለማዱ ጥቂት ሰዎች የተተወ እንደሆነ ያስረዳሉ። በመሆኑም ራስን ፍለጋ በመጀመሪያ የኢጎ ማደግ የሚጠይቅ፣ ሲቀጥል ይን የተፈጠረ ኢጎ ማስገዛት የሚያስችል የአምሮ ውቅር የሚጠይቅ እንደሆነ መረዳት ይገባል።

### ረ. ፀረ-ራስን ፍለጋ (Anti- Individuation)

ይህ ራስን ፍለጋ በአግባቡ እንዳይከናወን እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዩች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ፀረ ራስን ፍለጋ በተመለከተ ሹሜት እንደሚከተለው ሀሳቡን ገልፃል፡፡

> *ኢ- ንቁ አዕምሮ / unconscious/ የራስ ዋንኛ አካል የሆነውን አሰራር ለመረዳት ኢጎ በተገቢው መንገድ ጠንካራ መሆን አለበት፡፡ የኢጎ ጥንካሬ ደግሞ ውጤታማ እናትና ልጅ እንደሚፈጥሩት፣ ፍርሃትን መቆጣጠር፣ አይሳኔ ፈንጠዝያን ለማስወገድ፣ ውክል ለመፍጠር፣ ለመመስረት፣ ማዘን እና ቁሶችን የመጠገን ግንኙነት የተቀላጠፈ አካባቢ እንዴት ይፈጥራሉ ሚለውን ይወስናል፡፡ የራስን መፈጠር ኢጎቸውን በተሳካ ሁኔታ መቆጣጠር የማይችሉ ሰዎች ውስጥ ልንሆን እንችላን፡፡ በዚህ ጊዜ ራስን ፍለጋ ሊጨነግፍና ባለበት ሊቆም የችላል፡፡ አካባቢያዊና ሰዋዊ ህግ እጥረት ሲያጋጥም የመጀመሪያው ራስበውስጣዊና በውጫዊ ጥቃት ውስጥ ይወድቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ከፀረ-ራስን ፍለጋ ሀይል ጋር እንጋፈጣለን(ሹሜት 2005፣600-601)[19]፡፡*

ከሹሜት ሀሳብ እንደምንረዳው ራስን ፍለጋ ሊጨነግፍ የሚችል ሁነት ወይም ሂደት መሆኑን አብራርቷል፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክኒያቱ በመጀመሪያው አጋማሽ የራስን ፍለጋ ህይወት የተፈጠረውን ኢጎ በሁለተኛው አጋማሽ ህይወት በአግባቡ መቆጣጠር አለመቻል ራስን ፍለጋውን አጥፊ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህ ፀረ-ራስን ፍለጋ ደግሞ እስከ ሞት ሊያደርስ ይችላል፡፡

### ሰ.ራስ እና ኢጎ(Self and ego)

ሰልፍ በትክክል እኔ ማን ነኝ? ወይም እኛ ማን ነን? በሚል ሊተረጎም ይችላል፡፡ ራስ በፍሩዳዊያንም ይሁን በዩንጊያን ወሳኝ ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ልዩነቱ ግን በዩንጊያን ንድፈሀሳብ መሰረት ራስ ከኢጎ ቀድሞ የሚመጣ ሲሆን በፍሩዲያን ንድፈሀሳብ ግን ራስ የኢድ እና የሱፐር ኢጎ ድምር ውጤት መሆኑን ከላይ ከፍ ብለን ተመልክተናል፡፡ ሹሜት ስለራስ እና ኢጎ እንደሚከተለው አስረድቷል፡፡

> *ራስ ንቁ ለመሆን ረጅም ፍለጋ ማድረግ ሲሆን የኢጎን ንረት በቁጥጥር ስር ማድረግ የሚፈልግ ነው፡፡ ኢጎ ራስን የማምለክ ጤነኛ ያልሆነ ከንቱ ስሜት*

*ማጥፋት ውስጥ ከሆነ ራስ ይባላል። ቢሆንም ኢጎ ገለፃን ማፋጠን ካልቻለ ራስ ቁጥና አጥፊ የሆነ ልምምድ ሊኖረው ይችላል። የዚሀ ውጤት ደግሞ የራስን ፍለጋ ቀውስ በተንታኙና በበሽተኛውም ላይ ይዞ ሊመጣ ይችላል*( ሹሜት 2005፣601)[20]።

ራስ ለመፈለግ በምንፈልግ ጊዜ የኢጎ ከፍታን መቆጣጠር መቻል ያስፈልጋል። ቢሆንም ኢጎ ገለጻን ማፋጠን የማይችል ከሆነ ራስ ሀይለኛና አፍራሽ ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ ውጤቱ የራስን ፍለጋ ውድቀት ያመጣል። ስለዚህ በራስን ፍለጋ ሂደት ራስና ኢጎ ተመጋጋቢ እና አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። ምክኒያቱም የኢጎ ማደግ ራሳችን ለመፈለግ ለሚደረግ ጥረት እድገት ወሳኝ ሲሆን አለማደግ ደግሞ በራስ መተማመን እንዲወርድና በራስ ፍለጋ ሂደት እንዳንገባና ከገባንምራሳችን እንድንኮንን አጥፊ ሂደት እንዲኖረን ያደርጋል። በሌላ በኩል ያደገው ኢጎ ከመጠን በላይ ተለጥጦ ራስ ወዳድና ለክብሩ ብቻ የሚጨነቅ ግለሰብ እንዳያደርገን ለራስ ማስገዛት አስፈላጊ ነው።

### ሽ. ራስና ፈጣሪ(Self and God)

ራስ እና ፈጣሪ ያላቸው ግንኙነት በተመለከተ ወይም ራስን ፈጣሪን በምን መነፀር ወይም ምስል ይመለከተዋል የሚል ሀሳብ የሚንፀባረቅበት ነው። ዩንግ ስለ ራስና ፈጣሪ ግንኑነት እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> *ስነልቦና… ዲበቁሳካላዊ መግለጫ ለመስጠት በሚያስችል ቦታ ላይ አይገኝም። ስነልቦና መፍጠር የቻለው ግን የልቦና ምሉዕነት የሚፈጥረው ምስል ከፈጣሪ ምስል ጋር መግጠም መቻሉ ብቻ ነው፤ ነገር ግን የፈጣሪ ምስል ራሱ ፈጣሪ መሆኑን ወይም ራስ የፈጣሪን ቦታ መተካቱን ማረጋገጥ አልቻለም። (ዩንግ 1951፣308)[21]።*

ከዩንግ ሀሳብ የምንረዳው ስነልቦና ዲበቁሳዊነትን ማረጋገጥ የቻለበት ቦታ ላይ አለመሆኑን እና ልቡናችን የፈጣሪን ምስል ቢፈጥርምየፈጠርነው ምስል ትክክለኛው ፈጣሪ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳልቻለ ያትታል። ይህ ሲባል ግን ራስ ደግሞ የፈጣሪን ምስል መተካቱን እርግጠኛ መሆን አልተቻለም። ሹሜትም የዩንግን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ ስለ ራስ እና ፈጣሪ ዩንግን ሀሳብ በማብራራትየሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል።

*ዩንግራስን ትልቅ የሆነ ስብዕና ይለዋል፡፡ እስከመጨረሻው የማይታወቅ ፣ አለማቀፋዊ ፈለካዊ መለኪያ ጋር የሚያያዝ፣በሚደንቅ ሁኔታ ራስን መሆን የፈጣሪ ምስል በእኛ ውስጥ ከመሆን ጋር ያዝምደዋል፡፡ ከዚህ በላይ ሲገልጸው፣ ራስን ማብቃት (self realization) በሀይማኖታዊ ወይም ዲበቁስ አካላዊ አገላለጽ እንደምናየው ፈጣሪን እንደ ሰው ስጋ የለበሰ አድርጎ ይቆጥራል፡፡ ዩንግ ፈጣሪን ፣ በስነ ልቦናዊ አገላለጽ በመጀመሪያ በልቦናችን ውስጥ ያለ ነገር ፣ በታሪክ የመጣውን ከፍ ያለ የፈጣሪ ምስል የሚያስተጋባ እንደሆነ ይገልጻል*(ሹሜት 2005፣603)[22]፡፡

### 2.1.2.3 **የራስን ፍለጋ ደረጃዎች** (stages of individuations)

ዩንግ የራስን ፍለጋ በሁለት ዋና የልቡና እንቅስቃሴ ይከፍላቸዋል፡፡ እነሱም የመጀመሪያውና የሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ናቸው፡፡ ነገር ግን ደረጃዎቹ ሁልጊዜ ፊትና ኋላ ብቻ ሳይሆን ጎንዮሽ ሊሆኑም ይችላሉ ፡፡ እያንዳንዱ ደረጃዎች የአድገት ጥያቄ፣ ቅደም ተከተል እና ምስቅልቅሎሽ አላቸው፡፡

ዩንግ እንደሚለው የመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት ትኩረቱ ኢጎ መፍጠር እና የውጭውን አለም በቁጥጥር ስር ማዋል ላይ ሲሆን ይህ ደግሞ ለራስን ፍለጋ አድል ይፈጥርና ወደ ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት እንድንሸጋገር ይረዳል፡፡ በሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ኢጎን በማስወገድ የህይወትን ታላቅ ትርጉም መፈለግ ላይ እናተኩራለን፡፡

ኒዩማን የጁንግ ተማሪ ሲሆን የራሰን ፍለጋ ደረጃዎችን ከዩንግ በማይጣረስ ነገር ግን በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት ላይ በመጨመር እንደሚከተለው በሶስት ከፍሏቸዋል፡፡

ሀ/ የእቅፈት/እንክብካቤ ደረጃ ፣ እናታዊ ደረጃ በመባል ይጠራል፡፡.

ለ/ የማልመድ/ የማስማማት ፣ አባታዊ ደረጃ በመባል ይታወቃል፡፡ እና

ሐ/ የማማከል /የማዋሃድ፣ ግለሰባዊ ደረጃ (ዩንግ 1954)[23]

ከላይ ስለተጠቀሱት ሶስቱ ደረጃዎች ራሳቸውን ችለው የቆሙ እንዳልሆኑና ይልቁንም በሰዎች የህይወት ጉዞ ውስጥ አንዱ በአንዱ ላይ የሚያድግና የማይነጣጠሉ መሆናቸውን በማስረዳት ስቲን የሚከተለውን ብሏል፡፡

*እነዚህ ሶስት ደረጃዎች ፍፁም የተለያዩ ሀሳቦች አይደሉም። ይልቁንም እነዚህ ደረጃዎች አንዱ በአንዱ ላይ እያደጉና እየዳበሩ የሚሄዱ በሰው ልጅ ዋና የህይወት ጉዞ ዘመን የሚያሳዩ የቀደሙ አመለካከቶች ናቸው። የእያንዳንዱ ደረጃዎች መገለጫ ከአንዱ ወደ አንዱ ዝቅተኛ የቀደመ ተፅዕኖ ባለው መንገድ የሚቀጥል እና በግለሰቡ የህይወት ዘመን ሊከሰት የሚችል ነው። አንድ ሰው ወደ እነዚህ ደረጃዎች ለተወሰነ ጊዜ ሊገባ አይችልም፤ በመጀመሪያው ደረጃ ካለፈ በኋላ ወደ ቀጣይ ደረጃ በሚሸጋገርበት ጊዜ ይህን ወደኋላ ትቶት ይሄዳል*(ስቲን 2013፣4)[24]።

## 2.1.2.4 የራስን ፍለጋ ሥረመሰረታዊያን

የራስን ፍለጋ ወይም ኢንዲቪዲዮሽን ሂደት የሚረዱ 5 ዋና ሥረመሰረታዊያን ያሉ ሲሆን እነሱም ፐርሶና(persona)፣ ሻዶው(shadow)፣ አኒማ እና አንመስ (anima and animus) ማና(manna) እና ራስ(self) ናቸው።

### ሀ. ፐርሶና(Persona)

ፐርሶና በጁንግ አናላይቲካል ሳይኮሎጅ ውስጥ የሚገኝ አንዱ ሥረመሰረታዊያን ወይም አርኪታይፐ ነው። ፐርሶና ጀግና(hero/heroine) የሚል ተመሳሳይ ፍች ሊሰጠው ይችላል። ካዝሜንት ስለ ፐሮሶና እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> *ፐርሶና የሚወክለው አንድ ሰው ከውጭው አለም ጋር በሚኖረው ግንኙነት የሚኖረው እይታ ነው። "ማስክ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን የሚወክለው በግሪክ ትዕይንቶች ማስክ የደረጉ ተዋንያኖች አስቂኝም/ አሳዛኝም ክፍል መተወናቸውን ነው። አነስተኛ ተቀባይነት ያለው ስብዕና በፐርሶና ተሸፍኖ ይቆያል። በደንብ የተለየ ፐርሶና በደንብ የሚገጥም ፐርሶና ያሳድጋል። ይህ ደግሞ ለህልውና አስፈላጊ ነው*(ካዝሜት 2001፣142)[25]።

ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ እንደምንረዳው"ፐርሶና" ግለሰቡ ከውጭው ዓለም ወይም ከሰዎች ጋር በሚኖራቸው ግኝኙነት የተሻለ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚጠቀሙትን ጭንብል ነው። በተለያዩ የፊልም፣ የመድረክ ስራዎች ውስጥ ሰዎች የሚፈልጉት ገፀባህርይ ለመላበስ የራሳቸው አካላዊ ባህርይ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ጭንብል ያደርጋሉ። ያ ማለት ብዙም ተቀባይነት የሌለው

አካላዊ ባህርይ በጭንብሉ ይደበቅና ተፈላጊው ገፀ ባህርይ በጭንብሉ አማካኝነት እንዲመጣ ይሆናል፡፡ ጭንብል መጠቀማቸው ደግሞ ለመገለፕ ብቁ ያለሆነ መሸፈን የተፈለገ አካል ወይም ስብዕና እንዳለ በግልፅ ይጠቁማል፡፡

ግለሰቦች ወይም ገፀባህርያት ወይም ተዋንያን ከውጫዊ ዓለም በሚፈጠርባቸው ግንኙነት ጫና ምክንያት ከሁኔታው ጋር ተስማምቶ ለመኖር ያራሳቸው ያልሆነ ጀግንት ይላበሳሉ፡፡ ለመኖር ሲሉ ካሁን በፊት የራሳቸው መገለጫ ያልሆነ ነገር ግን ለሁኔታው ተቀባይነት ያለው ተግባር ይፈፅማሉ፡፡

የካዘሜትን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ አን በፐርሶና ዙሪያ እንደሚከተለው ታብራራለች፡፡

> *በደንብ የሚታወቀው ሥረመሰረታዊ ፐርሶና ነው፡፡ ቃሉን ዩንግ የተጠቀመው ግለሰቦች በህይወታቸው ለአለም መጫወት የሚፈልጉትን ሚና እንዲወክልላቸው ውጭኛው ፊታቸውን እንደሚጠቀሙ ለማመላከት ነው፡፡ ፐርሶና አንድ ሰው የሆነውን ስሜት የሚያሳይ አይደለም፡፡ አንድ ሰው በአለም ላይ ለሌሎች እንዴት ይታያል የሚለውን እና በውጫዊ ተፅዕኖ ፣ ባህል፣ በታሪክ ወስጥ ባለ ጊዜ፣ የህይወት እድገት እና ገጠመኝ የሚገዛ ነው*( አን 2014፣18-19)[26]፡፡

### ሻዶው(Shadow)

ሻዶው ሌላው የዩንግ የራስን ፍለጋ አንዱ ሥረመሰረታዊ ነው፡፡ ዩንግ እንደሚለው ራስን ፍለጋ የሚጀምርበት ምዕራፍ ነው፡፡ ይህ ከፐርሶና እጅጉን የተለየ ነው፡፡ ሻዶው የሰዎችን ጨለማውን ጎን የሚያመላክት ነው፡፡ እንደምናውቀው ጥላ(shadow) ጨለማ ወይም ጥቁር ቀለምን ያሳያል፤ ይህም በትክክል የሰዎችን የተደበቀ ማንነት ያመላክታል፡፡ ፎድሃም ስለ ሻዶው ምንነት እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡

> *ሻዶው ኢ-ንቁ ፐርሶና ማለት ነው፡፡ ሻዶው ከሃሳባዊ ማንነታችን እና ከማህበረሰባዊ መለኪያዎቻችን ጋር የማይስማማ ስሜታዊና ያልሰለጠነ ፍላጎት ሁሉ የያዘ፣ ሁላችንም የምናፍርበት፣ ሁላችንም ስለ እኛ ማወቅ የምንፈለገው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጠባብና ከልካይ በሆነ ማህበረሰብ ብዙው የምንኖረው ሻዶው እንዲሆን ያደርጋል*(ፎድሃም ፣244)[27]፡፡

ከላይ በፎድሃም ሀሳብ የምንረዳው ሻዶው ከማህበረሰባዊ እይታዎች ልክ ያልተገራ ወይም ያልሰለጠነ ማንነታችን ነው፡፡ ይህ ማንነታችን ደግሞ ብዙ ጊዜ የምናፍርበት ፣ የማናውቀው እና በማህበረሰቡ መሆን ከምንፈልገው ማንነታችን ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ ኮፐራ ደግሞ ስለ ሻዶው እንደሚከተለው ታብራራለች፡፡

> *ጨለማውን ጎናችን ችላ ማለት ለመራቅ መሞከር የተለመደ ነው፡፡ የማይካደው ሀቅ ግን ከሻዶዎችን መራቅ መሞከር ግን ሀይሉ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ይህን መካድ ለበለጠ ህመም፣ ስቃይ፣ ፀፀት እና በፍቃደኝነት ከስራ ለመልቀቅ የሚመራና የሚዳርግ ነው፡፡ ሃላፊነተ ለመውሰድ የምንፈራ ከሆነ ከንቁ አዕምሯችን ስር ተደብቆ ያለውን ጥበብ ለማውጣት ካልቻልን ሻዶው አፈትልኮ ይወጣል፡፡ ሻዶዎችንን ልንቆጣጠር ሲገባ የሚቆጣጠረን ከሆነ የሻዶውን ተፅዕኖ ሊቀሰቅስ ይችላል*(ኮፐራ 2010፣2)[28]፡፡

የኮፐራ ነጥብ ዋናው ጉዳይ ጨለማውን(የተደበቀውን) ማንነታችንን ወይም ስሜታችንን መገደብ የተለመደ ሲሆን ይህን ስናደርግ ግን ሻዶው ወይም የተደበቀው ማንነታችንን የበለጠ ሀይለኛ የሚያደርግ ነው፡፡ ሻዶው ማንነታችንን መግፋት ለተጨማሪ ስቃይ እና ፀፀት የሚዳርግ ነው፡፡ ይህም በንቁ አምሯችን ውስጥ የሚገኘውን የተደበቀ ጥበብ ሃላፊነት ወስደን ልንጠቀምበትና ልንቆጣጠረው የሚገባ ሲሆን ይህን ማድረግ ማንችል ከሆነ ራሳችን መልሶ የሚቆጣጠረንና የሚጎዳን ይሆናል፡፡

> *ብዙውን ጊዜ ይዞት የሚመጣው ህመም በህይወታችን የነበርንበት ህመም ነው፡፡ የልቡና ስሜታዊ መስተጓጎል በጣም ጠቃሚ ለሆነ ማምለጥ ተንኳሽን ቅድመ ጠቋሚ ነው፡፡ ትክክለኛው የሻዶው ስራ ሰባብሮ የሚጥለን ብቻ ሳይሆን ውስጣችን ያለው እንዲከፈት ፣ ትላንት ያደረግነው ለአሁን እንዲፈስ የሚከፍት ነው*(ማስተርስ 2010፣44-45)[29]፡፡

የማስተር ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ የኮፐራን ሃሰብ የሚያጠናክር ሲሆን የሚያመጣው ስቃይ በህይወት ዘመናችን የሚሰማንና ስነልቦናዊና ስሜታዊ ጉዳት እንደሚያመጣና ውስጣችንን ብቻ ሳይሆን የሚታየውን ውጫዊ ሁኔታችንም እንደሚጎዳ ያስረዳሉ፡፡

### አኒማ እና አኒመስ (Anima and Animus)

"Anima" and "Animus" በራስፍን ፍለጋ ሂደት ውስጥ ሁለተኛው ደረጃ እንደሆነ ዩንግ ያምናል፡፡ በላቲን ቋንቋ በ"-a" ድህረ ቅጥያ የሚያልቅ ሴትነት / አንዕስት ፆታን/ የሚያመላክት ሲሆን ድህረ ቅጥያ "- us " ደግሞ ወንድ ተባዕት ፆታን ያመላታል፡፡ በመሆኑም " Anima" በወንዶች ውስጥ የሚገኝ የሴቶች ነፍስ ሲሆን በሌላ በኩል "Animus" ደግሞ በሴቶች ውስጥ የወንዶች ነፍስ ነው፡፡

በማህበረሰቡ "ወንድ" እና "ሴት" ብለው የሚከፍሉበት መለያ መንገድ አለ፡፡ በዚህም ወንድ ማለት ውሳኔ ሰጭ፣ ደፋር፣ ተከራካሪ፣ ጠንካራ ሰራተኛ፣ሀላፊነት የሚሰማው ወዘተ. ሲሆን ሴት ደግሞ ቁጥብ፣ ታጋሽ፣ ይቅርታ የምታደርግ ፣ ለስላሳ ወዘተ.

በመሆኑም ይህ ሥረመሰረታዊ እንደሚነግረን ወንዶች የሴቶችን፣ ሴቶች ደግሞ የወንዶች መለያ አላቸው፡፡ "Anima" and "Animus" ሁልጊዜም የሚገኘው በሀሳብ ነው፡፡ አንዳንዴ በስርዐተ ፆታ ምልክቶች ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ሴቶችን በመሬት፣ በዋሻ ወዘተ. ወንዶችን ደግሞ በአንበሳ፣ በወንድ ብልት እና በቆመ ሀውልት ወዘተ. ሲወከል ይቻላል፡፡

### ሰልፍ(self)

ዩንግ እንደሚለው ሰልፍ በሰዎች ኢ-ንቁ አዕምሮ ውስጥ ጥልቁ እና ማዕከላዊ ክፍል ሲሆን ራስን ፍለጋ ሂደት በትክክል እንዲጓዝ ሚያደርግ ነው፡፡ *"ራስ የልቦና ማዕከል እና ምሉዕነት ነው፡፡ የስነልቦናም አጠቃላይ ፅንሰሀሳብ ነው የሚል ጠንካራ መከራከሪያም አለ፡፡ ራስ የራስን ፍለጋ ሂደትን ጥረት ግብ ነው*( ዩንግ ፣2006)[30]፡፡"

ራስ በትክክል እኔ ማን ነኝ? ወይም እኛ ማን ነን? በሚል ሊተረጎም ይችላል፡፡ ሰዎች ጤናማ ማንነት እንዲኖራቸው ሰልፍ ንቁ የአዕምሮ ክፍል እንደሆነ ማወቅ አለባቸው፡፡ ራስ የሚፈጠረው በጣም ውስብስብ በሆነ ጥምር ኢ-ንቁ አዕምሮ ነው፡፡ ሰዎች ማንኛውም ሰው፣ ቦታ፣ነገር እንዲሁም ራሳቸው እንኳን ቋሚ አለመሆናቸውን ሲረዱ የአለም ተለዋዋጭ ባህሪ አይሸውዳቸውም፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ የክለሳ ድርሳናት ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር በይበልጥ ተዛማጅነት ያላቸው 3 የኤም.ኤ. ድግሪ መሚያ ጥናቶች፣ እንዲሁም አንድ የዲክትሬት ድግሪ ማሚያ ጥናት ተዳሰው ቀርበውበታል። ሶስቱ የኤም.ኤ መመረቂያ ጽሑፎች ስነልቡናዊ እሳቤዎች ላይ የተሰሩ በመሆናቸው ከጥናቱ ጋር ስለሚዘመዱ የቀረቡ ናቸው። ሌላው 1 የዶክትሬት ማሚያ ጥናት ግን ከቀረቡት ተዛማጅ ጥናቶች ውስጥ ለእኔ ጥናት ይበልጥ የሚቀርበው ጥናት ሆኖ በመገኘቱ ተዳሷል።

*ቴዎድሮስ አለበል" ልጅት **በማህሌት አልንጋና ምስር**፤ስነልቡናዊ ንባብ"2006 ዓ.ም። ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ. ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት ነው።*

የቴዎድሮስ ጥናት ዋና አላማ "አዳም **በማህሌትና አለንጋና ምስር**" ልጅነትን በእንደምን አይነት ስነልቡናዊ እሳቤዎች ፣ በተለይም ስብዕና ፣ አንደሳለ በይነ ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ መተርጎም ነው። በጥናቱ ዘዴ ስር የጥናቱ አቀራረብ " በይነ ቴክስታዊ" ፣ የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ ፍካሬ መሆኑን አስቀምጧል። በትንተናው ላይ ታላሚ ልቦለዶችን ምዕራፍ ሁለት ላይ በገለፃቸውን የልጅት ስነልቦና ንደፈሀሳቦች አንፃር ተንትኖ አስቀምጧል። **ከአለንጋን ምስር** ከተመረጡ ታሪኮች ውስጥ "ልጅነት" የ"ደመነፍሳዊ" ማንነቶችና የማህበረ ባህላዊ ስርዐቶች መጎራበቻ ሆኗል።"ዘላን"ን ለመፈተሽ "ልጅት ማህበረ ባህላዊ ፍንገጣ እና የ sadistic displacemenet ማደሪያ"እና "ዘላን ፤ የጨቅላነት ግንትሮሽና የሁለት ስብዕናዎች መቃየጥ " የሚሉ ርዕሶች ተበጅተው ተተንትነዋል። አጥኝው በማጠቃለያው አዳም በታለሚ ቴክስቶቹ ስነልቦናዊ ንድፈሀሳቦችን እያለመደ እንደሚጽፍ፣ እነዚህን ፅንሰሀሳቦች ለማልመድ ባህላዊና ሚታዊ አስተማስሎዎችን እንደ ኪናዊ " ተውህቦ" ማላቂያ እንደሚጠቀም፣ የሚመስላቸው ገፀ ልጆች የኢሪክሰንን " ማህበረ ልቡናና " የፍሮይድን " ሳይኮ ሴክሿል" የእድገት ደረጃዎች በ" አፍራሽ " ጎኑ የሚያጠናቅቁ እንደሆኑ ገልጧል።

የቴወድሮስ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው አጠናን ዘዴያችን ማለትም የጥናቱ አቀራረብ በይነ-ቴክስታዊ፣ የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ ፍካሬ መሆኑ እንዲሁም ስነልቦናዊ እሳቤን በልቦለድ ውስጥ ማልመዱ ሲሆን የእኔና የቴወድሮስ ጥናት የሚለያየው ደግሞ በስነልቦናዊ ንድፈሀሳቡ አንጻር እሱ "የኢሪክሰንን ማህረ ልቡናዊ የፍሮይድን ሳይኮ ሴክሽን" መሰረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን እኔ ደግሞ የዩንግን የራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ ንድፈሀሳብ ላይ አተኩሬ

እሰራለሁ። በሌላ በኩል በመረጥናቸው ልቦለዶች ልዩነት ያለን ሲሆን እሱ በአዳም እረታ ስራዎች ላይ ሲሆን እኔ ደግሞ በአለማየሁ ገላጋይ ስራዎች ላይ ነው።

*አሸናፊ መለሰ። አተኩሮ በብርሃን ፈለጎች ውስጥ። 2007 ዓ.ም። ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ስነጽሑፍ ፎክሎር ትምህረት ክፍል ለአርስት ማስትሬት ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው።*

አሸናፊ መለሰ ጥናት ዋና አላማ የብርሃን ፈለጎች ውስጥ አተኩሮ በምን መልክ እንደታየና ለምን አገልግሎት እንደዋለ ማሳየት ነው። የጥናቱ ዘዴ የስነ ተረክ ንድፈሃሳብ አንድ ክፋይ የሆነው አተኩሮ(Focalization) መሰረት በማድረግ ለምርምር በመረጠው ድርሰት ላይ የቴክስት ትንተና የሚካሄድ ነው። በአተኩሮ የትችት አንጻር ስርም የአተኩሮ ገጽታዎች ማለትም ግንዛቤያዊ ገጽታ፣ ስነልቡናዊ ገጽታና ርዕዮተአለማዊ ገጽታዎችን ለትንታኔ ማስኬጅያነት ተገልግሏል። በትንታኔው የግንዛቤ ገጽታ፣ ሥነልቡናዊ ገጽታ ፣ ርዕዮተአለማዊ ገጽታ በሚሉ ዋና ዋና ርዕሶች በምዕራፍ ሁለት ንድፈሀሳባዊ ዳራ ለገለጻቸው ሀሳቦች ጋር እያገናኘ በብርሃን ፈለጎች መጽሐፍ ውስጥ አስረጅ ምሳሌዎችን በመውሰድ አሳይቷል።

አሸናፊ በማጠቃለያው በቴክስቱ ውስጥ የሚገኙ ማስረጃዎች በዋናነት በተረኩ ውስጥ ዋና ገጸባህርይ በሆነው መክብብ የእይታ አንጻር በኩል የቀረቡ እንደሆኑ ፤ የቴክስቱ አተኳሪ አንድ ብቻ በመሆኑ የአተኩሮው ጽናት ቋሚ እንደሆነ ገልጧል። በሌላ በኩል በተረኩ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎች በዚሁ በተረኩ ተሳታፊ ከሆነና ሁኔታዎች ፣ ድርጊቶችና ኑረቶች በቀጥታ ከሚመለከቱት ገፀባህርይ አንጻር ብቻ የቀረቡ መሆናቸው የአተኩሮው አይነት ውስጣዊ አተኩሮ እንዲባል እንደሚያደርግ ገልጧል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ በቴክስቱ ውስጥ ሶስት ዋና ዋና የአተኩሮ ገጽታዎች የተረኩን የመረጃ ፍሰት ለማቀላጠፍ እንደዋሉ ለማሳየት እንደሞከረ አትቷል። በዚህም በግንዛቤያዊ ገጽታው ፣ ገጸባህርይ አተኳሪው በጊዜና በቦታ የተገደበ በመሆኑ ከእይታ አጽናፍ ውጭ ስላለው አለም በስሚ ስሚና በግምት ከሚሰጠው መረጃ ውጭ የማግኘት እድሉን አጥብቦ እንደሚተርክ ፤ በስነልቦና ገጽታው አንድም በአዕምሮአዊ፣ አንድም በስሜታዊ አካላት መገልገያነት አተኩሮው የተሟላ እይታን እደሚፈጥር መደረጉ፤ በርዕዮተአለማዊ ገጽታው ደግሞ አንዳንድ ጉዳይ ደጋግሞ በማንሳት በድግግሙም አንዳች ርዕዮትን አጽንቶ በመትከል ፣ በነባሩ እውነታ ላይ በሚደረግ ፍተሻ አማካኝነት ተረኩ እንደታዩ ገልጧል።

ጥናቱ በታላሚ ልቦለዱ ውስጥ አተኩሮና የአተኩሮ ገጽታዎች ማለት ምግንዛቤያዊ ገጽታ፣ ስነልቡናዊ ገጽታና ርዕዮተ አለማዊ ገጽታዎችን ተንትኖ ማሳየት መቻሉ ጠንከራ ጎኑ ሲሆን የጥናቱ ዋን አለማ ቴክኒክ ማሳየት ሆኖ እያለ በትንታኔው ግን የይዘት ትንተና በብዛት መቅረቡ፣ የጥናቱ አለማና የምርምር ጥያቄዎች በትይዩ ባለመቅረባቸው ምክኒያት በትንታኔው ሆነ በማጠቃለያው የጥናቱ አላማ ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ መስራቱ ጥናቱ ያረጋና የሚዋልል መሆኑ የጥናቱ ድክመቱ ነው፡፡

የአሸናፊና የእኔ ጥናት የሚያመሳስለው በአንድ ደራሲ ስራዎች ላይ ስነልቦናዊ ርዕሰ ጉዳይ አንስተን የቴክስት ትንተና መስጠታችን ነው፡፡ የአሸናፊና የእኔ ጥናት የሚለያይበት ደግሞ ጥናቱን ለማካሄድ በመረጥናቸው መጻሕፍት ፣ በስነልቦናዊ ርዕሰ ጉዳይ ልዩነት ማለትም እሱ አተኩሮ ላይ የሰራ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ ራስን ፍለጋ ላይ መሆኑ እና በጥናት ዘዴያችን እሱ የሥነተረክ ንድፈሀሳብ አንድ ክፋይ የሆነውን አተኩሮ መሰረት አድጎ የሰራ ሲሆን የእኔ ጥናት ደግሞ በይነ ቴክስታዊ በመሆኑ ነው፡፡

*ሰብለ ወ/ኪዳን፡፡ የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡ ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለአማርኛ ሥነጽሑፍ የፒ.ኤች. ዲ መርሃ ግብር ማሟያ ቀረበ ጥናት ነው፡፡*

የሠብለ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና አላማ " በተመረጡ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ የእኔነት መገኛ ምንጮች ተደርጎ የቀረበው ሀሳብ ምንድን ነው? የሚለውን መለየት ነው፡፡ ንዑሳን የጥናቱ ዓለማ በሥነጽሑፍ ውስጥ እንዴት ባሉ ስልቶች ሐተታዎች እንደቀረበ ማብራራት፣ የአማርኛ ልቦለዶች በአንድ ሰው እኔነት መፈጠር ላይ ሌላ ስላለው ሚና ምን ይላሉ የሚለውን ማሳየት እና በአማርኛ ልቦለድ በአንድ ሰው የራስ ምስል ወይም እኔነት እና ማንነት መካል ስላለው ግንኙነት አተያይ ማብራሪያ ናቸው፡፡ የጥናቱ ዘዴ የማናበቢያ ንድፈሀሳብ "የ Jacques Lacan" የእኔነት ትንተና ተመርጧል፡፡ የተዛማጅ ጥናት ቅኝቷ የማንነት ተኮር ጥናት በአማርኛ ረጅም ልቦለዶች በሚል ርዕስ የፈቃደ አዘዘ " The intellectual in the Ethiopaina novel " ከ 1930-1974 በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ 1989 ዓ.ም የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ እና የቴወድሮስ ገብሬ **በይነ-ዲስፕናዊ የሥነፅሁፍ ንባብ** ( 2001 ዓ.ም) በሚለው መጻሕፍቸውን አራተኛ ክፍል " የአማርኛ ርዕይ መነጠቅ ልቦለዶች በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ተመልክታለች፡፡ ከጥናቶቹ በመነሳት በአማርኛ ልቦለድ ውስጥ የእኔነት ጽንሰሀሳብን ለመፈተሽ የተነሳ ጥናት አይኑር እንጂ

የገፀባህርያትን የማንነት ጥያቄ የአጥኝዎች ትኩረት እንዲሆን ያስገደዱ ሥነፅሑፋዊ ስራዎች በመግለጽ አብራርታለች፡፡

በትንታኔዋ " ፋለስ፣ ፍላጎትና ባይተዋርነት በሚል ርዕስ ስር የበአሉ ግርማ ከአድማስ ባሻገር ፣ የአዳም እረታ ግራጫ ቃጭሎች እና የአለማየሁ ገላጋይ የብርሃን ፈለጎች እንዲሁም በፍቅር ስም የራስ ማንነት ምስል ወይም እኔነት ትንተና ቀርቧል፡፡ በመደምደሚያዋ በፋለስ፣ ፍላጎትና ባይተዋነት ንድፈሀሳባዊ ማዕቀፎች አድርገው የተመረጡ ልቦለዶች ትንተና በመነሳት ተረካዎቹ የእኔነት መፈጠር መሰረት ድብቅ የሆነ ሃይል እንዳለ የሚጠቁሙ ናቸው የሚል መደምደሚያ መስጠት ይቻላል ትላለች፡፡

ጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊና ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቱ በዝርዝርና በጥልቀት መቅረቡ የጥናቱን እሳቤዎች በአግባቡ እንድንረዳቸው ማድረጉ፣ በታላሚ ልቦለዶቹ ውስጥ የእኔነት መገኛ ምንጩን ለማግኘት በውል ተተንትኖ መቅረቡ ተገቢ ማጠቃለያ መስጠቱ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡

የእኔና የሰብለ ጥናት ሚመሳሰለው በአንድ ደራሲ ስራዎች (የብርሃን ፈለጎችን አንዱ ታላሚ ልቦለዷ ስለሆነ)ሁለተቻንም ከመስራታችን ባሻገር ስነልቡናዊ እሳቤዎች ላይ መስራታችን ያመሳስለናል፡፡ ከላይ ከቀረቡ ጥናቶች የበለጠ የሚያቀራርበው እኔነት እና ራስ ስነልቦናዊ እሳቤዎች የተቀራረቡ መሆናቸው ነው፡፡ የእኔ ጥናት ከሰብለ ጋር የሚያለያየው እሷ በዋንኛነት ለጥነቷ ማናበቢያ ዘዴ የተጠቀመችው የ "Jacques Lacan" የእኔነት ትንተና ሲሆን እኔ ደግሞ በዋንኛነት የተጠቀምኩት የዩንግያን ራስን ፍለጋ ስነልቡናዊ እሳቤ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.ትንታኔ

በዚህ ምዕራፍ ስር በአለማየሁ ገላጋይ ሶስት ስራዎች ማለትም **በፍቅር ሥም፣ታለ በእውነት ሥም** እና ሀሰተኛው **በእምነት ሥም** መፅሀፍት ውስጥ የሚገኘው ዋናው ገፀባህርይ ታለ ከዩንጊያን 8 የራስን ፍለጋ የእሳቤው ዋና መገለጫ ባህርያትን መነሻ በማድረግ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ እነዚህ ሶስት መጻሕፍት ምንም እንኳን በርዕስ ቢለያዩም የአንድ ደራሲ ተከታታይ ስራዎች መሆናቸው፣ ከአንዱ ወደ አንዱ የሚሸጋገሩ ገፀባህርያት መኖራቸውና የታሪክና የጭብጥ ስንስል መኖሩን ስንመለከት ሶስትዮሽ (ታራይሎጅ) መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ትንተና ሳደርግም በእያንዳንዱ አርዕስት ስር እንደየ ሀሳብ ተዋረዱ ከሶስቱም ልቦለዶች ሀሳቦችን በማምጣት በማስረገጥ ይሆናል፡፡ ሆነው ሆኖ ትንተናውን ለማድረግ ያመች ዘንድ የሶስቱንም መፅሀፍት ታሪክ በአጭሩ እንመልከት ፡፡

በልቦለዱ ውስጥ አንድ አቶ ቢዘን እና ወ/ሮ አንጓች የሚባሉ ገፀባህርይ ስድስት ሴት ልጆችን ከወለዱ በኋላ በብዙ ሀይማኖታዊ እና ልማዳዊ ተማፅኖና ልመና በኋላ አንድወንድ ልጅ ይወልዳሉ፡፡ ሥሙንም ታለሰው ይሉታል፡፡ እናቱ ወንድ ልጅ እንዲወለድላቸው ቤተክርስቲያን ፀሎት አድርገዋል፤ እንዲሁም ጠንቋይ ቤትም(አፋ አቡኮ) እየሄዱ ተማፅነዋል፡፡ ከወለዱ በኋላም በተፈጠረበት የጤና እክል ምክንያት ሁለቱ ቦታዎች እየሄዱ ልመናና ተማፅኖ አድርገዋል፡፡

ታለ ከእናቱ ጋር ወደ ቤት በመጣ ሰው ምክኒያት የጤና እክሉ ተስተካክሎለት ትምህርቱን እየተማረ ባለበት ሰዓት በሴታሴት ተግባሩ በቅርቡ ያሉ ሰዎች ሲሳለቁበትና ተደጋጋሚ አስተያየት ሲሰጡት ይመለከታል፡፡ በዚህም ስለ ራሱ መጠየቅና እንዴት ወንዳወንድ መባል የምችለው? በማለት የተለያዩ ተግባራትን መፈፀም ይጀምራል፡፡ በዚህ መካከል የ11ኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ ከተሰራለት ዶርም ባለመውጣት ለ2 ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ የተለያዩ መፅሐፍትን ያነባል፡፡ ጠና ጋሸው ከሚባል የእህቱ ባል ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ይከራከራል፣ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ይጥራል፤ የገባውን ደግሞ ሞግቶ ለማስረዳት ጥረት ያደርጋል፡፡ በዚህ መካከል የመጀመሪያ ሴት ጓደኛው(ሲፈን) ጋር መለየቱና ወደ ናዝሬት መሄዱ ተጨማሪ የእለት ከእለት ጥያቄ ሆኖበት ነበር፡፡

ታለ በቤተሰቦቹ ጉትጎታ ምክኒያት ያቋረጠውን ትምህርቱን ቀጥሎ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በመግባት ፍልስፍና አጥንቶ ይመረቃል፡፡ በዩንቨርስቲውም በትርፍ ጊዜ በመምህርነት ማስተማር ከጀመረ በኂላ አቋርጦ ወደ ጋዜጠኝነት ሙያ ይመለሳል፡፡ ነገር ግን ይህ የጋዜጠኝነት ስራ በመቆሙ እሱና ጓደኞቹ ለከፍተኛ ችግር ይጋለጣሉ፡፡ የወንድ ጓደኛው( በአንድ ወቅት የት/ክፍሉ ኃላፊው) እና የሴት ጓደኛው ረቂቅ ወደ የዩንቨርስቲው ማስተማር ሥራ እንዲመለስ፣ ሌላ ስራ እንዲቀጠር፣ ከእሷ ጋር እየኖረ ካለበት ችግር እንዲወጣ ብትጠይቀውም አሻፈረኝ በማለት ከተከራየው ቤት ባለመውጣት በማንበብ ከቆየ በኂላ ወደ ገጠር በመሄድ መምህር ሆኖ ማስተማር ይጀምራል፡፡ በዚህ ቦታም ይጠይቃቸው ለነበሩ ህይማኖታዊ ጥያቄዎችን የተለያዩ ከበራዎች ጋር በማገኛኘት መልስ ለማግኘት፣ለመፍታት ይሞክራል፡፡

ታለ ያደርገው ከነበረው ሃይማኖታዊ ጥያቄዎች መነሻ ኤልዛቤል የምትባል ሴት የሚሄድበት ቦታ ሁሉ እየተከታተለች ባደረገችለት የታስፈልገናለህ ጥሪ የገጠር መምህርነቱን ትቶ የሃሳዊ መሲሁን ምንነት ለመገንዘብና ለመመርመር ወደ ከተማ ይመለሳል፡፡ መርምሮም ጥያቄዎቹን በከፊል መመለስ ይችላል፡፡ አንዳንዶችን ጥያቄዎች ደግሞ በእምነት እይታ በመመልከት ይደመድማቸዋል፡፡

በዚህ ሆነ በትንተናው በሰፊው በምንመለከታቸው በተለያዩ ገፊ ምክኒያቶች "ከወጣትነት እድሜው" ጀምሮ መሰረታዊ አካላዊ ፣ህይማኖታዊ፣ ማህበራዊ ጥያቄዎችን ውስጥ ይገባል፡፡ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ይጥራል፡፡ ገፀባህርይው በሶስቱም የጠመረጡ ልቦለዶች እነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ይወጣል፣ ይወርዳል፡፡

## 3.1 ቡድን እና ግለሰብ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

ይህ ሃሳብ በራስን ፍለጋ ወቅት በግለሰቡና በቡድኖች መካከል የሚኖርን ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ታለ በመጀመሪያዎቹ የልጅነት ጊዜያት ባደረጋቸው ራሱን የመፈለግ ሂደት ብዙ ችግር አልገጠመውም፡፡ በእሱና በቤተሰቦቹ መካከል፣ በእሱና በማህበረሰቡ መካከል ምንም አይነት የባህል ግጭት አልነበረም፡፡ በእኔ ላይ አለ ብሎ የሚያስባቸውን ጥያቄዎች በጥልቅ ይጠይቃል፡፡ መልስ ለማግኘት በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ያማክራል፣ ከዛ ለመውጣት በተግባር እንዲረዱት ያደርጋል፡፡ ወዲያውኑ መልስ ላላቸው ለጥያቄዎቹ መልስ ያገኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ

የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት፡፡ ታለ መጀመሪያ ራሱን የጠየቀው ወይም ራሱን መፈለግ የጀመረው በዙሪያ ያሉ ሰዎች እንዴት "ሴታሴት" አሉኝ የሚል ጥያቄ ነው፡፡

> *ምንድን ነው? ቻይና በኋላም አባቴ ምንድን ነው እኔ ላይ ያዩ የነበረው? አሁን ደግሞ ሲፈንን... እኔን ሴታሴት አድርጌ አይቼ አላውቅም፤ ስለዚህ እራሴን አላውቅም ማለት ነው? እንዴት ከራሴ ጋር ተጣለሁ? እኔ እራሴን ሳላውቅ እነ ሲፈን እንዴት ተረዱት?...*
>
> *... እራሴን ተፀየፍኩት፤ የት እንዳለሁ በማላውቅ ምንነቴ ላይ ጥላቻ አደረብኝ፡፡ እንደዛር ተፈናጥጦ እንደ አዶ ከበሬ እኔ ላይ ገዝፎ ለሌሎች ሲያሳጣኝ የኖረው ማንነቴ የመበቀል ብርቱ ፍላጎ አደረብኝ(አለማየሁ 2009፣64)፡፡*

ከላይ በቀረበው ጽሁፍ ታለሰው በእህቱ በቻይና "ሴታሴት" በመባሉ፣ በአባቱ በተደጋጋሚ "ወንድ ልጅ እግዜር አሳይቶ ነሳኝ" በማለታቸውና በመጨረሻም የመጀመሪያ የሴት ጓደኛው ሲፈን ደግሞ "የወንዶች ስራ ካለ አግዝ ፤ይህ የሴቶች ስራ ነው፡፡" በመባሉ ምክኒያት በማህበረሰቡ ዘንድ "ወንድ" የሚባለውን ደረጃ ለማግኘት ወይም ወንድ ሆኖ ለመገኘት በውስጡ ጥያቄዎች ይመላለሱበት ጀምሯል፡፡ ይህ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ኢጎው በሚገባ ባለማደጉ ምክኒያት ራሱን (ማንነቱን) የመጥላት አደጋ ሁሉ ተደቅኖበታል፡፡ ይህ ደግሞ የመጥፋትና የመኖርም ጭምር እንደሆነ በሚከተለው ንግግር በጉልህ ይታያል፡፡

> *እኔ ፀቤ ፣ ከራሴ ከተሸሸገው እኔ ጋር እንደሆነ እንደምን ላስረዳት? አባቴ፣ ቻይናና እሷ ካዩት የእኔ ወካይ ጋር የተፈጠረ የላጥፋህ አጥፋኝ ፀብ እንደሆነ እንዴት ልንገራት የት እምኔ ውስጥ ተሸሸገ? እንዴት እንደምን አጮልቆ ለእነሱ ታየ?... እራሴን ፈራሁት፡፡ በየትኛው ድርጊቴ ውስጥ ተቀጥላው እኔነቴ ብቅ እንደሚል አልተገለፀልኝም፡፡ ስተኛ? ሳወራ? ስበላ? ስለብስ? ... የቱ ድርጊቴን ተንተርሶ ሴታሴትነት ብቅ አለ? ለእኔ ግልፅ አይደለም(አለማየሁ 2009፣68)፡፡*

እዚህ ላይ እንደምንረዳው ታለ ሴታሴት እንዴት እንደሆነ? በየትኛው ድርጊቱ እንደሚታይ ይጠይቃል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ራሱን ለመፈለግ መንደርደሪያ ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ የሰጠውን "ወንድነት" ለማግኘት የተለያዩ ተግባራትን መፈፀም ይጀምራል፡፡ ከእነዚህ ድርጊቶች መካካል ደግሞ የመጀመሪያው ወደ ጦር ሜዳ ለመሄድ መታፈስ ነው፡፡ ምክኒያቱም በማህበረሰቡ ጦር ሜዳ መሄድ የወንዶች ጥሩ የጀግንነት መገለጫ እና ወንድ መባያ የስራ

መስክ እንደሆነ ካለው ቤተሰባዊም (አባቱ ወታደር መሆናቸው) ልምድም ይሁን በማህበረሰቡ ዘንድ ያ ነፀብራቅ እንዳለ ያውቃል። ይህን ደግሞ ታለ ራሱ እንዲህ በማለት ይናገራል፡-

> *አንዳንድ ሰዎች በስጋት የዩኛል። ወንድነቴን በመታፈስ ፣ ከዚያም ወታደር በመሆንና በመሞት የማገኘው ከሆነ ግድ አልነበረኝም። በተዘጋ በርና መስኮት በኩል ስሜን የሚጠሩ ድምፆች ይሰሙኛል።... ጡረታ ድልድይ ላይ የማይጠፉት ጡረተኞች እንኳን የሉም። እንዳይታፈሱ ፈርተው ይሆን?... አቢዮት ጠባቂዎች አደባባዩን ትተው መንደር ለመንደር ያስሳሉ። ስለዚህ ጭር ብሏል። በተለይ የወንድ ዘር አይታይም። ... እንኳን ለመሰልጠን ጊዜ የሚሰጠውን ፣ እንኳን ወታደር ለመሆን ጊዜ የሚበላውን ጦርነት አሁን እዚህ ብሞት ለኔ ምንም አልነበረም(አለማየሁ 2009፣ 65)።*

ይህ ታለ በሴት ጓደኛው በሲፈን ፊት ክብር አግኝቶ "ወንድ" ሆኖ ለመታየት አብዮት ጠባቂዎች ወንድ እየፈለጉ በሚያፍሱበት ሰዓት እሱ በቀጥታ ወደ እነሱ የሄደበት አጋጣሚ ነው። በእርግጥ ታለ ወታደር የመሆን አላማ፣ፍላጎት፣ ወኔ እና ድፍረት ያለው ሆኖ ሳይሆን በሌሎች ሰዎች "ሴታሴት" የተባለውን "በወንድነት" ለመተካት በማሰብ ነው። ይህን ደግሞ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይልን "ድብቅ እኔቴን መበቀል የምችለው በመቆም ሳይሆን በመሮጥ ነው" የሚለው አባባሉ ነው። ይህ ማለት ታለ ይህን ማድረግ የፈለገው በእነሱ ፊት ሞገስ ለማግኘት እንጂ ከልቡ ተደፋፍሮ ወይም ጀግና ሆኖ አይደለም። ይህ አጋጣሚ በእርግጥ ምንም እንኳን በእናቱ ጥረት እንዳይታፈስ ቢያደርገውም በእህቱ በቻይና፣ በአባቱና በሲፈን ፊት የፈለገውን ክብር ወንድ መባልን አስገኝቶለታል። በዚህ ድርጊት በግለሰቡና በቡድኑ መካከል አንዱ ለአንዱ መተጋገዝና ማዘን እንጂ ግለሰቡ ቡድኑን ሲያኮርፍ ወይም ሲኮንን አይታይም።

ሌላው ሁለተኛው ታለ የወሰደው እርምጃ ደግሞ ቻይናን (እህቱን) ወንድ አድርጊኝ ብሎ መጠየቁ ነው። እህቱ ቻይና ቤተሰቦቿ ወንድ እንድትመስል ከመፈለጋቸው የተነሳ እሷን ከአለባበሷ ጀምሮ ድርጊቷም፣አረማመዷም፣ ውሎዋም ከወንዶች ጋር በመሆኑ በማህበረሰቡ " የወንድ" ፀባይ አላት። በዚህም እንደሷ ወንድ እንድታደርገው አረማመዱ ላይ የሚታየውን" ሴታሴት አረማመድ" ለማስተካከል እንድታስተካክለው ነው። እሷም እሺ ትለውና ወደ ስፖርት ሜዳ ወስዳ ስፖርት በማሰራት አረማመዱ ወይም አሯሯጡን እንዲያስተካል ታግዘዋለች።

*"አስቲ፣ እስቲ፣ እንዴት ነው የምትሮጠው? እጅህን ጡትህ ላይ የምታደርገው ለምንድን ነው? ጡት መያዣ አላደረግክም እንዴ? ምናባቱ!! ሂሽ!!"*

*" ስማ! የምትሮጠው ጡቷ ትልቅ ሆኖ እንደሚያስቸግራት ሴት ነው። ሂሽ! እጅህን አውርድ! ደግሞ ስትራመድ እግርህን ወደ ፊት እንጂ ወደ ጎን አትስደድ ገጥመህ ወደ ጎን የምትራመደው ድንግልናህ እንዳይጠፋ ነው?... ሂሽ!"... ይሄ አካሄድና እርምጃ እኔ ውስጥ ተደብቆ ነበር? ግራ ያጋባል። ትምህርት ቤት ስፖርት ክ/ጊዜ ይስቁብኝ ነበረው ለዚህ ኖሯል? ይህን ለማረም ከወር በላይ ፈጀብኝ(አለማየሁ 2009፣79)።*

ነገር ግን የመጀመሪያው ቀን የስፖርት ገጠመኙ የምንመለከተው የተደበቁ ማንነቱን በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው። አሯሯጡ፣ የእጅና የእግር አጣጣሉ ለመሸፈን ቢፈልግ እንኳን በወቅቱ በቶሎ መቀየር ያልቻላቸው ማንነቱ ናቸው። በዚህ ደግሞ እስከማልቀስ ደርሷል፤ ተማሪዎች እንዲስቁበት አስደርጎታል። ነገር ግን ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት በህመም ውስጥ እንኳን ተራምዷል።

በዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሀሳብ የዩንጊያን ንድፈሀሳብ የሚያፀናው "አኒማ" ወይም በወንዶች ውስጥ ያለ የሴቶች ነፍስ ወይም በወንዶች ውስጥ የሚገኙ የሴቶች መገለጫዎች መኖርን በትክክል ያሳያል። እነዚህ መገለጫዎች ደግሞ አካላዊና ስነልቦናዊ ናቸው። ነገር ግን ታለ ከእነዚህ መገላጫዎች ጋር እንዲኖር የማህበረሰቡ ባህል ሊፈቅድለት አልቻለም። በዚህም አስገዳጅ ሁኔታ በከፍተኛ ልምምድ አካላዊ መገለጫዎችን ለማስተካካል ችሏል። ለሁለተኛው ጥያቄ መልስ ሲፈልግ በቡድኑ ድጋፍ አልተነፈገውም። ግላዊ ጥያቄው በቡድኑ እርዳታ መስተካከል ችሏል። ከዚህ በኋላ የሚመጡ ራስን ፍለጋዎች ግን በታለና በቡድኑ መካከል ያለው ግንኑነት የሻከረበት በውጤቱም የተለያዩ ችግሮች የገጠሙበት ነበር።

ታለ አስራ አንደኛ ክፍል ሲደርስ ( ይሕ እድሜ ክልል ከፍተኛ የሆነ የማንነት ጥያቄ የሚጠየቅበት ወቅት መሆኑ ልብ ይለዋል) ትምህርቱን አቋርጦ ቤቱን በመዝጋት መፅሐፍ ማንበብ ይጀምራል። የዚህ መነሻው ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መጻሕፍት ውስጥ መልስ ለማግኘት የሚል ነው። ትምህርቱን ካቋረጠ በኋላ ቢሆንም የሻንበል ጠና ጋሻው(በመጀመሪያ ከኢህአዴግ ጋር ጦርነቱን አሸንፈው ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ የወታደር ሻምበል መሪ ሁኖ የመጣ

ከዛ በኋላ የእህቱ ባል የሆነ) ጋር ሲገኛኝ የሚከተለውን ምክር ስለ ማንበብ አስፈላጊነት ሰጥቶታል፡፡

> *ጥሩ፣ የሕይወት ጥያቄ በእነዚህ መፅሐፍት ከሚሰጠው መልስ በላይ ይበዛል፡፡ ጥሩ፤ ድፍረት ይመስላል ግን ባህልንና ስነልቦናህን የሚያውቁ ደራሲዎች የሚፅፏቸውንም ማንበብ ያስፈልጋል፡፡እሱን አንብብ…ጥሩ ለንባብ ዘግይተሃል፣ ቢሆንም ጀምር፡፡ መፅሀፍት ለጥያቄዎችህ ቀጥተኛ ምላሽ ባይኖራቸውም እንኳን የማሰብ ልምምድህን በማፍጠን የጥያቄህን ምላሽ እራስህ እንድታገኝ ያግዙሃል (አለማየሁ 2009፣155)፡፡*

ይህ ምክር የበለጠ ጉልበት ሰጥቶትም ሊሆንም ይችላል ትምህርቱን አቋርጦ ለ2 ዓመት ያክል አንብቧል፡፡ ነገር ግን ይህ ከማህበረሰቡ ተገሎ ማንበብ ከቡድኑ (ከማህበረሰቡ) ጋር ያለው ግንኙነት እንዲቋረጥና በስተመጨረሻም የጠበቀውን ውጤት ሳያገኝ እንደወጣ በራሱ አንደበት ተናግሯል፡፡

> *ለአመታት ቤቴን ዘግቼ እራሴን አልፈለግኩም? በራሴ ላይ ከመዘባበት ውጭ ምን አገኘሁ? እንደ ባሕት የምትቆጠር ቤቴን ከፍቼ የገባሁት የ11ኛ ክፍል ትምህርቴን አቋርጬ ነው፡፡ የዘጋሁትን በር ከፍቼ ስወጣ በአንዲት ጀንበር እድሜ ሁለት አመታት አልፈው ነበር፡፡ እነዚህ ሁለት አመታት በውስጣቸው ብዙ ቅራቅንቦ እንደያዙ ሁለት ከረጢቶች ነበሩ፡፡ አንዱ ከረጢት ብዙ መጻሕፍት ይዟል፡፡ ሌላው ከረጢት ውሰጥ አያሌ ክንውኖች ቁልጭ ብለው ይታዩኛል፡፡ ክንውኖቹ የመጻሕፍቱን ያክል ህይወትን ቁልጭ አድርገው የሚያስተምሩ ነበሩ (አለማየሁ 2011፣8)፡፡*

በዚህ የታለ የራስን ፍለጋ ህይወቱ እንዳለፈው ("ሴታሴት" የተባለበትን ክብር እንደመለሰበት "ወንዳወንድ" እንዳገኘበት ጊዜ) የግልና የቡድን ወይም የቤተሰቡንና ማህበረሰቡን ፍላጎት ያላጣጠመበት፣ ይልቁንም ራስን ፍለጋ ውስጥ ነኝ በሚል እሳቤ የተገለለበት ወቅት ነበር፡፡ በዚህ ሂደት ከላይ ባለው ንግግርም እንደምንረዳው ምን እንዳገኘ እንኳን በቅጡ ያልተረዳበት ህይወት አሳልፏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ትምህርቱን አቋርጧል፡፡ ቡድኑን(ቤተሰቦቹን) ምን ይሻለዋል? ይሆን ጭንቀት ዳርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ትምህርቱን መቀጠል እንዳለበት ከወሰነ በኋላ ዩንቨርስቲ ገብቶ የፍልስፍና ትምህርት ተምሮ ከተመረቀና ስራ ከጀመረ በኋላ በተመሳሳይ ስራ ማቋረጥ እና ቤተ ዘግቶ ማንበብና ለጥያቄዎቹ መልስ ማግኘት ሂደትን ቀጥሎበታል። ነገር ግን አሁንም ተመሳሳይ የሆነ የግልና የቡድን ፍላጎት የማጣጣም ችግር እንደገጠመው መረዳት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ከሴት ጓደኛው ከነፀብራቅ ሳይቀር  የተነገረው አስተያየትና ግጭት አብነት መሆን ይችላል።

> *እንዴት ይህን ያክል ዝቅ ማለት ይቻላል? እንዴት ሁሉን ነገር ትቶ ህይወትን ባዶ በማድረግ ኑሮን መምራት ምርጫ ይሆናል? ቤትን ክፍት ትቶ እርኩስን፣ ቅዱሱን ሳይመርጡ መጋበዝ ለሰው ልጅ ይቻላል?... መጀመሪያ ጋዜጠኝነት ያንተ ቦታ አልነበረም። ጭንቅላትህ እኮ ከዚህ በላይ ሊያሰራ የሚችል ነው። ሁለተኛ ቋሚ መምህርነት ተወዳድረህ መግባት ስትችል በኮንትራት ውርደት መምህርነትን መረጥክ። እሺ ይሁን ፤ ለምን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በደህና ደሞዝ አትቀጠርም? እኔም ብሆን ላገኝልህ እችላለሁ(አለማየሁ 2011፣92)።*

በዚህ የነፀብራቅ ንግግር ላይ እንደምንረዳው ባለው የትምህርት ዝግጅት እና ስራ የመቀጠር እድል የተሻለ ቦታ ላይ መገኘት ይችል ነበር። ነገር ግን ራሴን እየፈለግኩ ነው በሚል ሰበብ በማይመች ቤት ውስጥ እና በከፍተኛ ርሃብ ውስጥ ተገኝቷል። ይህ ብቻ አይደለም በውስጣዊ ዓለም የመመሰጥ ሂደት ራሱን ከማህበረሰቡ ወደ ማግለልና በዚህም ምክኒያት በተለያዩ ጊዜያት ራሱን ለማጥፋት ማሰብ ውስጥ ገብቶም ነበር። ይህ ከቡድኑ ጋር የነበረው ግንኙነት ካለመጠንከሩ ጋር ተያይዞ የመጣ ችግር ነበር። ለማስረገጫ እንዲሆነን ይህን የታለ ንግግር እንመልከት፡-

> *ብዙ ጊዜ ቤትህ ውስጥ፣ አንዳንዴ መንደርህ ውስጥ፣ሌላ ጊዜ ከተማህ ውስጥ፣ አልፎ አልፎ ሃገርህ ውስጥ መገኘት እንደሌለብህ አይሰማህም? የአንተ እዳው ገብስ ነው። ሀገርህን መሸሽ -መሰደድ! ጉዱ ዓለም ውስጥ ለአንተ ቦታ እንደሌለ ስትደመድም ነው። መፍትሄው በአንድ ጊዜ ከስደት እራስን ወደ ማጥፋት ይሸጋራል። ለእኔ ዓለም ላይ ቦታ የለም፤ ሲልቪያ ፕላት ከማይፈታ ቤተሰባዊ ችግር ውጭ ለእርሷ የሚሆን ቦታ ዓለም ላይ በማጣቷ ነው ጭንቅላቷን ዳቦ መጋገሪያ ውስጥ ከትታ የሞተችው (አለማየሁ 2011፣ 148)።*

## 3.2 . ሁለት አጋማሽ ህይወት በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

በዚህ ርዕስ ስር በታለ የራስን ፍለጋ ህይወት ሁለት አጋማሽ ህይወት እውነት ተከስቷል የሚለው የሚዳሰስበት ነው፡፡ በታለ የመጀመሪያዎቹ ራስን ፍለጋ ሂደት በተለየም በፍቅር ሥም ላይ ያሉ ራስን ፍለጋዎች የመጀመሪያ አጋማሽ ህይወቶች ናቸው፡፡ እነሱም ብዙውን ጊዜ የራሱን ግላዊ ጥያቄዎች ለመሙላት የደከመበትና ማህበራዊ ክብሩን ከፍ ለማድረግ ጥረት ያደረገበት ወቅት ነው፡፡ ይኸውም ያደረጋቸው ፍለጋዎች በማህበረሰቡ ዘንድ "ወንድ" መባል፣ አካሄዱን እንደ ወንድ ማድረግ፣ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ተከራክሮ በእውቀት የበላይ ሆኖ መገኘት ወዘተ. ናቸው፡፡

የሚጠይቃቸው ጥያቄዎችም ይህን የሚደግፉ ነበሩ፡፡ *"ወንድ አድርጊኝ" አልኳት "በእናትሽ ቻይና ወንድ አድርጊኝ..." ዝም አለች፡፡ እራሴን ጠላሁት ፤ በናትሽ አለዚያ እራሴን እገላለሁ፡፡ ደግሞ እውነቴን ነበር፡፡ ደነገጠች ትወደኝ ኖሯል?... ወንድ ለመሆን መዋጋት ካለብኝ እዋጋለሁ፣ መሞት ካብኝ እሞታለሁ* (አለማየሁ 2009፣ 77-78)፡፡ ከዚህ የምንረዳው ታለ ማህበረሰቡ ሴታሴት ከሚለው አረማመድ፣ አነጋገር መውጣት እና ትክክለኛ ወደ ሚባለው የወንድ አካሄድና አነጋገር መሸጋገር የእኔነት ጥያቄው ነበር፡፡ ይህ የእኔነት ጥያቄው መልስ ሲያገኝ ደግሞ ደስተኛ ሲሆን ይታያል፡፡ *" ለአንድ ሰሞን ወንዳዊ አካሄድና አሯሯጥ ብርቅ ሆኖብኝ ሰነበተ፡፡ እኔን ለሚያውቅ እንጅ ለማያውቅ ልዩነቱ የማይታይ ተራ ጉዳይ መሆኑ እንደተገለጠልኝ ስሄድ መርሳት ጀመርኩ"* (አለማየሁ 2009፣80)፡፡

ታለ ወንዳወንድነቱን ውትድርና በመሄድ፣ በመሞት ጭምር ለማግኘት ጥልቅ የሆነ ፍላጎት ነበረው፡፡ በዚህም ውትድርና ምልመላ ሲደረግ ሁሉም በፈራበት ሰዓት እሱ መሄዱና ያን በማድረጉ በአባቱ፣በሲፈን (ሴት ጓደኛው) ያመጣለትን ተቀባይነትና ክብር ይወደውና ይደሰትበት ነበር፡፡

ሌላው ማህበራዊ ክብርና የበላይነት ማግኘት የሚፈልግበት ጉዳይ እውቀት ነበር፡፡ እናቱ ለምንድነው ትምህርትህን ትተህ ቤት ዘግተህ የተቀመጥከው ብለው ሲጠይቁት *" በሻንበል ጠና ጋሸው እውቀት ቀናሁ ፤ ጫት በሚያመነዥኩት ፈላስፎች ፊት አፈርኩ ብላት ይገባታል? እውነቱ ግን ይህ ነው"*(አለማየሁ 2011፣8)፤ ሲል ይደመጣል፡፡ ከዚህ የታለ ንግግር እንደምንረዳው ታለ በሚያነቡ እና እውቀት አላቸው በሚባሉ ሰዎች የሚቀናና እነሱን መሆን መምሰል ትልቁ ዓላማው መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህን ካደረገ በኋላ እንኳን ከሰዎች ጋር

በሚያደርጋቸው ምሁራዊ የሀሳብ ክርክሮች በእሱ አሸናፊነት ካልተደመደሙ ከፍተኛ ቁጭት ውስጥ ሲገባ እንመለከታለን፡፡ ለዚህ አብነት የሚሆነው ከጠናጋሽው ጋር ባደረገው ሙግት በበላይነት ባለመደምደሙ የተሰማውን የበታችነት ስሜት መመልከት ይቻላል፡፡

> *ጠና ጋሽው ሲያሳረግ ወይም ክርክር ሲረታኝ እንደሚሆነው ሁሉ ከባድ ፀጥታ ወረደብኝ፡፡ እኔ እትከነከናለሁ፡፡ ጭንቅላቴ ጠና ጋሽው በሀሳብ እንዲጋተር ( በወቅቱ) ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ከሁሉም ነገር እርቄ መፅሐፍት ውስጥ ተደብቄያለሁ፡፡ ዛሬም ነገር ግን ሀሳብ ከማንሳትና እየጠየቁ ከመቆስቆስ ያለፈ በእኔ አሸናፊነት የሚደመደም ክርክር የለም (አለማየሁ 2011፣ 20)፡፡*

እነዚህ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን፣ ክብርን ለማግኘት የሚደረጉ ፍላጎቶችና ተግባራት የራስን ፍለጋ መጀመሪያ አጋማሽ ህይወት ናቸው፡፡ ይህ በታለ ራስን ፍለጋ ሂደት በሚገባ ተንፀባርቋል፡፡ ነገር ግን ራስን ፍለጋ ከመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት ሚቀጥል ሌላ ሁለተኛ ህይወት አለው፡፡ የሁለተኛው አጋማሽ ህይወት እንደ መጀመሪያው በራስ ክብር እና ዝና መገንባት ላይ የሚቀጥል ሳይሆን በዚህ ዓለም የመኖር ፋይዳዎችና ጥያቄዎች የሚጠየቅበት አጋማሽ ህይወት ይሆናል፡፡ ከዚህ በታች ይህን ሂደት በሚገባ እንመርምር፡-

ታለ የመጀመሪያው አጋማሽ ህይወትን ከጨረሰ በኋላ በተለይም **ሐሰተኛው በዕምነት ሥም** መጽሐፍ ላይ የተለያዩ በዚህ አለም የመኖር ትርጉም ጥያቄዎችን ሲጠይቅ ይስተዋላል፡፡

> *እውነት ህይወት ለኔ ምን ማለት ናት?.. ህይወት ከከንቱ ውልደት ወደ ከንቱ ሞት የመንዝ ከንቱ መናወዝ አይደለምን?ስል ለራሴ ምላሽ ሰጠሁ፡፡ የመፅሐፉ ደራሲ ዶክተር አልፍሬድ አድለር ማንኛውንም ሰው የህይወት ፍችው ምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ ምላሽ የለውም ብሎ ይደመድማል፡፡ የሰው ልጅ በተናጥል መኖር ስለማይችል ጥሞናውን በጫጫታ፣ ቁምነገሩን በጭዋታ እያድበሰበሰ ተላላ ህይወት ያስተናግዳል፡፡ ሳይኖር ይሞታል፡፡ በምፅአት ቀን፡- " እንደምን ኖረህ መጣህ?" ይለኛል ፈጣሪ፤ " እንደምን እንደኖርኩ እንጃ" እለዋለሁ(አለማየሁ 2012፣14)፡፡*

ይህ ጥያቄ እውነትም ታለ ከመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት ወደ ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ማደጉን ጉልህ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በዚህ ዓለም የመኖሩን ትርጉም መጠየቅ ጀምሯል፡፡ የእሱን ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በዚህ ዓለም የመኖር ትርጉም ምንነት ሲጠይቅ ይስተዋላል፡፡ መጠየቅ

ብቻ ሳይሆን እሱ ምን እንደሰራ ቢጠየቅ ምንም እንደሆነ በመመለስ ለሌላ ራስን ፍለጋ እያዘጋጀ ነው። የመኖር ዓላመው ምንድን ነው? አንኳር የእራስን ፍለገ ጥያቄ ጠይቋል። በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት እንደነበሩ ጥያቄዎች የአካላዊ ጥያቄ መልሶችን በመመለስ፣ የራስን ክብር ከፍ በማድረግ ብቻ ማለፍ የሚቻል አይደለም። ለዚህ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሆን ዶስቶቭስኪን ዋቢ በማድረግ የሞገተበትን ሀሳብ እንመልከት።

> *ሰው በዳቦ ብቻ የማይኖር እንግዳ ፍጡር ነው። የጥበብ፣ የመመራመርና የእምነት ፍላጎቶቹ በህይወት ለመቆየት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ እስከመሆን ደርሰዋል። ሩሲያዊው ደራሲ ፊዮዶር ደስትየቭስኪ " the secrate of the man's being is not the only to live" ያለው ለዚህ ነው። but to have some thing to live for" የሰው ልጅ መኖርን ብቻ በሌጣው አይሻም። የሚኖርለት የህይወት ፍች ይፈልጋል፤ እንዲያ ካልሆነ በምድር ላይ ከመቆየት ይልቅ እራሱን ቢያጠፉ ይመረጣል ይላል ዶስትየቭስኪ ። እውነታን ብቻ አይደለም የምናብ ቅንብርንም እንሻለን(አለማየሁ 2012፣115-116)።*

ይህ የህይወት ጥያቄ በሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ሊጠየቅ የሚገባ መሆኑና ይህን ማድረግ መቻሉ ከእሳቤው አንፃር የታለን የራስን ፍለጋ መፈፀም ወይም ሂደት ጥሩ ደረጃ ላይ እንዳለ አስረጅ ነው። በመሰረቱ ጥያቄው ይህ ብቻ አይደለም። ስለ እምነት፣ስለክብር፣ ስለተፈጥሮ እና ፈጣሪ ጥያቄ ሲጠይቅ ይስተዋላል።

ሌላው እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ የታለ ሁለተኛ አጋማሽ ህይወት ማደጉን የምንረዳው በዙሪያው ላሉ ሰዎች አብዝቶ የሚጨነቅ ራስ ወዳድ ያልሆነ ሰው መሆኑና ለግሉ ብሎ በሚሰራቸው ስራዎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚፀፀት ሰው መሆኑን ስንረዳ ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ታለ በአንድ ወቅት ከጋዜጠኝነት ስራ ተባረው በደባልነት አንድ ቤት ውስጥአብረው በሚኖርበት ጊዜ ርሃብ ይጠናበትና ያገኘውን ቆሎ ረድ ሠርዌን ሳያሰማ ቤት ሲቆረጥም እንዳይሰማ በውሃ አርሶ በመመገቡ ያደረበት ፀፀት ነው።

> *... ሰው መሆን መጥፎ ኃይል ነው፣ የሰው ተፈጥሮ ላይ ያለው ስልጣን ሚረጋገጠው የመሰረታዊ ፍላጎት እጥረት በተፈጠረበት ስፍራ ነው። ከተፈጥሮ ጋር ተዋወቅኩ። እፍኝ ቆሎ አገኘሁ። ከየት እንደሆነ እንጃ፣ ቡና ቁርስ ሲያስዙኝ ያለይሉኝታ አፍሼ ይሆናል። ከመሬት ፈሶ ለቅሜ ሊሆን ይችላል፤*

*እና ረድ ሠርዌ ቤት ውስጥ አለ። በርሃብ ሰመመን ውስጥ የተኛ መስሏል፤ ማካፈል የሚሉት ጣጣ አለ፣ ሰው ማለት ይህ ነው። ስቆረጥም ረድ ሠርዌ እንዳይሰማኝ በውሃ እያለዘብኩ ብቻዬን በልቼ ጨረስኩት(አለማየሁ 2012፣ 129)።*

ይህ የታለ ድርጊት በዩንግ የራስን ፍለጋ ንድፈሀሳብ "ሻዶው" የሚባል ሲሆን በዋንኛነት እንስሳዊ ባህሪያችን ብቅ የሚልበት ሲሆን ፣ ይህን ለመግዛት ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ ደግሞ የራስን ፍለጋው ውጤት እየሆነ ይሄዳል። በመሆኑም ታለ በርሃብ ጊዜ ደግሞ የትኛውንም መንገድ ተጠቅሞ ራስን ማትረፍ እንስሳዊ ባህሪ ቢሆንም ታለ ግን በዚህ ተግባሩ እጅግ ሲፀፀትና አደራ የማይጣልበት እንደሆነ ሲናገር ይደመጣል። ነገር ግን ጓደኛው ዶ/ር አሮን የእሱ ባህርይ ይህ እንዳልሆነ ከዚህ ምልልስ እንዲህ ያስረግጣል።

*ከአንተ ጋር የማስቀምጠው ዕቃ አለኝ። ባህሪህ ለዚህ አደራ ያበቀሃል። ብዙ ጊዜ እንዳየሁህ ገንዘብ አንተ እጅ ላይ ኖሮ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ደግነትህን አትነፍጋቸውም። ክፉ ቢሆኑም የአንተን ልግስና አያጡም። እንዲሞት የምትፈልገው ሰው ቢኖር እንኳን የሚቀምሰው ከሰጠኸውና ካዳንከው በኋላ እራስህ ትገድለው እንደሆን እንጂ ከደግነትህ ሳይቋደስ አይቀርም(አለማየሁ 2012፣128)።*

ይህ የዶ/ር አሮን ንግግር ታለ የደረሰበት የራስን ፍለጋ ሂደት ከፍ ማለት በጉልህ ይሳያል። ምክኒያቱም ክፉ የሚባሉ ሰዎችን እንኳ ቢሆን ልግስናው እንደማይለያቸው ነግሮለታል። ይህን ደግሞ ብዙጊዜ በሃሳብ አለመጣጣም እና ግጭት ለነበረባቸው ለሙሴ ፀሊም በአደራ የተሰጠውን ብር በመስጠት አረጋግጧል። ታለ ይህን ያደረገው ተርፎት ካለው ላይ ሳይሆን በከፍተኛ የኑሮ መጎሳቆል ውስጥ ሆኖ እየኖረ ባለበት ሰዓት መሆኑ ኢጎውን ማስገዛቱን ይጠቁማል።

## 3.3 ግንኙነት በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

ግንኙነት(Relationship) በሰው ራስን ፍለጋ ሂደት ከፍተኛ የሆነ አስተዋፆ አለው። በተለይ ደግሞ በመጀመሪያዎቹ የህፃንነት ዘመን የሚኖረን ግንኙነት ከፍተኛ አስተዋፆ አለው። በታለ የራስን ፍለጋ ያገጠመውም ከንድፈሀሳቡ የተለየ አይደለም።

ታለ ከቤተሰቦቹ ጋር ባለው ግንኙነት ከሌሎቹ ልጆች በተለየ ከልክ ያለፈ እንክብካቤ እያደረጉለት ያደገ ልጅ ነው። እናቱ ከሰባቱ ሴት ልጆቻቸው በተለየ እሱን እየተንከባከቡ አሳድገውታል። ይህም ብዙ ጊዜ የአደራ ልጄ ነው፤ የስለት ልጄ ነው፤ ከመላዕክት እስከ አጋንንት ደጅ የረገጥኩበት ልጄን አትንኩ፣ ከአባ ኪሮስ እስከ ዲያቢሎስ ደጃፍ የተንከራተትኩበትን ልጄን አትንኩ እያሉ ነው ያሳደጉት። ይህን ከእናቱ ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነትና መወደድ ታለ በራሱ እንደበት እንዲህ ብሏል።

> *አንድ ቀን ድንገት ህመም ሰቅዞ ሲይዛት ያሳየችው ሁኔታ ከልጆቿ ሁሉ እኔን አብልጣ እንምትወደኝ ተገለፀልኝ። ሞት እራስጌዋ ቁሞ ካልወሰድኩ እያለ ሲተናነቃት እናቴ ትወተውት የነበረው ስለ እኔ ሆነ። "ልጄን ፣ልጄን አደራ፤ እስላም ክርስቲያኑን ደጅ የጠናሁበትን ልጄን አደራ ፣ በምድር ሰጠኋችሁን በሰማይ እጠይቃችኋለሁ። እንዲች ብሎ የከፋው እንደሁ የሰማዩ ጌታ ፊት ልፋረዳችሁ ቃል ለምድር ለሰማይ..."አለች (አለማየሁ 2009፣14)።*

በእናቱ ብቻ ሳይሆን በቀሩት የቤተሰብ አባላት ዘንድም አንድ ወንድ ልጅ ስላላቸው የተለየ ፍቅርና እንክብካቤ ያደርጉለታል፤ እህቶቹ አንዳቸው ለአንዳቸው የማያደርጉትን እንክብካቤ ለሱ ያደርጉለታል። ልብሱን ያጥቡለታል፣ አባት እያላቸው፣ ያላቸውን ከፍ ያለ መውደድ ለመግለፅ "ታለ ይሙት" ብሎ እስከመማል ይደርሳሉ።

ታለ በነበረው ቤተሰባዊ ግንኙነት በሴቶች እህቶቹ ተከብቦ ያደገ በመሆኑ በመነጨ ምክኒያት ከአረማዱ ጀምሮ ""ሴታሴት" ለመባል ና "እስኪ ወንድ ሁን" ለመባል አብቅቶታል። በመጨረሻም የአባቱና፣ የእህቱ ብሎም የመጀመሪያ ልጅነት ፍቅረኛው አስተያየት ተጨማምሮበት ራሱን እንዲጠይቅ ምክንያት ሆኖታል። ይሕ "ሴታሴት" እንዴት ልባል ቻልኩ የሚለው ጥያቄ ዝም ብሎ የተፈጠረ ሳይሆን በነበረው የመጀመሪያዎቹ የልጅነት አመታት ግንኑነቶች የተፈጠሩ ናቸው። ለተፈጠሩበት ጥቄዎች ደግሞ መልስ ለማፈላለግ ተፈጥሮን፣ ሰዎችን፣ ማህበረሰቡን ሲጠይቅ፣ ሲመረምር ይታያል።

> *አሞራ ሴታሴት ይኖረው ይሆን? አንበሳስ? የፍየልስ ሴት አውል ሞልቷል፤ ሴታሴትስ? ወንዱ ኤሊ ያን ሁሉ መቶ አመታት በወንዳ ወንድ ባህሪ ብቻ ይዘልቀዋል? ... ለመሆኑ ወንዱ ወፍ እንቁላል ታቅፎ ሲቀመጥ ሴታሴት*

> *ያስብለው ይሆን? አውራ ዶሮም በሰባት ሴቶች መካል ውሎ ያድራል፤ የእነሱ መራመድ አይገባበት ይሆን? (አለማየሁ 2009፣ 73)።*

ይህ ጥያቄ በእንስሳት ያለ ነው? ተፈጥሮ የሚደግፈው ነው? ወይስ አይደለም የሚለውን የመረመረበት ነው። ጥያቄው ግን በዚህ የሚቆም ብቻ ሳይሆን በሴቶችና በወንዶች መካከል የተፈጠረውን ማህበረሰባዊ የስራ ክፍፍል ማን ፈጠረው? ይህ ማህበራዊ የስራ ክፍፍል ሲፈጠር ማህበረሰቡ እንዴት ተቀበለው? የሚል ጥያቄ እየጠየቀ ለመረዳት ሞክሯል። የስራ ክፍፍሉ ደግሞ የትኛውም ቦታ የስሜት መረበሽ በሚገጥምበት እንደ ሀዘን ባሉ ቦታዎች እንኳን እንዳለ ያስረዳል። ይህ ደግሞ ማህበራዊ የስራ ክፍፍልና ስነፆታ ክፍፍል ስር የሰደደ መሆኑ ያመላክታል።

> *ወንድ እዚያ... ሴት እዚህ...በሀበሻ ምድር የፆታ አጋፋሪው ማን ነው? ለቅሶ ሲሆን ድንኳን መትከል፣ ድንኳን መንቀል የወንድ... እቃ ማጠብ የሴት በቅጡ ሀዘንን መግለፅ የወንድ ... ደረት መድቃት የሴት፣ የሬሳ ሳጥን መግዛት የወንድ... ንፍሮ መቀቀል የሴት...፤ እንጨት መፍለጥ ወንድ... ቡና ማፍላት የሴት፤ ጋቢ መደረብ የወንድ...ደረት መጣል ለሴት፤ ጉድጓድ መቆፈር ለወንድ... ወጥ መቀቀል ለሴት፤ ደልዳዩ ማን ነው? የመጀመሪያ ጠንሳሹ? በምን አሳመኗቸው ተቀበሉትና ወጥ ሰራን ወንድ አይንህን ላፈር አሉት?... ( አለማየሁ 2009፣73)*

ሌላው ከእናቱ ጋር በነበረው ግንኙነት ተፅዕኖ ያሳደረበትና ራሱን እንዲጠይቅ ምክኒያት የነበረው እናቱ ሲታመም ሆነ ታሞ ሲድን ይወስዱበት የነበረው ቤተክርስቲያን እና ጠንቋይ ቤት ነው። እንዳውም አንድ ጊዜ ይህ ያለፈው ግንኙነቱ ያሳደረበትን ተፅዕኖ ለማስረዳት " *ከእግዚአብሔር የተሻለ በአውሊያዎች ህልውና ለምን እርግጠኝነት ይሰማኛል? ልጅ ሆኜ እናቴ ይዛኝ በመሄዷ እና በመዘየሬ?*(አለማየሁ 2012፣100) ሲል ይናገራል። ይህ መጋለጥ እምነት ላይ ያሉ የራስን ፍለጋ ጥያቄዎችን እንዲያነሳ አድርጎታል።

ይህ ደግሞ በእምነቱ ላይ የትኛው ነው ትክክል? እግዚአብሔር(ፈጣሪ) አለ ወይስ የለም? ፈጣሪ እና ተፈጥሮ ሰውን ልጅ ፈጥረው ዝም ብለው ለቀቁት ወይስ በቁጥጥሩ ስር አድርገው ጥበቃቸው እንዳይለያቸው አድርገውታል? ሰው ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ ተፈጥሮን ፈጥሮት

እያለ ለመቆጣጠር እንዴት ይሞክራል? እያለ አመክንዮችን እያቀረበ እንዲሞግት ራሱን እንዲፈልግ ከፍተኛ ግፊት አሳድሮበታል።

ከዚህ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችለው ታለ እናቱ ጋር በነበረው የልጅነት ወቅት ጊዜ ይሉት የነበረው "አይንህ ይወጋል፣ ትክሻህ ይከብዳል ፣ግርማህ ያስፈራል፣ እንዲህ አትየኝ" የሚሉ አስተያየቶች እውነትም ባለ ውቃቤ ነኝ? ወይ ብሎ እንዲጠይቅ፣ ስለ ሀሰተኛው መሲህ እንዲመረምር መጨረሻም ራሱን ፈልጎ የሐሰተኛው መሲህ ሙቶ የሚነሳው አልዓዛር ሆኖ ላገኘበ ትልቅ ገፊ ምክኒያት ሆኖታል። ለዚህ ደግሞ ሲፈን እና ታለ ያደረጉት ምልልስ አስረጅ ነው።

> *"አንጓች እይኑ ይወጋል፣ ትክሻው ይከብዳል፣አደብ ገዝቶ ክፍሉ ቢቀመጥ ጥሩነው ብላለች። ለምን ክፍልህ ቡና እያፈላሁልህ..."*
>
> *ቆይቼ ቆይቼ ጠየኳት፣ ልክ አይደለሁም ግን ለምን እንደታዘዘችኝ ቀስ አድርጌ ጠየኳት*
>
> *ለአንትኮ አይደለም*
>
> *እህስ*
>
> *ለውቃቢህ ነው። ውቃቢህ ካረፈብኝ...*
>
> *እንደሴታሴተነቴ ሁሉ አንዳች የታያት ነገር ሳይኖር እንደማቀር ሳስብ ፈራኋት። እራሴነም ፈራሁት። ከዚያ ቀን አንስቶ እሸሻት ጀመር(አለማየሁ 2009፣114-115)።*

ሌለው በመጀመሪያ ጊዜያት ግንኙነቶች የመነጨው ትልቁ ግፊት አባቱ ወታደር በመሆናቸው ስለ ውትድርና ዓለም ይነግሩት የነበረው የወንድነት መለኪያነት ተፅዕኖ ታለም ይህን ሲተገብር ታይቷል። በመጀመሪያው የብሔራዊ ውትድርና ለመሄድ ሞክሮ በእናቱ ከፍተኛ ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። ይህም ሆኖ ግን የሚፈልገውን ወንዳ ወንድ የመባል ክብር እንዳስገኘለት ከላይ በቀረበው አሳቤ ተመልክተናል።

በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅትም ጠና ጋሸው ጋር በነበረው ግንኙነት በተፈጠረበት ተፅዕኖ ምክኒያት ታለ ውትድርና ገብቶ ሶስት ወር ቆይቶ በምክኒያት እንደተመለሰ እንመለከታልን።

ጠናጋሻው 11ኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ ትምህርት ያለ ሃብት አያስደስትም ብሎ ውትድርና የገባ፣ ብዙ የፍልስፍና መጻሕፍት ያነብ የነበረና የኢህአዴግ እና የኢህድሪ (ደርግ) ጦርንት ከተጠናቀቀ በኋላ ትምህርቱን ጨርሶ ፍልስፍና መመህር የነበረ ሲሆን ከታለ ጋር በነበረው ግንኙነት መጻሕፍት እንዲያነብ የመከረው፣ትምህርት ማቋረጡ እና ወደ ውትድርና እሄዳለሁ ማለቱን እንደሚያመሳስላቸው የገለፀለት፣ በተለያዩ ሀሳቦች ላይ ሲሞግተው የነበረ በመሆኑና ታላላቅ ፈላስፎች ወታደር እንደነበሩ ስለነገረው ለሁለተኛ ጊዜ ላደረገው ወደ ውትድርና ዓለም መቀላቀል አስተዋጽዎ አድርጓል።

*"የዚህ መፅሀፍ ደራሲ ፊዮዶር ደስተየቭስኪ ይባላል። ጥሩ! ሩሲያዊ ነው። በመጀመሪያ እስረኛ ነበር። ከባድ የጉልበት ስራ የተፈረደበት፤ በኋላ ውትድርና እንዲያገለግል ያደረጉት "( አለማየሁ 2009፣158)።* ይህ የጠና ጋሸው ንግግር አዕምሮው ውስጥ እንዳለ ተፅዕኖ እንዳሳደረበት የምንረዳው **ታለ በእውነት ሥም** ላይ *"ዶስተየቭስኪ፣ ቶልስቶይ፣ ሌርሞንቭ፣ ሔሚንግዌይ፣ ስቴንቤክ፣... ይሄን ሁሉ የውትድርና ቤተ-ሙከራ አልፈው ነው መልሰው እራሳቸውን ያገኙት? እንደኔ በመከራ የቆፈሩትን የነፍስ ወከፍ ምሽግ መልሰው እንዲደፍኑ ተጠይቀዋል?" አለማየሁ 2011፣162)* ። ከዚህ የታለ ንግግር የምንረዳው የፋለስፎች የውትድርና ህይወት ተሞክሮእና እሱ እነሱን ሞዴል አድርጎ እየተጓዘ ብቻ ሳይሆን በትክክል ራስን ፍለጋ ውስጥ መሆኑንም ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

## 3.4. ሁነት ወይስ ሂደት በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

ራስን ፍለጋ በታለ ህይወት ውስጥ የደረሰባቸውን ደረጃዎች ከላይ በሁለቱ አጋማሽ ህይወቶች ተመልክተናል። በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት የነበሩት ጥያቄዎች እንዳየነው የእሱን ስብዕና መገንባት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። በሁለተኛው አጋማሽ ህይወቱ ግን በዙሪያው ላሉ ጓደኞቹ መጨነቅ የጀመረበት፣ የእሱን የመኖር ትርጉም ደጋግሞ የጠየቀበት የህይወት አጋማሽ እንደነበር ተመልክተናል።

በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት የነበሩ የራስን ፍለጋ ጥያቄዎች መልስ እያገኘባቸው ሂዷል። ከላይ በተለያዩ ምሳሌዎች እንዳስረገጥነው "ሴታሴት" ለምን ተባልኩ፣ እንዴት " ወንዳወንድ" መባል እችላለሁ? ወንዳወንድ ለመባል ምን ተግባራትን ልፈፅም? የሚሉ ጥያቄዎችና በተግባር የተቀየሩና መለስ የተገኘባቸው ሆነዋል። በሌሎች ዘንድ "የአዋቂነት" ክብርን ማግኘት ትምህርት አቋርጦ ለአንድ አመት ከስድስት ወር በማንበብ ጥያቄውን በመመለስ አዋቂ ለመባል ችሏል።

ምክኒያቱም በዩንቨርስቲ መምህራን ጓደኞቹ፣ በት/ክፍል ኃላፊው ሳይቀር ከሌሎች ጓደኞቹ ይልቅ ጥናቶችን የመስራት ችሎታ ያለው እንደሆነ እና በእውቀት ከሁሉም የሚበልጥ እንደሆነ ተመስክሮለታል፡፡

ሌላው ታለ በህፃንነቱ ጀምሮ እኔ ማንነኝ፣ በህፃንነቴ ህመምተኛ ነበርኩ እናቴ ባትቀይረኝ ኑሮ ማን እሆን ነበር? የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መነሻ ሆነው ደግሞ እህቱ ቻይና እንዲህ በማለት በጎረቤታቸው ቹቹ መቀየሩን ስለነገረችው ነበር፡፡

> *እኔ ብቻ ነኝ ማውቀው፤ አባታችን የለም፤ሌሎችም ወደ ኬላ ሄደዋል፤ እኔ አሞኝ አልጋ ነበርኩ፡፡ እናቴ ገርበብ ያለውን በር ከፍታ ገባች፡፡ አንተን አዝላለች፤ አንድ እንግዳ ሰው አብሯት አለ፡፡ ሰውየው ከዚያ ተቀመጠ፣ እናታችን አንተን አውርዳ አስቀመጠችህ፤ " ሂጅ ልጁን አምጭው" አላት ሰውየው፡፡ ሄዳ ቹቹን ይዛው መጣች፡፡ ሰውየው ምን እንዳደረገ አላውቅም፤ እኔ ፈርቼ ተከናነብኩ፡፡ በቅርብ ቀን ውስጥ አንተ ዳንክ ቹቹ ታመመ(አለማየሁ 2009፣99)፡፡*

እህቱ ቻይና የነገረችው ግን ምናልባት እሱ በታለ መቀየሩን ያረጋገጠለት መልስ እንጂ እንዴት መቀያየር ተቻለ? እኔ ማን ነኝ? እሱስ ማን ነው? ስንቀያየር ማን ተጎዳ? ማን ባልፈለገው እጣ ፈንታ ውስጥ ገባ የሚለው ጥያቄ በወቅቱ መልስ ያላገኘለት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም እንዳውም እናቱ እንደቀየሩት ካወቀ በኋላ ለከፍተኛ ስነልቦናዊ፣ ቤተሰባዊ ግጭት እና ሀዘን ውስጥ ገብቷል፡፡

> *ለመሆኑ እናቴ ባትለውጠኝ እኔ ማን ነበርኩ? ቹቹስ? የቹቹ እናት እኔን ይሆን የምታሳድገኝ? እናቴስ? ማን ማን ላይ ጥሩንባ ነፋ? ማን ተጨንቆ? መንኛውን አስጨነቀ? እዚያ ቀለም አልባ ፣ ድምፅ ተራቆተበት፣ እንቅስቃሴ የነጠፈበት ዓለም ውስጥ የነበርኩት እኔ ነኝ፣ እንዴ? እኔ የምለው ማነን ነው? እሱስ? ( አለማየሁ 2009፣100)፡፡*

ይህን ከየት መጥነት ጥያቄ ከሃይማት አንፃር ከእግዚአብሔር (ከቤተክርስቲያን) ነው ወይስ ከሳይጣን (ከጠንቋይ)፣ ይህን እንዴት ማድረግ ይቻላል? የሚል ተደጋጋሚ ጥያቄ ጠይቋል፡፡ ይህን ጥያቄ **ሐሰተኛው በዕምነት ሥም** መጨረሻ ላይ ምላሽ በመስጠት ይጠናቀቃል፡፡ ይህም *"ተዓምራችን መንትያነታችን ላይ ነው፡፡ ሁላችንም አብረው ያላደጉ አምሳያ ወንድሞች አሉን፡፡ "*(301) በሚል የኖላዊ (ሀሳዊ መሲህ) ንግግር አማካኝነት ለጥያቄው መልስ ለማግኘት ችሏል፡፡

በመሆኑም በታለ የራስን ፍለጋ ህይወት ውስጥ ከላይ በማስረጃ በተደገፉት የማንነት ጥያቄዎች አንፃር ሲታይ ራስን ፍለጋ የሚጠናቀቅ መስሎ ይታያል፡፡ ምክኒያቱም ራስን ፍለጋዎቹ እያደጉ መጥተው መልስ አግኝተዋል፡፡

በሌላ በኩል እምነትን፣ የፈጣሪ እና የፍጡር ግንኙነት ፣ የተፈጥሮና ሰው ግንኙነት እና በህይወት መኖር የተመለከቱ ሌሎች ጥያቄዎችን ጠይቋል፡፡ ራሱን ለመፈለግ ሞክሯል፡፡ እምነትን በተመለከተ አንድ ጊዜ "እምነት መበዝበዣ መሳሪያ ነው፡፡ ዓላማው ደግሞ ከምድርና ከቁሳቁስ እንቶ ፍንቶ የማያልፍ ነው፡፡" ሌላ ጊዜ ደግሞ " ዘላለማዊነትን መቃወም ወይም መካድ የጅላጅሎች ሀሳብ ነው፡፡... ስለክብሩ መስገድ ይገባል" የሚሉ የማርክስንና የቮልቴርን ሀሳቦች በማንሳት ተከራክሯል፣ እውነታው ጋር ለመድረስ ሞክሯል፡፡ ነገር ግን ወዲያውኑ መልስ ማግኘት አልቻለም፡፡ አለመቻሉንም እንዲህ በማለት ይገልፃል፡፡

> *ሁሉን ለማወቅ መጣርና በሰው ልጅ የታሰበውን ሁሉ ለመሰብሰብ መፍጨርጨር ትርፉ ምንድን ነው? በቀላሉ አለመርካት ሁሉን መጠራጠር አይደለምን? የታለ ደስታየ? የታለ ከእምነት የሚገኝ እረፍቴ? ከእኔ ይልቅ እናቴ ደስታን እረፍት አላት አይደለምን? ስባዝንና ስባትል ማደሬ ትርፉ ምንድን ነው? የከን ከንቱ፣ ከንቱ ንፋስ እንደመከተል አይደለምን? (አለማየሁ 2011፣36 )፡፡*

ከዚህ በተጨማሪ የልዕለ ተፈጥሮና የተፈጣሪው ግንኙነት ምድንነው? የተፈጥሮና የሰው ግንኙነት ምንድን ነው? ፣ የህይወት ትርጉሙ ምንድን ነው? የመኖር ትርጉም ምንድን ነው? ለሚለው የራስን ፍለጋ ጥያቄ በተደጋጋሚ ቢነሳም እቅጩን ምልስ ማግኘቱን የሚገልፅ ማስረጃ የለም፡፡ እነዚህ በሁለተኛው አጋማሽ ህይወት የተጠየቁ ጥያቄዎች በሂደት እየተመለሱ የሚሄዱ መሆናቸውን ስናስብ ራስን ፍለጋ ሂደት መሆኑን በግልፅ ይጠቁማል፡፡ ይህን ደግሞ ጠናጋሻው በአንድ ወቅት ከታለ ጋር በነበረው ውይይት እንዲህ ሲያስረዳው እንመለከታለን፡፡

> *አንዳንድ ጥያቄዎች መልሳቸው መተው ብቻ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ጥሩ! ከእፀ በለሱ ጋር ውስጣችን ጋር ይግባ ፤ አይግባ ባይታወቅም ከሰው ልጅ ሁሉ እጣ ፈንታችን የሚጠቅመንና የማይጠቅመንን፤ የምንደርስበትንና የማንደርስበትን ማሰብ ሆኗል፡፡ ከጠቀመን ጥሩ! ካልጠቀመን መተው! ከደረስንበት ጥሩ! ካልደረሰንበት ለሚደርስበት ትውልድ መተው... የሰው ልጅ ውሰንና ፍጡምነት የሚጎድለው ፍጡር መሆኑን መገንዘብ፡፡ ይሄንን የተማርኩ ከአቦይ(ከአባትህ)*

*የተግባር ውጣ ውረድ ነው፡፡ እሳቸው ጋር ባልገናኝ ኑሮ ገና ድሮ እራሴን አጥፍቼ ነበር፡፡ ገና ድሮ! (አለማየሁ 2009፣ 156)፡፡*

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው ሰው ፍፁማዊ ፍጡር ባለመሆኑ ብዙ ጥያቄዎች ቢኖሩበት እንኳን መመለስ የማይችላቸው፣ በጊዜ ሂደት እየተፈቱ የሚኖሩ(የሚደረስባቸው) ይኖራሉ የሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ የተሰጠውን አዕምሮ ተጠቅሞ ፈልጎ የሚደርስበት ጥያቄ እንዳለ ሁሉ የማይደርስበት ሂደት የሆነ የራስን ፍለጋ ጥያቄዎች እንደሚኖሩት ሁነኛ ማስረጃ ነው ያረጋግጣል፡፡

## 3.5. የራስን ፍለጋ መገኛ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

የራስን ፍለጋ መገኛ እሳቤ ራስን ፍለጋ ውስጥ የሚገኛው ማንኛውም ሰው ነው? ወይስ ደግሞ ለሙሁራን ወይም ለአዋቂዋች የተተወ ነው? የሚለው የሚመለስበት ክፍል ነው፡፡ ከታለ የራስን ፍለጋ ሂደት የምንረዳው ራሱን መፈለግ የጀመረው ገና ከልጅነቱ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በዋንኛነት ግን የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ሲሞክር አይተናል፡፡ ይህ የወጣትነት (Adolescent) እድሜ እንደሚታወቀው የሰው ልጅ የማንነት ጥያቄዎችን የሚጠይቅበትና መልስ ለማግኘት የሚፍጨረጨርበት ጊዜ ነው፡፡ ታለም እሱ ይሆናል ባለው መንገድ ይህን ፍለጋ ጀምሯል፡፡

ታለ ይህን ሲያደርግ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ከመሆን ያለፈ ከምሁር የሚመደብ ሰው አልነበረም፡፡ ከዛ ይልቅ በእውቀት መተንተን የሚፈልግ አንድ ሰው ለመሆንም ነው ይህን ራስን ፍለጋ የጀመረው፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የራስን ፍለጋ መገኛ "የምሁርነት" ክልል ብቻ አለመሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሣያል፡፡ ነገር ግን ታለ ጥያቄዎቹን ተረድቶ ኢጎውን ከፍ ለማድረግ ይጥር ነበር፡፡ ያ ማለት የመጀመሪያ አጋማሽ ህይወቱን በሚገባ ያላሳደገ ምናልባት ራስን ፍለጋ ጅማሮ ላይ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ነገር ግን በአምሮው ውስጥ የሚመላለሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ኀበዝ የስነልቦና ጸሃፊዎች የፃፋቸውን መጻሕፍት እንዲያነብ ምክር ማግኘቱ ማንበቡን ይበልጥ እንዲገፋበት አድርጎታል፡፡ ይህ ታለ ከመጀመሪያ አጋማሽ ህይወት ጥያቄዎች በጥሩ መልሶ የራስን ኢጎ ከፍ በማድረግ ወደ ሁለተኛ አጋማሽ የህይወት ራስን ፍለጋ እንዲገባ መደላድል ሆኖሎታል፡፡

*ጥሩ፣ የሕይወት ጥያቄ በእነዚህ መፅሐፍት ከሚሰጠው መልስ በላይ ይበዛል። ጥሩ፤ ድፍረት ይመስላል ግን ባህልንና ስነልቦናህን የሚያውቁ ደራሲዎች የሚፅፏቸውንም ማንበብ ያስፈልጋል። እሱን አንብብ…ጥሩ ለንባብ ዘግይተሃል፣ ቢሆንም ጀምር። መፅሀፍት ለጥያቄዎችህ ቀጥተኛ ምላሽ ባይኖራቸውም እንኳን የማሰብ ልምምድህን በማፍጠን የጥያቄህን ምላሽ እራስህ እንድታገኝ ያግዙሃል (አለማየሁ 2009፣155)።*

ከላይ የቀረበው ሀሳብ ሰው ባነበበ ቁጥር፣ ባወቀ ቁጥር አምሮው የሰላ እንዲሆን፣ ራስን ፍለጋው የሰመረ እንዲሆን እንደሚያግዝ ከታለ የራስን ፍለጋ ህይወት መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ማንበብ ብቻው ጥያቄዎችን ሁሉ ይመልሳል ማለት አይደለም። የማይመልሳቸው ብዙ የራስን ፍለጋ ጥያቄዎች እንዳሉ ከዚህ ከፍ ብለን ተመልክተናል።

በአጠቃላይ ከታለ የራስን ፍለጋ ህይወት የምንረዳው ራስን ፍለጋ ራሱን ለመፈለግ ዝግጁ ባደረገ አዕምሮ ሁሉ የሚጀመር መሆኑን፣ለማስቀጠል ግን የሰላ አዕምሮ እንዲኖረን መጠየቅ፣ ማወቅ፣የሚመጣውን ህመም ለመቋቋም የሚያስችል የአዕምሮ ሁኔታ ሊኖረን እንደሚገባ ያስረዳል።

## 3.6. ፀረ ራስን ፍለጋ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

ፀረ ራስን ፍለጋ የምንላቸው ራስን ፍለጋ በትክክል እንዳይሳካ የሚያደርጉ ስሜቶች ናቸው። ከዚህ አንፃር በሶስቱ ልቦለዶች ውስጥ በታለ የራስ ፍለጋ ምን ተከሰተ የሚለውን ቀጥለን እንፈትሻለን። ታለ የመጀመሪያውን አጋማሽ ህይወት የራሱን ክብርና ማንነት በሚገነቡ ጉዳዮች ላይ መጠመዱን እና ኢጎውን ማሳደጉን አይተናል። በሁለተኛው አጋማሽ ህይወቱ ይህን ኢጎ ተቆጣጥሮ ወደ ሚፈለገው የሕይወት መልስ ሂዷል ወይ? የሚለውን የምንመለከትበት ሲሆን ካልሆነ ይህን ማድረግ ያላስቻሉትን ፀረ ራስን ፍለጋ ጉዳዮች ላይ ትኩረት እናደርጋለን።

ከዚህ አንፃር ስንመረምር የታለን ራስን ፍለጋ እንዲጨናገፍ ይፈታተነው የነበረው ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መልስ በፍጥነት እንዲያገኝ መጠየቅና ይህ ካልሆነ የመኖር ትርጉም ማጣትና በዚህ የሚፈጠርን ሀዘን የመቆጣጠር ችግር ነው። በዚህም ምክኒያት ራሱን ለማጥፋት በተደጋጋሚ ማሰብ ገጥሞታል። ይህ ብቻ ሳይሆን ራሱን ከማህበረሰቡ ማግለል ድርጊቶችን ከላይ ባሉት ክፍሎች ተንትነን አይተናል። ለዚህ ትልቅ ማስረጃ የሚሆነው ቸቸ ለፈረንጆች በተሰጠ ጊዜ የተፈጠረው ክስተት ለፀረ ራስን ፍለጋ ትልቅ ምሳሌ ይሆናል።

*ልበለድ ቢሆን እንዲህ ባልጨረስኩት ነበር። ግን ህይወት ነው። ያው እውነት የማይገባው እውነታ የታከለበት። ምን ማድረግ እችላለሁ። ሁለት ወር ያክል እኔ ቹቹን ሆኜ ነበር፤ ወይ ቹቹ እኔን ሆኖ ነበር። ልክ ስለአንት የተቸነከረው ጌታ አቅም ሲያንሰው መስቀሉን በሽክም የማገዝ እድል ቢገጥምህ እንደማለት ነው። ሁለት ወሩን እንዲያ ነው የተመለከትኩት።*

*ሁለተኛ ወር ቹቹን ሆኜ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ፍራሽ ላይ ነቃሁ። … ስሰማ ከፀበልና ከቃልቻ በኋላ የእምሮ ሃኪም ዘንድ ቀረብኩኝ። …( አለማየሁ 2009፣ 214)።*

ታለ ከቹቹ ጋር ተቀያይረሃል ተብሎ ከተነገረ በኋላ ከጥያቄዎቹ በመጠኑ እረፍት ለማግኘት ሀዘኑን ለመጋራት በማሰብም ጭምር ከራሱ ከፍል አብሮት እንደሆነ አድርጎ ነበር። በዚህ መካከል እናቱ ቹቹን ለፈረንጆች መስጠታቸውን በሰማ ጊዜ የተፈጠረበት ከፍተኛ የሀዘን ስሜትና የአዕምሮ መታወክ ለሁለት ወር ታሞ የስነ ልቦና ባለሙያ ጋር እስከመሄድ አድርሶት ነበር። ይህ ከፍተኛ የሆነ የሀዘን ስሜትን የመቆጣጠር ችግር ምናልባት በስነልቦና ሃኪም በቶሎ ባይታገዝ ውጤቱ ከፍተኛ የአዕምሮ መቃወስ/ መታመም ድረስ ሊደርስ የሚችልና ራስን ፍለጋውን የሚያጨናግፍ ሊሆን ይችል ነበር። ምክኒያቱም ራሱን የማጥፋት አደጋም ሊገጥመው ይችል ስለነበር ማለት ነው።

ሌላው በህይወት እርካታ ማጣትና በሕይወት ደስተኛ አለመሆን ይታይበት ነበር። ይህ እርካታ ማጣት ደግሞ መሰላቸት፣ ከስራ ቦታ መልቀቅ፣ ራስን ለማጥፋት ማሰብ ችግሮችን እንዲጋፈጥ ምክኒያት ሁነውታል።

*ይብላኝ ለእኔና ለጠቢቡ ሰለሞን ፤ እምነትና እረፍትን ላጣን ፤ ህይወት የከንቱ ከንቱ ከንቱ ለሆነችብን፤ ኑሮን መልሶ መላልሶ የማመንዠክ ዑደት ለሆነብን፤ ደስታና ረፍትን ላጣን … በመጨረሻ በእኔና በጠቢቡ ሰለሞን ሳቅኩ ፤ ለእኔና ለጠቢቡ ሰለሞን አዘንኩ … ለተፈጠርንበት ያልኖርን ከንቱ፣ከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ… ንፋስ ተከታዮች ( አለማየሁ 2011፣36)*

ታለ በተለያየ ጊዜያት ራሱን ከጠቢቡ ሰለሞን ጋር ሲያነፃፅር ይታያል። የመጀመሪያው ጠቢቡ ሰለሞን ሰባት መቶ እቁባቶች አሉት ሚለውን በመውሰድ፣ እሱ ደግሞ ሰባት ሴት እህቶች በመኖሩ ምክኒያት የሚያገኘውን እንክብካቤ ሲያጠይቅ ሲሆን፣ሁለተኛው ደግሞ በዚህ አውድ

ውስጥ እንደተናገረው ጠቢቡ ሰለሞን " ከንቱ ፣ከንቱ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ።" የሚለውን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በትይዩ በማምጣት ነው። ይሕ የሚያመላክተው ታለ በመድር ላይ ምን ያክል ጣዕም ወይም የመኖር ትርጉም እንዳጣ በትይዩ በማምጣት ለመግለፅ ነው።

ሌላው በመጀመሪያዎቹ አመታት የነበረው በሴቶች ዘንድ እንደ ወንድ አለመታየት፣ ይልቁንም ሴታሴት መባል፣ ይህን ተከትሎ ደግሞ በወቅቱ የወንድነት መራቢያ አካሉ በፍጥነት ዝግጁ አለመሆን ወደኋላ ከሴቶች ጋር ለነበረው ተደጋጋሚ ወሲባዊ ፍላጎት( ወንድ መሆኑን ለማሳየት) መነሻ ሆኖታል ብሎ መውሰድ ይቻላል። በዚህም ከሲፈን፣ ከለገነት፣ ከነፀብራቅ፣ ከናትራን እንዲሁም ከኤልዛቤል ጋር ወሲባዊ ግኙኙነት እንደነበረው በሶስቱ መጻሕፍት በግልፅ ታይቷል።

ይህ የሻዶው *ሥረመሰረታዊያን* በሚያረጋግጥ መልኩ ይህ የመበቀል ስነልቦና ተደብቆ ያለ ነገር ግን በተግባሩ የሚረጋገጠው ሴቶች ላይ ባለው ግንኙነት ነው። ይህም ከሲፈን "ወንድ" ሁን ንግግር ጋር የሚመሰረትና ከሲፈን ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ ኬሎች ጋር ህይወት ሲጀምር በመወደድ ወይም በመፈለግ መኩራራት ውስጥ በመግባት እነሱን ደጅ ማስጠናት፣ ከወሲብ ያለፈ ዘላቂ ህይወት አለማሰብ ታይቶበታል። ይሕ የበቀል ስሜት ደግሞ የተደጋገመና በንግግር ጭምር የተረጋገጠ ነው። *"እራሴን ተፀየፍኩት፤ የት እንዳለሁ በማላውቅ ምንነቴ ላይ ጥላቻ አደረብኝ። እንደዛር ተፈናጥጦ እንደ አዶ ከበሬ እኔ ላይ ገዝፎ ለሌሎች ሲያሳጣኝ የኖረው ማንነቴ የመበቀል ብርቱ ፍላጎ አደረብኝ።"( አለማየሁ 2011፣64)*

## 3.7.ራስ እና ኢጎ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

ኢጎ በዩንጊያንም ይሁን በፍሩዲያን ንድፈሀሳብ አስፈላጊ እሳቤ ነው። በዩንጊያን ንድፈሀሳብ ኢጎ በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት መገንባት ያለበት ሰዎች ለራስ የሚሰጡት ከፍ ያለ ግምት መገለጫዎች ናቸው። በሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ይህን በመጀመሪያው አጋማሽ ህይወት ያደገውን ኢጎ በሚገባ መቆጣጠር ካልተቻለ አፍራሽና የራስን ፍለጋ ሂደቱ እንዳይሳካ እንዲያውም እንዲጨነግፍ ሚያደርግ ነው።

ከዚህ አንፃር በታለ የራስን ፍለጋ ህይወት ስንተነትን ሁለት አጋማሽ ህይወት በሚለው የራስን ፍለጋ እሳቤ ስር ከአካላዊ ስብዕና ፣ ከእውቀት እንጻር እንዴት ኢጎውን ከፍ ማድረግ ቻለ የሚለውን ተመልክተናል። ከዚህ በታች ደግሞ ታለ ኢጎውን በትክክል መቆጣጠር አለመቻሉ በራስን ፍለጋ ህይወቱ በምን መልኩ እንዲወጣ ረዱት ሚለውን እንመለከታለን።

ታለ ከተፈጠረበት የራስን ፍለጋ ሂደት ውስጥ "ሴታሴት" መባልን "ወንድነት" መገለጫዎች በመቀየር፣ "አላዋቂነትን" "አዋቂነት" በመቀየር የራሱን ክብር ከፍ ማድረግ ችሏል። ነገር ግን ይህ የራስ ክብር ከፍ ማለትና አንዳንዴ ይህን መቆጣጠር አለመቻሉ በራሱን ፍለጋ ሂደት ላይ ምን ይዞ መጣ? ምን አስከተለበት? የሚለውን እንመለከታለን።

ታለ በሶስተኛው መፅሐፍ **ሐሰተኛው በእምነት ሥም** የመጨረሻዎቹ ምዕራፍ ላይ አዲስ አበባን ትቶ አይነ ምሳ ከሄደ በኋላ ነፀብራቅ (የዩንቨርስቲ መምህርትና የሴት ጓደኛው) እሷን ጨምሮ በሌሎች ላይ ያደረሰውን ስነልቦናዊ ጉዳት እንዲህ ትወቅሰዋለች።

> በአካል ያሉትን፣ የሌሉትን ሰዎች ሁሉ ታሪክ አዳምጫለሁ። የሁላችንም ቁስል ተመሳሳይ ነው። እንባችን ቢሰፈር እንኳን እኩል ነው። ሲፈን… ለገነት…ሊሊ… ናትራ…እኔ… እናትህ… አባትህ…እህቶችህ… ጠናጋሻው… ቹቹ… የቹቹ እናት… ብዙ የፈሰሱ እንባዎች እንደ ምንደር ውሃ መውረጃ ያለምንም ፀፀት ተሸግረሃቸው አልፈሃል (አለማየሁ 2012፣ 239)።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው ታለ በተለይ ከሴቶች ጋር በነበረው ግንኙነት ለሚፈፅመው ጉዳት ምንም ደንታ ሳይሰጡት ከአንዷ ወደ አንዷ ሲሸጋገር ታይቷል። ይህ ደግሞ ከላይ በተነተነው መሰረት "ሴታሴት" መባሉን የሚበቀልበት እንደሆነ ኢጎውን በሚገባ መቆጣጠር ያለመቻሉ ውጤት እንደሆነ አይተናል። ይህን ደግሞ እራሷ ነፀብራቅ መልሳ አስረግጣ ስታስረዳው ይታያል። መልዕክቱ በዩንቨርስቲ የፍልስፍና መምህርቷ አፍ እንዲናገር መደረጉ ሀሳቡ ሚዛን የሚዲፋና አመክንዮ ያለው መሆኑን ማስረገጫ ነው።

> *ብዙ ያልቋጨኸው ህይወት ውስጥህ አለ። ደፋር አይደለህም። ጀግንነት ይጎድልሃል። መቋጨት ድፍረት ይጠይቃል። በሴት ህይወት ውስጥ ጥያቄ እንደሆንክ ማለፍ ደጋግመሃል። መቋጨት ማግባት አይደለም። የምትሸሸው ትዳርን አይደለም። ህይወትህ እንደ ጀሮ ጌጥ ተንጠልጥሎ ትወዛወዛለህ። ለማረፍ አልታደልክም። ይሄ ደግሞ ከሌላው ይልቅ በራስህ ላይ ጨካኝ መሆንክን ይናገራል። ከእኛ ጋር ሳይሆን መጀመሪያ ከራስህ ጋር ታረቅ። ሌላውን ሳይሆን መጀመሪያ እራስክን መጉዳት አቁም… (አለማየሁ2012፣239)።*

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ ታለ በህይወቱ ከሰዎችም ላይ ካደረሰው ጉዳት በላይ ራሱንም እየጎዳ ያለው ፍርሃት መሆኑ መረዳት ይቻላል። ፍርሃትን መቆጣጠር አለመቻሉ ደግሞ ኢጎው

መቆጣጠር አለመቻሉ ማሳያ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በታለ ራስን ፍለጋ የታየው ከፍተኛ ፀረራስን ፍለጋ አካል መሆኑን ጭምር አይተናል፡፡ ነገር ግን በመጨረሻም ጊዜ ቢሆን ኢጎውን ለመግዛት እድል እንደተፈጠረለት ምንረዳው ፀፀት ውስጥ መግባቱ ነው፡ ይህን ከዚህ በታች በቀረበው የታለ ሀሳብ ለማስረገጥ እንሞክር፡-

> *ከድክመቱ ጋር ፊት ለፊት የሚጋፈጥ ማን ነው? ነፀብራቅ እንድታጠቃኝ ተመቻችቼ ጠብቄያታለሁ፡፡ የምትናገረው እውነት ነው፤ የጠራቻቸው ሰዎች በሙሉ በእኔ የተጎዱ እንደሆኑ ግን አስቤ አላውቅም፡፡ ልበ ደፍን ያስመሰለኝ ይሄ ነው፡፡ ሰው ለሆነ ሰው ለራስ ይቅርታ ከማድረግ የከበደ ነገር የለም፡፡ ነፀብራቅ ያሰሰችውን ቦታ ሁሉ ላስስ? የገኘችውን ሁሉ ላግኝ? እንዴት በደፈናው ለራሴ ይቅርታ አደርጋለሁ? እንግዲህ አይነ ምሳ የወቀሳ ሥፍራየ መሆኗ ነው (አለማየሁ 2012፣240)፡፡*

## 3.8. ራስ እና ፈጣሪ በአለማየሁ ገላጋይ ልቦለዶች ውስጥ

ታለ የራስን ፍለጋ ሂደት ውስጥ ከነበረው ቤተሰባዊ ግንኙነት መነሻ ከጠየቃቸው ጉልህ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ፈጣሪን በተመለከተ መሆኑን በላፉት እሳቤዎች ለመመልከት ችለናል፡፡ ታለ በራስን ፍለጋ ሂደቱ እግዚአብሔርን( ፈጣሪን) እና እምነትን እንዴት እንደፈለጋቸው እንመልከት፡፡

ታለ በመጀመሪያው የራስን ፍለጋ ጊዜያት እምነትን ከማርክሳዊ እይታ አንፃር በመረዳት ፈጣሪ (እምነት) አለመኖር የሚያጎሉ ክርክሮችን ሲያደርግ የነበረ መሆኑን **በታለ በዕውነት ሥም** መጻሕፍ ላይ ከጠና ጋሸው ጋር ባደረገው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም *"ማርክስ ያለው ትክክል ነው እምነትን በተመለከተ፡፡ መበዝበዣ መሳሪያ ነው፡፡ ስራ ጠል የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሰራተኞቹን ምንዳ አስፈራርተው የሚቀራመቱበት፣አላማው ከምድርና ከቁሳቁስ እቶ ፈንቶ የማያልፍ ተራ ማታለያ" (አለማየሁ 2011፣19)፡፡* በማለት ያስረዳል፡፡

በዚህ ክርክር ላይ ጠና ጋሻው የሚታመን እንኳን ባይኖር ማመን ግዴታ እንደሆነ፣ ለዚህም ደግሞ የሰው ልጅ ሰማያዊና መንፈሳዊ አፈጣጠር ያለበት መሆኑ፣ ባይሆን እንኳን የማይጨበጡት ሰማያዊና መንፈሳዊ ትርክቶች ብቻ መልስ የሚሆኑት ፍጡር እንደሆነ አስረጅዎችን በማጣቀስ ሊያሳምነው ይሞክራል፡፡ ነገር ግን ታለ ይህ የፍልስፍና ተማሪ ጠባይ አለመሆኑን እና መፈተሽ ግዴታው እንደሆነ ያስረደዋል፡፡ ነገር ግን በቀጣይ ባደረጋቸው

ፍለጋዎች የሰው ልጅ ዝም ብሎ ስጋዊ ፍላጎቱን ብቻ እየፈፀመ የሚኖር ፍጡር አለመሆኑን ተረድቷል። ይልቁንም የእምነት ፍላጎት አንዱ በህይወት ለመኖር መሰረታዊው ጥያቄ መሆኑን ጠቁሟል። ከዚህ መነሻ የተለያዩ የእምነት እይታዎችን በማምጣት በመመርመር ራሱን ለማግኘት ሞክሯል።

> *ሰው በዳቦ ብቻ የማይኖር እንግዳ ፍጡር ነው። የጥበብ፣ የመመራመርና የእምነት ፍላጎቶቹ በህይወት ለመቆየት የሚያስፈልጉ መሰረታዊ እስከመሆን ደርሰዋል። ሩሲያዊው ደራሲ ፊዮዶር ደስተ-ቭስኪ "... the secreat of the man's being is not only to live " ያለው ለዚህ ነው። " but to have something to live for" የሰው ልጅ መኖር ብቻ በሌጣው አይሻም። የሚኖርለት የህይወት ፍች ይፈልጋል፤ እንዲያ ካልሆነ በምድር ላይ ከመቆየት ይልቅ እራሱን በራሱ ቢያጠፋ ይመረጣል። ይላል ዶስተየቭስኪ ( አለማየሁ 2012፣ 115-116)።*

ከላይ በቀረበው ፅሁፍ የምንረዳው ታለ መጀመሪያ ከነበረው እምነት የለም የሚል አቋም የሰው ልጅ ለመኖራቸው ምክኒያት እምነት አንዱ መሆኑን መመርመር መጀመሩ፣ እግዚአብሔር ( ፈጣሪ) ማን ነው ወደ ሚል ፍለጋ እንዲሄድ መንደርደሪያ ሁኖታል።

በዩንጊያን የፈጣሪ እሳቤ መሰረት ፈጣሪ በሰው ልጅ አዕምሮ ውስጥ ያለ እንደሆነ ያብራራሉ። ይህን በትክክል ሊገጥም በሚችል መልኩ ታለም የተለያዩ ሙህራንን አስተያየቶችን በማምጣት ሲሞግት እና ሀሳቡን ሲያጤን ይስተዋላል። ሌላም ማስረጃ እንጨምር፡-

> *ፍጥረት ሁሉ ስህተት የተፈጥሮም ብሎም የፈጣሪን አለመሟላትና ፍፅምና ማጣት የሚያመላክት አይሆንም? ሰሪው በተሰሪው ውስጥ አይደል? "ታላቁ ተጠራጣሪ" በመባል ሚታወቀው Robert Ingrosoll ምን ሲል ተናገረ " An honest God is the noblest work of man " ሳቁ አመለጠኝ ። ፈጣሪ ይሄንን የተፈጣሪ ድምዳሜ ሲሰማ አይስቅ ይሆን?*( ዝኒ ከማሁ፣ 15)።

በዚህኛውም ሀሳብ እንደምንረዳው ፈጣሪ ያለው በሰው ልብ ውስጥ ነው። ይህም ፈጣሪ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ብቻ ያለ የሰዎች የፈጠራ ውጤት እንጂ ህልው እንዳልሆነ ተገንዝቧል። ለዚህ ደግሞ እንደ ዋንኛ መከራከሪያ ያደረገው ፈጣሪ ካለ የራሱን/የታለን ጨምሮ የሰው ልጅ

ለሚጠይቃቸው የህይወት ጥያቄዎች በቶሎ መልስ እየሰጠ መሄድ ነበረበት ከሚል መነሻ ነው። የታለን ጥያቄ ከታች ባለው ማስረጃ ጨምረን እናጢነው፡-

> *… እኛ እሱን በመፍጠራችን ልንፀፀት ይገባል። ከዚህ የተሻለ ያስቀመጥንበትን ቦታ የሚመጥን እግዚአብሔር መፍጠር ይገባን ነበር። የአጥቢያ ዳኛ ይመስል የሐጢያት መዝገብ አገላብጦ 'አንተ ለእሳት'፣ 'አንተኛው ለገነት' የሚል ብሎ መፍረድን እንኳን ታላቁ እኔንስ ይመጥናል ይሄን ታላቅነት እኔ እፈልገዋለሁ?…*
>
> *ኡ!ኡ!ኡ!     (ዝኒ ከማሁ፣ 84)።*

ታለ ፈጣሪን በዳግም ምፅዐት ፍርድ ሰጭ ብቻ እንዲሆን ይገደብነው እኛ ሰዎች ነን። ማለትም ሰዎች በአዕምሯችን እግዚአብሔርን ስንፈጥር በዚህ መልኩ መገደባችን ትክክል አለመሆኑን እና ሰዎች ይህ የምንፈልገውን እግዚአብሔር(ፈጣሪ) መስራት ባለመቻላችን ልንቆጭ ይገባል በማለት ይሞግታል። አሁንም ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ በመጨመር ታለ ፈጣሪ የለም ወይም ደግሞ የእኛ የሰዎች የማሰብ አቅም ፈጣሪን በትክክል መድረስ አይችልም በማለት ያስረግጣል።

> *…እንደተባለው እግዚአብሔር የለም። ወይንም እግዚአብሔር ሞቷል! የእኛ የመፍጠር አቅም ሆነ የማሰብ አድማስ ትክክለኛውን ፈጣሪ አይሸከመውም። መፍጠር ህልውናው የሆነ አምላክ ቁጭ ብሎ ጥንት በፈጠራቸው ላይ ለመፍረድ መከዳ አያሞቅም። ሌላ ይፈጥራል… ሌላ… ሌላ … አንዴ ከፈጠራቸው ጋር ጉዳይ የለውም። ምስጋና ለማትረፍ የሚፈጠር የፈጣሪነት ሚና ሊኖረው አይችልም።*
>
> *ኡ! ኡ! ኡ!     (ዝኒ ከማሁ፣ 84)።*

ከላይ ከቀረቡ ሀሳቦች በግልፅ የምንረዳው ታለ እምነትን(ፈጣሪን) ለመፈለግ የሚያደርገው ሂደት ቀላል አለመሆኑን አሳይቷል። ይህንንም ኡ! ኡ! ኡ! በማለት ጭምር ገልፆታል። ለዚህ ደግሞ እምነት ማመን፣ መታመንን ወይም እምነት ሁሉንም ጠይቀን በአመክንዮ አስተንትነን የምንረዳው ብቻ ባለመሆኑ ነው። ይህ ደግሞ በስተ መጨረሻ በሶስተኛው መፅሀፍ መጨረሻ ላይ ምንም እንኳን የፍልስፍና ተማሪ ቢሆንም (ፍልስፍና መጠየቅና በአመክንዮ መረዳትን ያስቀድማል) ከእናቱ የበለጠ አማኝና የፈጣሪን ህልውና በዕምነት በመቀበል ያጠናቅቃል። እንዲህ በማለት፡-

*ጭንቅላቱ በተዓምር ደዌ ተይዟል፡፡ የተማርኩና በአመክንዮ የማምን እንደሆንኩ ለራሴ ብነግርም ፤ ከእናቴ የማልሻል ጭፍን አማኝ ነኝ፡፡ ጋሊሊዮ ከስንት መቶ አመታት በፊት የደረሰበትን የህዋ ቁመና ስጋየ እንጂ ነፍሴ አልተቀበለችውም፡፡ ዛሬም ለእኔ ሰማይ ማህሌታይ ያሬድ እደተቀኘበት ያለ ባለ ሰባት ድርብ ከምድር በላይ ያለ ሰገነት ነው፡፡ ጠፈር… ምጽነዐት… ሰማይውዱድ… ሄኖስ… ኢዮር… አርያም… መንበረ ፀባዖት… የእኔ ሰማይ ምንዛሬዎች ናቸው፡፡ መላዕክታት ሱራፌል ካህናት ሰማይ፣ መብረቅ ለብሰውም ለምስጋናና ለሰው ልጅ ምህረት ይዘምራሉ፡፡ … ይወርባሉ ( አለማየሁ 2011፣ 302)፡፡*

ከላይ በቀረበው የመፅሀፍ የመጨረሻ ገጽ ፅሁፍ በተመለከተ ታለ በስተመጨረሻ ይህን ፍልስፍና ተማሪና በአመክንዮ የሚያምንና እስተመጨረሻው ሲሞግትበት የነበረው የእምነት ራስን ፍለጋ በዚህ መልኩ እንዴት ተጠናቀቀ? የሚል ሀሳብ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ይህን ጥያቄ አንድም የራስን ፍለጋ ሂደቱ ሁነት ወይም መልስ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ግን ደራሲው ተደራሲያንን ታሳቢ በማድረግ ሆን ብለው በገፀባህርይው አፍ የሰጡት ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. ማጠቃለያና መደምደሚያ

### 4.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "በፍቅር ሥም"፣"ታለ በእውነት ሥም" እና "ሐሰተኛው በእምነት ሥም" ልቦለዶች ውስጥ የራስን ፍለጋ ስነልቦናዊ እሳቤን በይነቴክስታዊ ንባብ በማድረግ መተርጎም፣ማሳየትና መፈከር ዓላማው አድርጎ የተሰራ ነው። ጥናቱ በሶስቱ ልቦለዶች ዘላቂ ገፀባህርይ በሆነው ታለ ላይ የተደረገ ሲሆን የዩንጊያን የራስን ፍለጋ ጽንሰሀሳብ የእሳቤው መገለጫ ባህርያት እና ሥረመሰረታዊያን አንፃር የራስን ፍለጋውን ሂደት ተተንትኗል።

ቡድን እና ግለሰብን በተመለከተ ታለ በመጀመሪያዎቹ የራስን ፍለጋ ጊዜያት ራሱን ከቡድኑ ወይም ከማህበረሰቡ ጋር ማስማማት የቻለበት፣ እንዳውም ያለውን ጥያቄ ከቡድኑ ተረድቶ በቡድኑ ተግዞ ለመፍታት ጥረት የሚያደርግ ነበር። ነገር ግን ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት በኋላ ግን ከቡድኑ ጋር ግጭት ውስጥ ገብቶ ታይታል። ይኸውም በዋንኛነት ራስን ፍለጋ ውስጥ ነኝ በሚል መገለልና ራስን ለማጥፋት ማሰብ ድረስ ተስተውሏል።

በታለ የራስን ፍለጋ ሂደት ሁለት አጋማሽ ሂደት በትክክል ተንፀባርቋል። ይህም በመጀመሪያዎቹ የራስን ፍለጋ ህይወት ሂደት የራሱን ክብር መገንባት ነው። ይኸውም በማህበረሰቡ ወንድ የሚያስብለውን ጉዳዮች መፈጸም እና ራሱን በሌሎች ዘንድ የአዋቂነትን ክብር( በፍልስፍና ተከራክሮ የሚያሸንፍ) ሁኖ መገኘት ነበር። ይህን በተከታታይ ማድረግ እንደቻለ በትንተናው ተረጋግጧል። ከዚህ በመቀጠል ወደ ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት በስኬት የተሸጋገረ ሲሆን ይህ ደግሞ በዚህ ምድር የመጣበትን ዓላማ መጠየቅ፣ ፈጣሪን መርምሮ ለመረዳት የጣረበት እና የፈጣሪና የተፈጥሮን ግንኙነት የመረመረበት( የፈለገበት) ነበር።

ግንኑነትን በተመለከተ የቀደሙት የታለ የልጅነት ግንኙነቶች ወደ በኋላ ያደረገው የራስን ፍለጋ ሂደት ላይ ያመጣበትን ተፅዕኖ የሚያሳይ ነው። በዚህም በትንተናው ዋና ገፀባህርይው ከእናቱ፣ ከቤተሰቦቹ፣ ከመጀመሪያ የፍቅር ጓደኛው ጋር የነበረው የመጀመሪያዎቹ የልጅነት አመታት ከፍተኛ ተፅዕኖ የራስን ፍለጋ መነሻዎች መሆናቸውን ተመልክተናል። ይህም ግንኙነት በራስን ፍለጋ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽዎ እንዳለው ጥናቱ አረጋግጧል።

ራስን ፍለጋ ሁነት ወይስ ሂደት ሚለውን ሁለቱን መሆኑን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመጀመሪያዎቹ አጋማሽ ህይወት የነበሩ ራስን ፍለጋ ጥያቄዎች ሁነት ሁነው መቋጫ ያገኙበት፣ ነገር ግን ሁለተኛው አጋማሽ ህይወት ጥያቄዎች ሂደት መሆናቸው በትንተና ተረጋግጧል፡፡

ራስን ፍለጋ መገኛ በተመለከተ ጥናቱ የታለን የራስን ፍለጋ ሂደት በመተንተን ራስን ፍለጋ በየትኛውም ማንነት ውስጥ ያለ እንደሆነ ( የተማረ ይሁንም ያልተማረ) ነገር ግን ምሁርነት (ወደኋላ የደረሰበት ሁነት) የራስን ፍለጋን የበለጠ አመክኗዊ ለማድረግና ለማፋጠን እንደጠቀመው አመላክቷል፡፡

በታለ የራስን ፍለጋ ህይወት ያጋጠሙ ፀረ ራስን ፍለጋዎች መኖራቸውን ጥናቱ አረግጧል፡፡ ይህም ለራስን ፍለጋው በቶሎ መልስ ካላገኘሁ የሚል በህይወት  ተስፋ መቁረጥና ፍርሃት ናቸው፡፡ ይህም ራስን ፍለጋው መጨናገፍ ባይደርስበትም ፈተና ገጥመውት ነበር፡፡ ለዚህም ራስን እስከማጥፋት ማሰብና መፀፀት የፀረ ራስን ፍለጋው ውጤቶች ሁነው ተመልክተናል፡፡

ራስና ኢጎን በተመለከተ ጥናቱ ኢጎ በመጀመሪያው የራስን ፍለጋ ህይወት የሚጎለብትና በሁለተኛው የራስን ፍለጋ ህይወት መቆጣጠር ሚገባ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ይህ ኢጎ ለራስን ፍለጋ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለውም ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ገፀባህርይው ኢጎን በመጠኑም ቢሆን የመቆጣጠር ችግር ገጥሞት ነበር፡፡ ይህም ሴቶች ላይ ለፈፀማቸው ጉዳቶች መነሻ እንደሆኑ እና በስተመጨረሻም መፀፀቱ ግን ራስን ፍለጋው እንዳይጨናገፍ እንደረዳው ተመልክተናል፡፡

ራስና ፈጣሪን ስንመለከተ በታለ የራስን ፍለጋ ሂደት እስከመጨረሻው ጊዜ ፈጣሪ የለም፣ ፈጣሪ በሰዎች አዕምሮ የተፈጠረ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ከዩንጊያን ፍካሬ ልቡና አንፃር እሳቤውን የሚገጥም ነው፡፡ ነገር ግን በሶስተኛው መፅሀፍ በመጨረሻው ገፅ ከፍልስፍና ተማሪነቱ ባፈነገጠ መልኩ ፈጣሪን አማኝ መሆኑን በመናገር መፅሐፉ ይጠናቀቃል፡፡ ይህ ምናልባት አንድም የራስን ፍለጋ ሂደቱ ደረሰበት እልባት ሊሆን ይችላል፡፡ አለበለዚያ ግን ደራሲው ተደራሲያንን ያገናዘበ ልህቀት ለመስጠት ሆን ብሎ ያደረገው ሊሆን ይችላል፡፡

በጥናቱ ታለ  በተለይ "ሴታሴት" ለሚሉት ሰዎች "ወንዳወንድ" ሆኖ ለመታየት የራሱ ማንነት ያልነበሩ ፀባዮች ይላበስ ነበር፡፡ ይህ በግልፅ ፐርሶና መሆኑን ያመላክታል፡፡ ምክኒያቱም መጀመሪያ የነበረው ፀባይ ወንዳወንድ ለመሆን በቂ ስላልነበር ወንድ ለመባል እየፈራ ጀግና

የመምሰልን ጭንብል ሲያጠልቅ ነበር፡፡ ይህ ማስመሰል ደግሞ እውነት አለመሆኑ ከራሱ አንደበት ሲያስረግጥልን አይተናል፡፡

ጥናቱ በታለ ማንነት ውስጥ የተሸፈኑ ተፈጥሯዊ ማንነቶች (ሻዶው) መኖራቸውንም አረጋግጦልናል፡፡ እነዚህም ከልጅነቱ በተፈጠሩበት ግንኙነቶች ምክኒንያት አዕምሮው ውስጥ የተደበቁ ነገር ግን በኋለኛው ህይወቱ ሲንፀባረቁ አይተናል፡፡ ይህም ከሴቶች ጋር የነበረው ግንኙነት የበቀል ስሜት መኖር፣ ፍርሃት፣ በእውቀት አለመበለጥ ወዘተ. ሻዶዎች ሲንፀባረቁ ታይተዋል፡፡

በታለ ራስን ፍለጋ ጋር በተያዘ በእሱ ውስጥ የሴት ማንነቶች መንፀባረቃቸው ከዩንግ ንድፈሀሳብ አንፃር አኒማ መሆኑን አይተናል፡፡ ይህ ደግሞ በዋንኛነት ከአረማመዱ፣ከተግባሩ አንፃር ማስረጃዎችን ተንትነን ማስረገጥ ችለናል፡፡

የዩንጊያን የራስን ፍለጋ መገለጫ እሳቤዎች ለልቦለዶቹ ጭብጥ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽዎ ነበራቸው፡፡ ይህን በእያንዳንዱ እሳቤዎች ስር የተጠየቁ የራስን ፍለጋ ጥያቄዎችና የተገኙ መልሶች፣ እንዲሁም ሂደቶች ልቦለዱ እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋጽዎ አላቸው፡፡

በመጨረሻም በሶስቱም መጻሕፍት የቀረቡ ትንተናዎች  ከሹሜት የዩንጊያን የራስን ፍለጋ መገለጫ ባህርያትም ይሁን ከሥረመሰረታዊያን አንፃር ሲፈተሽ ታለ ራስን ፍለጋ ሁነትና ሂደት ላይ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ ለራስ የመሆን ጥያቄዎች መልስ ያገኙባቸው (ሁነቶች) እንዳሉ ሁሉ፣ በሌላ በኩል በጊዜ ሂደት መልስ የሚያገኙ እንዳሉ አረጋግጠናል፡፡

## 4.2 መደምደሚያ

ታላሚ ልቦለዶችን ከዩንጊያን የራስን ፍለጋ የእሳቤው ዋና መገለጫው ባህርያትና ሥረመሰረታዊያን አንፃር ሲተነተን ታላሚ ገፀባህርይው ታለ በጭንብል ተጀቡኖ፣ በውስጣዊ ማንነት እየበገነ በሰባዊነት ተወጥሮ፣ ራሱን ሳይሆን ራሱን ሊሆን ከወዲያ ወዲህ የሚባዝን ገፀባህርይ ነው፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

*ቀዳማይ ጽሁፎች*


አለማየሁ ገላጋይ። (2009)። <u>በፍቅር ሥም</u>። አዲስ አበባ፣ሔሪቴጅ ኅትመትና ንግድ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር።

አለማየሁ ገላጋይ። (2011)። <u>ታለ በዕውነት ሥም</u>። አዲስ አበባ፣za printing press።

አለማየሁ ገላጋይ። (2012)። <u>ሐሰተኛው በእምነት ሥም።</u> አዲስ አበባ፣H&F።


ካልዐይ ጽሁፎች


*ሰብለ ወ/ኪዳን።(2010)።"የእኔነት ሐተታ በተመረጡ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ"።* የፒ.ኤች.ዲ መርሃ ግብር ማሟያ ቀረበ ጥናት፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ።

*ቴዎድሮስ አለበል።(2006)። "ልጅነት በማህሌት አልጋና መስር፤ስነልቡናዊ ንባብ"።* ኤም.ኤ.ድግሪ ማሟያ፣ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ጥናት ክፍል፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ።

ቴዎድሮስ ገብሬ።(2001)። <u>በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ</u>። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

*አሸናፊ መለሰ።(2007)። "አተኩሮ በብርሃን ፈለጎች ውስጥ"።* ለአርስት ማስትሬት ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ።

Can, B. E.( 2016). Literature and Psychology in the context of the interaction of social science ; Kazare jornal of humanities and social science, vol 19,4.

Casement,A.(2001). Carl Gustav Jung. Londen; sage publications.

Chopra, D.(2000). How to know god: the soul's journey into the mysteries of mysteries, Random House, New York, NY.

Emre,Ismet.( 2006).Edebiyat ve pasikoloji, Ankara; Ani Yayinicilik.

----------------( 2009). " yeni Turk Edebiyatinin piskoloji Kayanaklari",Turkish studies ,4(1) 319-355.

Fordham, F 1969, 'Some Views on Individuation', Journal of Analytical Psychology, vol. 14, pp. 1-12.

Fordham, M 1958, 'Individuation and Ego Development', Journal of Analytical Psychology, vol. III, no. 2, pp. 115–30.

Holland,N.N (1990) To psychoanalytic psychology and literature- and- psychology, New York; Oxford university press.

Jung,C.G.(1931). The aims of psychology.CW 16.

--------------(1935). The relation the Ego and Unconscious

---------------(1951). Aion.CW 9ii.

--------------(1954).On the nature of the psyche. CW8.

Neumann, E 1954, The Origins and History of Consciousness Routledge & Kegan Paul., London.

Schmidt, M.A. (2005). 'Individuation: finding oneself in analysis-taking risks and making sacrifices', The Journal of Analytical Psychology, Vol 50,5,595-616.

Solak, Omer (2014).Edebiyat Biliminin Disiplinler arasi Imkanlari, Ankara; pegem Akademi.

Wellek,R., & Warren ,A( 1963).The Theory of literature.London; penguin.

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1.Beside literature and psychology there is no other branch of science which is engaged so much in the study of relationship between human body and soul with its contradictions and dilemmas, making efforts to define relationship interms of certain rules, to know the mysterious aspects of human soul and and its sub conscious areas by means of long and detailed journeys ; at the same time both branches have been struggling in their existence between arts and science for about a century (2006, III)

2.Literature and psychology are two branches of science that study human soul. Psychology researches human behavior and their causes while literature depicts human behavior through fiction. These two branches of social science studing human behavior are interrelated and mutually beneficial.(2016 ,49)

3."Psychological elements will be present in literary works as long as human are the theme of the text. Literature psychology covers almost everything we must to know about literature, because literature is product of mind." (2016,50)

4.Today we all know that Dostoevsky is one of the most important person indispensable for psychology and that his text are used as text book and reference books in the psychology departments. But the same thing is done literature and the study of literature. Psychological data is used both by authors in the process of the characters of imaginary world and by literature researchers in their efforts to penetrate the inner world of existance litrarary works (2009, 325)

5.From the literature stand point, analyzing psychology based on the writer, poet and literary work is look at it from a new perspective by providing practical data for it."(2004,104)

6. The rationa governing agent of the psyche, through the ego lacks the strong vitality of the id so that they may be released in no destractive beheveral patterns, and though a larje portion of the ego is unconsciousness, the ego nevertheless comprises what we ordinarily think of as the conscious mind.( Guerin Etal 157)

7. Individuation is is a complex process not easy to define. My own understanding aligns closely with Mc Neely who states, that in its simplest form, individuation means choosing to be

conscious, or mindful and specially, it means become conscious of the person. we are capable of being in our fullness,our strength and our limitations'(2014፣13).

8.The process of forming and specializing the individual nature …(and)… the development of the psychological individual as differentiated being from the general collective psychology"(1969,1)

9.Jung saw it is the process of self realization, the discovery and experience of meaning and purpose in life; the means by which one find aone self and become who one really is. It depends on the interplay and synthesis of opposites e.g., consciousness and unconsciousness, personal and collective, psyche and soma, divine and human, life and death. (2005,597)

10. Individuaton proceds in two major movements. First, it requires a person to break up (I, e to analyze and make conscious) the prevailing state of unconscious identification with extera new figures and psychic contents. This movementshasthe effect of creating a mirror of consciousness. Second after a person had made headway with his analysis, individuation requires paying carefull and continuous attention to the emergency of life (2005,2)

11. The principle of individuation defines the essence of the human. It is absolutely fundamental to human beings to distinguish them selves from their surroundings. This is essential nature of individual consciousness;to be itself , it must crate distinctions and separateness. It is in accord with human nature, therefore to seck individuation.(Stein 2005፣3)

12.The aim of individuation is nothind less than to diverse the self of the false wrappings of the persona on the one hand, and the suggestive power of primordial image on the other. (1935, 269)

13.if someone is over conserned with his owun personal affairs and personal status he is danger of becoming too identified with his persona, e,g the school teacher who is dedicated at home, or the analysis who never stop analyzing. Living such blinkered life, focused on short- sighted and egocentric goals, denies the values of the collective. Thise can lead to a narcissistic allination from a deeper sence of oneself and ones place in a society. (2005፣595)

14. Individuaton proceds in two major movements. First, it requires a person to break up (I, e to analyze and make conscious) the prevailing state of unconscious identification with extera new figures and psychic contents. This movements has the effect of creating a mirror of

consciousness. Second after a person had made headway with his analysis, individuation requires paying carefull and continuous attention to the emergency of life (2005,2)

15.The self is relatedness… The self only exists inasmuch as you appear. Not that you are, but that you do the self. The self appears in your deeds and deeds always mean relationship.” (Jung 1935-39, p. 73

16.Another area of confusion is whether Jung considered individuation to be a state, capable of being attained, or an on-going process…However he also argues that individuation is an active on-going process and not a static state when he proclaims…Individuation can be seen as a process that is never fully completed but is one that can generate experiences, which feel, momentarily, as if it has been attained.

17.only experienced by those who have gone through the wearisome but… indispensable business of coming to term with the unconscious components of the personality"(1954,430)

18.How widespread is individuation? Is it universal and commonplace or aristocratic – a vocation for the elite? Of course this depends upon what we mean by it. Jung calls individuation an unconscious natural spontaneous process but also a relatively rare one, something…Individuation requires the development of ego, but it is not synonymous with it. Although the process of deintegration and reintegration occurs throughout life.

19.Our clinical work reminds us that the Self is not always experienced as benign and positive. It can be self-regulating and yet the experience of it can also be very destructive. The ego needs to be sufficiently strong to withstand the coming into awareness of aspects of the unconscious, which is the greater part of the self. Ego strength is dependent upon how successful mother and baby have been in creating a facilitating environment to manage anxieties, surrender omnipotent fantasies, form symbols, establish, mourn and repair object relationships.

20.The self, in its quest for consciousness, requires the surrendering of ego inflation. The narcissistic delusion that the ego is the self. Although purposive, the self can be experienced as violent and distractive if the ego is unable to facilitate its expression. This may result in an individuation crisis for both analyst and patien. (2005꞉50꞉601)

*21.P*sychology…is not in a position to make metaphysical statements. It can only establish that the symbolism of psychic wholeness coincides with the God-image, but it can never prove that the God-image is God himself, or that the self takes the place of God.” (1951 : 308)

*22.*jung (1942a) saw the ego in service to the Self – its representative on earth. The Self he called the Greater Personality, ultimately unknowable, linked to a universal sense of cosmic unity – not surprisingly he related to it as the image of God within us. He went further and described self realisation, as seen in religious or metaphysical terms, as amounting to God’s incarnation. Jung saw God, in psychological terms, as an archetype in that there has to be something in the psyche which resonates with the manifold images of God throughout history.

23.A)The containment /nurturance stage ; symbolized as ‘matriarchal’ stage.

B)The adapting /adjusting ,symbolized : as the ‘patriarchal’ stage, and

C)The centering / integrating , individual stage. ( 1954)

24.These three stages should not be thought of as entirely separates, they are stages of growth and development that graduates from one in to next signifying the predominant attitudes during the major eras of person’s life journey. Futures of each stage continue in to the next but in less predominate way, and can be revisited through the persons lifespan. One does not enter the stages for a particular period of time, pass through this stage and then leaves it behind when one enters the next stage. (stein 2013,p.4)

25.The definition of persona is that it represents that aspects of individual which is in relation to the outer world. It drives from the Greek world for ‘mask’ and denotes those mask that were worn by actor is performing comic/ tragic part in Greek plays. The less acceptable part of the personality are kept hidden behind the prosona. Awelldifferentiated persona developes a well fitting persona and the letter is essential for survival. (Cassment 2001: 142)

26.The most identifiable archetype is ‘the prosona’, the term Jung used to denote the outer face we represented to the world, the role the individual playes in life. The prosona is not the sence of what one is. It is how one appears to other in the world and is governed by external factors – culture, time in history, life staged development,and the experience encounterd. (Ann,2014: 18-19)

27.The shadow is the prosona unconscious; it is all those uncivilized desires and emotional that are compatable with social standards and our ideal personality, all that we are ashamed of, all that we don’t want to know about ourselves. It follows that the narrower and more restrictive the society in which we live the larger will be our shadow (Fordham; 244)

28. Ignoring or repressing our dark side is the norm, the sobering truth is that running from the shadow only intensifies its power. Denying it only leads to more pain, suffering, regrets and resignation. If we fail to take responsibility and extract the wisdom that has been hidden beneath the surface our consciousness minds, the shadow will take charge, and instead of us being able to have controle over it, the shadow minds up having controle over us, triggering the shadow effect. (Copra, 2010;2)

29.The pain it brings up is the pain we have been fleeing most of our life ; the psycho emotional breakdowns it catalyzes are the pre cursors to hugely relevant breakthrough… real shadow work not only breaks us dowun but also breaks us open, turning frozen yesterdays in to fluid now(masters 2010, 44-45)

30. The self has both the center and the totality of psyche, it has strong clame to be regarded as the central concept of the entire psychology. The self is the goal towards which the process of individuation strives.